# በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


ለ በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ (M.A) ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ


ባዩ ተሾመ


ሰኔ 2004 ዓ/ም

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

# በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ

**በ**

**ባዩ ተሾመ**

**ሰኔ 2004 ዓ/ም**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

1. ጌታሁን አማረ (ዶ/ር) ________________
   አማካሪ ፊርማ

2. ጌታቸው እንዳላማው (ረ/ፕ) ________________
   የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

3. ብቃለ ስዩም (ዶ/ር) ________________
   የውጭ ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

ለመቆምም ሆነ ለመቀመጥ በጣም የሚያሰቃየኝን ከባድ የነርብ ህመምና የተስፋ መቁረጥ ስሜት በትዕግስት ተቋቁሜ ለዚህ እንድደርስ ያበቃኝ ፈጣሪ አምላኬ ቸሩ እግዚአብሄር ዛሬም፣ ዘወትርም፣ ለዘለአለሙ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን፤ አሜን፡፡

የዚህን ጥናት ርዕስ የመጨረሻ ቅርጽ ከማስያዝ ጀምሮ ደረጃ በደረጃ የሰራኋቸውን ስራዎች በማየትና በማረም፤እንዲሁም ጠቃሚ የሆኑ ምክሮችን በመለገስና አቅጣጫ በማስያዝ ጥናቴ ለዚህ እንዲበቃ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶክተር ጌታሁን አማረ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለዚህ ጥናት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች በመስጠት ለተባበሩኝ ትምህርት ሚኒስቴርና የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ፤ መጠይቆችን በቀናነት በመሙላት ለተባበሩኝ መምህራንና ተማሪዎች፤ እንዲሁም ፍጹም ቀና በሆነ ስሜት በቃለ መጠይቅ ምላሻቸውን ለሰጡኝ የመማሪያ መጻህፍቱ አዘጋጆች ከፍ ያለ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡

ያጋጠመኝን የጤና መታወክ ተቋቁሜ ትምህርቴን በትዕግስት ጠንክሬ እንድቀጥል በሀሳብ፣ በገንዘብና በልዩ ልዩ የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፋቸው ላልተለየኝ ወንድሜ ሰለሞን ተሾመና እህቴ ሐይማኖት ተሾመ፤ የክፍል ባልደረቦቼ አግዐዚት ገብሩ፣ አበበች ገብሩ፣ ልዕልት ግደይ፣አስቻለው ይልማ፣ከድር ጋሻው፤ የረጅም ጊዜ ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ ስለሺ አዛገው፣ ዝናቡ ቱኑ፣ ጌታቸው መኮንን፣ አበበ ደሴ፤ እንዲሁም ይህንን ጥናት ከጅምር እስከ ፍጻሜው ለተየበችልኝ እህቴ ወይንሸት አሸናፊ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


ምስጋና ------------------------------------------------------------------------------------------------I

ማውጫ ------------------------------------------------------------------------------------------------II

የሰንጠረዥ ማውጫ ---------------------------------------------------------------------------------V

አህጽሮተ-ጥናት/አጠቃሎ ------------------------------------------------------------------------ VI

**ምዕራፍ አንድ ------------------------------------------------------------------------------------------- 1**

1. መግቢያ -------------------------------------------------------------------------------------------- 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------------------------------------------------------------------------------- 1

1.2 የጥናቱ አላማ ------------------------------------------------------------------------------- 4

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ --------------------------------------------------------------------------- 5

1.4 የጥናቱ ወሰን -------------------------------------------------------------------------------- 6

**ምዕራፍ ሁለት------------------------------------------------------------------------------------------- 7**

2. ክለሳ ድርሳን -------------------------------------------------------------------------------------- 7

2.1 ሰዋስው ምንድነው? ----------------------------------------------------------------------------- 7

2.2 የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ------------------------------------------------------------------ 8

2.2.1 የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ሚናና አስፈላጊነት ---------------------------10

2.2.2 የሰዋስው ትምህርት ግብአት ------------------------------------------------------------12

2.3 በሰዋስው ትምህርት ላይ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች -----------------------------------------16

2.4 በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ----------------------------------------------------------------------------------20

2.4.1 በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ -----20

2.4.1.1 ግልጽነት --------------- ---------------------------------------------------------21

2.4.1.2 ትክክለኛነት ----------------------------------------------------------------------22

2.4.1.3 ተመጣጣኝነት -------------------------------------------------------------------22

2.4.1.4 ተገቢነት ---------------------------------------------------------------------------23

2.4.2 በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ----24

2.4.2.1 ተከታታይነት ---------- ----------------------------------------------------------26

2.4.2.2 ቀጣይነት ----------------------------------------------------------------------27

2.4.2.3 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ---------------------------------------------28

2.4.2.4 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ---------------------------------------------28

2.5 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት --------------------------------------------------------------29

**ምዕራፍ ሦስት ------------------------------------------------------------------------32**

3. የአጠናን ዘዴ ----------------------------------------------------------------------------32

3.1 የጥናቱ መረጃ ምንጮች ------------------------------------------------------------32

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ -------------------------------------------------------32

3.2.1 የሰነድ ግምገማ ---------------------------------------------------------------32

3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ --------------------------------------------------------------32

3.2.3 ቃለ መጠይቅ -----------------------------------------------------------------33

3.3 የናሙና አወሳሰድ ----------------------------------------------------------------33

3.3.1 የመማሪያ መጻህፍቱ ናሙና አወሳሰድ ----------------------------------------33

3.3.2 የዞንና የከተማ ናሙና አወሳሰድ ------------------------------------------------34

3.3.3. የትምህርት ቤቶች ናሙና አወሳሰድ -----------------------------------------34

3.3.4 የመምህራን ናሙና አወሳሰድ --------------------------------------------------35

3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ --------------------------------------------------35

3.3.6 የመጻህፍቱ አዘጋጆች ናሙና አወሳሰድ -------------------------------------38

3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ------------------------------------------------------------38

**ምዕራፍ አራት ---------------------------------------------------------------------40**

4. የመረጃዎች ትንታኔ -------------------------------------------------------------------40

4.1 የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ ቅኝት ----------------------------------------------40

4.2 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ --------42

4.2.1 ከግልጽነት አንጻር --------------------------------------------------------------42

4.2.2 ከትክክለኛነት አንጻር ----------------------------------------------------------54

4.2.3 ከተመጣጣኝነት አንጻር --------------------------------------------------------58

4.2.4 ከተገቢነት አንጻር ---------------------------------------------------------------63

4.3 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት -------68

4.3.1 ከተከታታይነት አንጻር ---------------------------------------------------------69

4.3.2 ከቀጣይነት አንጻር ------ -------------------------------------------------------------------79

4.3.3 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንጻር ----------------------------------------83

4.3.4 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር ----------------------------------------88

**ምእራፍ አምስት ---------------------------------------------------------------------------------95**

**5. ማጠቃለያና የመፍተሄ ሀሳብ** --------------------------------------------------------------------95

5.1 ማጠቃለያ ---------------------------------------------------------------------------------------95

5.2 የመፍትሄ ሀሳብ ---------------------------------------------------------------------------------96

**ዋቢ ጽሁፎች ------------------------------------------------------------------------------------98**

**አባሪዎች**

አባሪ አንድ፡-የመማሪያ መጻህፍቱ አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ ምላሽ -------------------------- 101

አባሪ ሁለት፡- የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ----------------------------------------------------- 110

አባሪ ሶስት፡- የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ----------------------------------------------------- 112

አባሪ አራት፡- የመማሪያ መጻህፍቱ አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ ------------------------------- 114

## የሰንጠረዥ ማውጫ


**ይዘት** **ገጽ**

ሰንጠረዥ አንድ፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ --------------------35

ሰንጠረዥ ሁለት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የቁራ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር -------------------------36

ሰንጠረዥ ሶስት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የጎርጎቻ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር -------------------------37

ሰንጠረዥ አራት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር ------------------------------------------37

ሰንጠረዥ አምስት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛትና የጾታ ስብጥር -----------------------------------------37

ሰንጠረዥ ስድስት፡- የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ መረጃ ---------------------------------42

ሰንጠረዥ ሰባት፡- የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ -----------------------------------------44

ሰንጠረዥ ስምንት፡- የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ -------------------------------------46

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የስርጭት ሁኔታ ------------------------------------------------------------------59

ሰንጠረዥ አስር፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የድግግሞሽ መጠን ---------------------------------------------------------------70

## አህጽሮተ-ጥናት/አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አቢይ ትኩረት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ነው። የዚህ ጥናት አቢይ የመረጃ ምንጭ የሰነድ ግምገማ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ አጋዥ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል። ጥናቱ በዋናነት አይነታዊ ወይም ገላጭ የምርምር ዘዴን ለመረጃ ትንተናው ተጠቅሟል። በዚህም መሰረት በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ ከግልጽነት፣ ከትክክለኛነት፣ ከተመጣጣኝነትና ከተገቢነት አንጻር ፈትሿል። እንዲሁም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹን አደረጃጀት ከተከታታይነት፣ ከቀጣይነት/ተለጣጣቂነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አንጻር ያላቸውን ገጽታ መርምሯል። በዚህ ጥናት በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀቶች በክለሳ ድረሳን ውስጥ ከቀረቡ ጽንሰ ሃሳቦች አንጻር እየታዩ የተተነተኑ ሲሆን፤ በናሙናነት ከተመረጡ መምህራንና ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ፣ ከመጻህፍቱ አዘጋጆች ደግሞ በቃለ መጠይቅ በተገኙ ምላሾች ትንታኔውን ለማጠናከር ተሞክሯል። በዚህም መሰረት የሰዋስዋዊ ይዘቶችን አቀራረብ በተመለከተ በአራቱም ተተኳሪ መጻህፍት ውስጥ ችግሮች መኖራቸውን በተደረገው ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል። በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የተካቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት በተመለከተ ደግሞ በአራቱም መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የአደረጃጀት ችግር እንደሚታይባቸው የተደረገው ግምገማ ያሳያል። በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የታዩ ድክመቶችን ለማሻሻል ያስችላሉ ተብሎ የታመነባቸውን የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች ለመጠቆም ተሞክሯል፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ የታዩትን የአቀራረብና የአደረጃጀት ችግሮች ለማስወገድ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤ ተማሪዎችና ልዩ ልዩ የትምህርት ባለሙያዎች ስለ መማሪያ መጻህፍቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ያላቸውን አስተያየት መስጠት እንዲችሉ እድሉን ማመቻቸትና ግብረ መልሶችን በተግባር ላይ ማዋል፤ወዘተ።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ዘመናዊ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳብ ከመምጣቱ በፊት የነበሩትን የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳቦችን Batston(1994) በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ውስጥ ይመድቡዋቸዋል፡፡ እነዚህም ዋናዋና ክፍሎች ውጤታዊ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳብ እና ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳብ ናቸው፡፡ በ Batston ገለጻ መሠረት ሁለቱ ጽንሰ ሀሳቦች የተለያየ ባህሪ ያላቸው፣ በተለያየ ዘመን ውስጥ በተናጠል የተሰራባቸውና የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የነበሩዋቸው ናቸው፡፡

ለተወሰኑ ዘመናት እንደ ኋላ ቀርና ጎታች ታይቶ የነበረው ውጤታዊ የሰዋስው ማስተማር ጽንሰ ሀሳብ ምንም እንኳን ብዙ ደካማ ጎኖች ቢኖሩትም በዚያው ልክ ጠንካራ ጎኖችም ስላሉት መናቅ እንደሌለበት የቅርብ ጊዜ ጥናቶች ያስገነዝባሉ፡፡ ይዘቶችን ለመምረጥና ለማደራጀት የስነ ልሳን ትወራዎችን እንጂ የተማሪውን ፍላጎት መሠረት አለማድረጉ፣ለቅርጽ እንጂ ለፍች ትኩረት አለመስጠቱ፣ድርጊታዊ የማስተማር ስልት አለመጠቀሙና በራስ የመማር ዕድልን ለተማሪ አለመፍቀዱ ከሚሰነዘሩበት ነቀፌታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተቃራኒው ግብአቶችን መርጦና አደራጅቶ ማቅረቡ፣ ውስን አላማን ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ ቅርጽ ላይ መገደቡና የጽንሰሀሳብ ግንዛቤን ማስጨበጡ ጠቃሚ ጎኖቹ እንደሆኑ ምሁራን ይገልጻሉ (Batston፣1994፤Leech፣1994፤Harmer፣1991)፡፡

ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልትም የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖች ስላሉት እንደ እንከን የለሽ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ ለፍች እንጂ ለቅርጽ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ግብአቶችን መርጦና አደራጅቶ ለተማሪ አለማቅረቡ፣ ውስን አላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ላይ አለመገደቡና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ሳያስጨብጥ ተማሪውን በጭፍን ወደ ተግባቦት ልምምድ ውስጥ ማስገባቱ ደካማ ጎኖቹ እንደሆኑ ጥናቶች ይገልጻሉ (Batston፣1994፤Leech፣1994፤Nunan፣1988)፡፡

ከ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ውጤት-ወሂደት የቋንቋ ማስተማር ስልተ-ትወራ ተቀባይነትን አግኝቶ በስፋት እየተሰራበት ይገኛል(Tonkyn፣1994፤Batston፣1994)። ይህ ዘዴ ቀደም ባሉት ዘመናት በተናጠል ሲሰራባቸው በነበሩት በውጤታዊና በሂደታዊ ስልተ-ትወራዎች ጠንካራ ጎኖች ላይ የተመሰረተ ነው። በውጤት-ወሂደት ስልተ-ትወራ መሠረት የሰዋሰው ትምህርት ለቅርጽም ለፍችም ትኩረት መስጠት አለበት። የስነልሳን ትወራዎችንና የተማሪውን ፍላጎት መሠረት አድርጎ፣ ግብአቶችንና ክንዋኔዎችን መርጦና አደራጅቶ ለተማሪው ማቅረብ ይኖርበታል። የተለያዩ የመማር እስትራቴጂዎችን ለተማሪው ሊያቀርብ ይገባል። የትምህርቱ አቀራረብ በቅርጽ ላይ ከሚደረግ የጽንሰ ሀሳብ ማስጨበጥ ልምምድ ተነስቶ በተገቢ ሁኔታ ወደ አውዳዊ የተግባቦት ልምምድ ሊሸጋገር እንደሚገባና የተማሪዎችን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ወይም ቅርጽ ላይ መገደብ እንዳለበት ወይም የተወሰነ አላማን ይዞ መነሳት እንዳለበት ምሁራኑ ይገልጻሉ።

በመሆኑም አንድን ቋንቋ በአፍ መፍቻነትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማር ተማሪ የታላሚውን ቋንቋ ስነልሳናዊ እውቀት ሊያዳብርለት የሚችል የሰዋስው ትምህርት ያስፈልገዋል። ይሁን እንጂ ሁለቱ የተማሪ ቡድኖች (አፍ-ፈት፣ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ) የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው በሚማሩበት አላማ፣ ወደ ትምህርቱ ይዘውት በሚመጡት የሰዋስውና የገሃዱ አለም እውቀት አይነትና መጠን፣ እና በመሳሰሉት ተላውጦዎች ስለሚለያዩ የተለያየ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ስልት እንደሚያስፈልጋቸው በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያስረዳሉ (Batston፣1994፤Leech፣1994፤Ur፣1996)።

በአጠቃላይ አንድን ቋንቋ በአግባቡ መካን ይቻል ዘንድ የሰዋስው እውቀት አስፈላጊ መሆኑን መገመት አያዳግትም። ይህ የሰዋስው እውቀትም በሰው ልጆች አእምሮ ውስጥ ያለና መኖሩ እንኳ የማይታወቅ ወይም በትምህርት የተገኘ እውቀት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የአንድ ቋንቋ ቃላት እንዴት ባለ መልኩ መቀናጀት እንዳለባቸው ካላወቅን በቃላቱ ሳንጠቀም ወይም ሳንግባባ እንችላለን (Ur፣1988)። በተጨማሪም Batston(1994) እንደሚያስረዱት በአንድ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ችሎታ ከሌለን ወይም የቋንቋውን ሰዋስው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ካላወቅን በቋንቋው የምናደርገው የተግባቦት ሙከራ ደካማ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

ምክንያቱም ሰዋስው ቋንቋ ስርአታዊ የመግባቢያ መሳሪያ እንዲሆን ካስቻሉት ክስተቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ እንዲሁም ጌታሁን(1990፣V) ‹‹ክህሎትንና ስርአትን አቀናጅቶ ያስተማረ መምህር ቋንቋውን በተሟላ ሁኔታ አስተምሯል፡፡ ተማሪውም የተሟላ እውቀት አግኝቷል ማለት ይቻላል››፤ በማለት የቋንቋ ስርአት የጎደለው የቋንቋ ትምህርት ሙሉእ ሊሆን እንደማይችል ያስረዳል፡፡

ከላይ በምሁራኑ የቀረበው ገለጻ ሰዋስው የአንድ ቋንቋ ስርአታዊነት መገለጫ ማእከላዊ ክፍል እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡ እንዲሁም ሆን ተብሎ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚሰጥ መደበኛ የአፍ መፍቻ፣ የሁለተኛ ወይም የውጪ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው የማስተማር ተገቢነትና ጠቀሜታም ያመላክተናል፡፡

የሰዋስው ትምህርት በተደራጀ መልክ ከሚሰጥባቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የተማሪዎች መማሪያ መጻህፍት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚተገበር የትምህርት አሰጣጥ ስልት የመማሪያ መጻህፍት ግንባር ቀደምት የዕውቀት ማስተላለፊያ ወይም የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የመማሪያ መጻህፍት በየትምህርት አይነቱ የሚዘጋጁ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በጥንቃቄ የተመረጡና የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይችሉ ዘንድ በዝግጅት ወቅት የተለያዩ ስነልሳናዊ፣ ስነትምህርታዊና ስነልቦናዊ ንድፈ ሀሳቦችን እንዲሁም እንደ መርሃ ትምህርት ያሉ የትምህርት ሰነዶችን መሰረት እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዝግጅት ወቅትም ይሁን በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ወይም ፍተሻ ሊደረግባቸውና ከዚህም በሚገኙ ምላሾች ሊሻሻሉ እንደሚገባ Stern(1992) እና Cunningsworth(1995) ይገልጻሉ፡፡

በሀገራችን አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተቀርጾ በተግባር ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ክልሎች ካላቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በመጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል) ለሚማሩ ተማሪዎቻቸው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን አዘጋጅተው በስራ ላይ አውለዋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ በተለያዩ ክልሎች ያለው የአገልግሎት ደረጃና የተማሪዎች ችሎታ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ካለው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ

በመነሳት ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎቻቸው ተስማሚ የመማሪያ መጻህፍት እንዲያዘጋጁ መደረጉ የራሱ የሆኑ አወንታዊ ገጽታዎች ይኖሩታል፡፡

የመማሪያ መጻህፍቱን ዝግጅት ለክልሎች መስጠቱ ብቻ ሀገራዊ ደረጃቸውን ከመጠበቅና የመጻህፍቱን ብቃት ከማጎልበት አንጻር በቂ አይሆንም፡፡ በየክልሎቹ የሚዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል የቋንቋውን ስነልሳናዊ፣ ስነትምህርታዊና ስነልቦናዊ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት አድርገዋል? በየደረጃው ከተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶችስ ጋር ምን ያህል ተዛምደዋል? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱና ተገቢ ምላሽ ሊያገኙ ይገባል፡፡ እነዚህ መሪ ጥያቄዎችም ለዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ሆነዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር ከተዘጋጁ የተማሪዎች መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት (ደብብህክመ) ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (ከ5ኛ-8ኛ ክፍል) ተማሪዎች ታስበው የተዘጋጁት ይገኙባቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ቀደም ሲል የተጠቀሱትን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ በክልሉ መንግስት በተዘጋጁ በነዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት እንዲሁም በየደረጃው ከተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድ ለመገምገም ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህን አጥኚ ለጥናት በተመረጠው ክልልና የትምህርት እርከን ላይ ትኩረት ለማድረግም ያነሳሱት አቢይ ምክንያቶች፡- አንደኛ፣በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስውን ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት አስመልክቶ በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የተደረገ ጥናት አለመኖሩ፤ ሁለተኛ፣ በክልሉ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የኖረና በተተኳሪው እርከን ሲያስተምር የነበረ በመሆኑ፤ ይህ ዳራው ለጥናቱ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥርለት በማመኑ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ማደረግ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ

መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ጥናቱ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት ይፈትሻል፤ በየደረጃው ከተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶችም ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ይህን አጠቃላይ አላማ መሰረት በማድረግም ለሚከተሉት ቁልፍ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

1.2.1 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት የአቀራረብ መርሆችን ተከትለው በተገቢው መንገድ ቀርበዋል?

1.2.2 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ መልኩ ተደራጅተዋል?

1.2.3 የመማሪያ መጻህፍቱ ከሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት መርሆዎች እንዲሁም በየደረጃው ከተዘጋጁ መርሃ ትምህርቶች አንጻር ሲገመገሙ መሠረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ምን ጥንካሬዎች እና ድክመቶች አሏቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በዝግጅት ወቅትና ተዘጋጅተውም በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ በቀጣይነት መገምገሙ ይዘቶቹን በሂደት ለማሻሻልና ጥንካሬያቸው እየጎላ እንዲሄድ ለማድረግ የሚያስችል አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህ ጥናትም ይህንኑ ለማድረግ የሚሞክር እንደመሆኑ መጠን ሲጠናቀቅ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

1.3.1 በተተኳሪው የትምህርት እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚያዘጋጁና የሚያሻሽሉ አካላት በዝግጅታቸውም ሆነ በማሻሻል ሂደታቸው ሊገለገሉባቸው የሚችሉ ግብአቶችን ይጠቁማል፡፡

1.3.2 በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ቀጣይነት እንዲኖራቸው፣ ደካማ ጎኖቻቸው ደግሞ እርምት እንዲደረግባቸው የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል፡፡

1.3.3 ከዚህ በኋላ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ግብአቶችን ሊያመላክት ይችላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ተማሪዎች አዘጋጅቶ እየተገለገባቸው ባለው የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ላይ ነው። በመማሪያ መጻህፍቱም ሆነ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት የአማርኛ ትምህርት ይዘቶች በርካታ በመሆናቸው የሁሉንም ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሽ ሰፊ ጊዜና ገንዘብ ይጠይቃል። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚያተኩረው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ሲሆን አሁን በአገልግሎት ላይ ያሉትን መማሪያ መጻህፍት ብቻ የሚፈትሽ ነው። ከተተኳሪው እርከን በታችም ሆነ በላይ ያሉትን የመማሪያ መጻህፍትም ሆነ አስቀድመው በስራ ላይ ውለው የነበሩትን የመማሪያ መጻህፍት አይመለከትም። በተተኳሪው እርከን ያሉትንም የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ማስተማሪያ መጻህፍት (የመምህሩ መምሪያ) ጥናቱ አያካትትም። ከተተኳሪ ክልሉ ውጪ ያሉትን ሌሎች ክልሎችንም አይመለከትም።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 ሰዋስው ምንድነው?

ሰዋስው ምን እንደሆነ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰነዘሩ ፍችዎችን/ብያኔዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ጌታሁን (1990፣iv) የሰዋስውን ምንነት በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል፡፡

> በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበት ቋንቋ ‹እውቀት› የሚጠቁመውና በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለውን ችሎታ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አእምሯዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋ ስርአትና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለጻ የሚጠቁመው ነው፡፡ ይህ ፍቺ የአንድን ቋንቋ የስርአት ጥናት የሚመለከት ስለሆነ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው፡፡ በማለት የሰዋስውን ምንነት ይገልጻል፡፡

Ur(1996፣75) ደግሞ የሰዋስውን ፍች እንደሚከተለው ያቀርቡታል፡፡‹‹አንዳንድ ጊዜ ሰዋስው ቃላት ተገጣጥመው ትክክለኛ አረፍተ ነገር የሚመሰርቱበት መንገድ ነው››፡፡Ur እንደሚሉት ይህ ፍች ተማሪዎችን ስለሰዋስው ምንነት ለማስረዳት እንደ ጥሩ መነሻ የሚቆጠር እንጂ የመጨረሻ ፍች አይደለም፡፡ በአጠቃቀም ረገድ ሰዋስዋዊ የምንለው ነገር በአረፍተ ነገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባነሰ መልኩ ሊታይ እንደሚችል ኡር ያስገነዝባሉ፡፡ለምሳሌ፣ ‹‹ሁለት ሊትሮች ወተት ገዛሁ፡፡›› ቢል በአረፍተ ነገር ደረጃ ሰዋስዋዊ አይደለም፡፡ ሁለት የሚለው ቃል እስካለ ሊትር በብዙ ቁጥር መጻፍ አይኖርበትም፡፡ ከዚያም ባነሰ መልኩ ‹‹ሄጄ›› በሚለው ቅርጽ መነገርና መጻፍ ሲገባው ‹‹ሄድጄ›› ቢል ሰዋስዋዊ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል Cross(1991) ሰዋስው ግዙፍ የትምህርት መስክ እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ አያይዘውም ሰዋስውን በሁለት ገጽታ ማየት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም ገጽታዎች መዋቅር እና ሰዋስው በመባል ይታወቃሉ፡፡ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደሆኑ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ አንዱ ሲነሳ ሌላውን ማንሳት ወይም ማሰብ አይቀሬ ነው፡፡ ለምሳሌ ‹‹በሬ ጥጃ ወለደ›› በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የቃላት አሰላለፍ/አወቃቀር ችግር የለም፡፡ ነገር ግን ፍችው አያግባባንም ወይም ትክክል አይደለም፡፡ እንግዲህ ይህንን ነው ሰዋስዋዊ የምንለው በማለት ግልጽ ያደርጉታል፡፡ Cross እንደሚሉት የቃላት በስርአት

መሰለፍ በምሁራንና ተመራማሪዎች በጎ ፈቃድና መልካም አመለካከት የሚመጣ ሳይሆን የቋንቋው ተናጋሪ በመደበኛነት ያስለመደውን ቅደም ተከተል ወይም አሰላለፍና ፍች በመጠበቅ ላይ የተመሰረተ ነው ፤ ይህም እንደየቋንቋው ይለያያል፡፡


ሰዋስው ‹‹የአንድን ቋንቋ ሰርአት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሀረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው›› (ባየ፣2000፣xxi)፡፡ ስለሆነም ሰዋስው የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጸው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያለን የድምጾችን፣ የቃላትንና የሀረጋትን ስደራ የሚመለከት ነው፡፡ ስርአቱ ደግሞ የቋንቋው ተናጋሪዎች የለመዱትና በአጠቃቀም ወቅት ትክክል ወይም ስህተት ለማለት የሚያስችላቸው ነው፤ በማለት ባየ የሰዋስውን ምንነት በዚህ መልኩ ይገልጹታል፡፡

## 2.2 የሰዋስው ትምህርት ትኩረት

በቀደምት የቋንቋ ትምህርት ክንውኖች ውስጥ የቋንቋ ትምህርት አላማ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችና ህግጋት በማቅረብ ተማሪዎች በደንብ እንዲያጠኗቸውና እንዲካኗቸው ማስቻል ነበር፡፡ ለዚህም በምሳሌነት ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን መጥቀስ ይቻላል፡፡ Stern(1983) እና Larsen-Freeman(1986) እንደሚገልጹት በሰዋስው ወትርጉም ዘዴ የታላሚው ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርጾችና ህግጋት ማቅረብ ነበር፡፡ ለሰዋስዋዊ ቅርጾቹ አጠቃቀም እምብዛም አይጨነቅም፡፡ በክፍል ውስጥም ጥንታዊ የስነጽሁፍ ውጤቶች የሚቀርቡ ሲሆን በነሱ ላይ ተንተርሶ የቃላት ሽምደዳና ሰዋስዋዊ ትንተና ይሰጣል፡፡ በዚህ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ህግጋትን ብቻ ማስጠናት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ግን የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ህግጋትን ብቻ ማስተማሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ እንደ Larsen-Freeman(1986) እና Cunningsworth(1995) ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት የቋንቋው ቅርጽ ወይም መዋቅር፣ ፍችና አጠቃቀም መሆን አለበት፡፡ ሰዋስዋዊ ቅርጽ ወይም መዋቅር አንድ የቋንቋ ክፍል እንዴት እንደተዋቀረ ወይም እንደተገነባ ያሳያል፡፡ ፍች ደግሞ የሰዋስዋዊ ቅርጹን ወይም መዋቅሩን ትርጉም ያስገነዝባል፡፡ አጠቃቀምን በተመለከተ በአጭሩ ይህ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም ቀለል ባለ አገላለጽ በቋንቋውና ቋንቋው ለአገልግሎት

በሚውልበት አውድ መካከል ያለውን ግንኙነት ይመለከታል፡፡ አውድ ስንል ደግሞ ማህበራዊ አውድ፣ ስነልሳናዊ አውድ፣ የዲስኩር አውድ ወይም የቋንቋው ተጠቃሚ ቋንቋው በአገልግሎት ስላለበት አውድ ያለው ቀደምት እውቀት ሊሆን ይችላል፡፡ ከላይ የቀረቡትን ሶስት የሰዋስው ትምህርት ትኩረቶች በሚከተለው መልኩ በስዕላዊ መግለጫ ማቅረብ ይቻላል፡፡




Larsen-Freeman (1991፣280)

እንደ Larsen-Freeman (1991) ገለጻ በቀረበው ምስል ውስጥ ሶስቱ የሰዋስው ትምህርት ትኩረቶች በቅደም ተከተል የተቀመጡ አይደሉም፡፡ ስለዚህም በሰዋስው ትምህርት ወቅት አንዳቸው ከአንዳቸው ተበላልጠው ወይም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚቀርቡ አይደሉም፤በአንድ ላይ እንጂ፡፡ እርስ በርሳቸው በቀስት መያያዛቸውም የሚያሳየው እርስ በእርስ የተሳሰሩ ወይም የተገናኙ መሆናቸውንና አንዱ ጋ የሚከሰት ለውጥ የተቀሩትን እንደሚነካ ነው፡፡

Ur(1988) በበኩላቸው የታላሚውን ቋንቋ የተለያዩ ክፍሎች ወይም አካላት ቅርጽ፣ ፍችና አውዳዊ አጠቃቀም በተመጣጠነ መልኩ ማስተማር እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ ትምህርቱም በተለያዩ የቋንቋው ክሂል ትምህርቶች ማለትም በማድመጥ፣ በንግግር፣ በንባብና በጽሁፍ ውስጥ ተመጣጥኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህም በተለያዩ የቋንቋው

ክሂሎች ውስጥ ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርጽ፣ ፍችና አውዳዊ አጠቃቀም እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡

Harmer(1987) ቀደም ሲል የቀረቡትን ሀሳቦች በሚደግፍ መልኩ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በሰዋስዋዊ ቅርጾች ወይም መዋቅሮች ላይ ብቻ ማነጣጠር እንደሌለበት ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰዋስዋዊ ቅርጽ ወይም መዋቅር የተለያዩ ፍችዎች ሊኖሩት ይችላሉና፡፡ ስለዚህ በሰዋስው ትምህርት ወቅት የቀረቡ ሰዋስዋዊ ቅርጾች ወይም መዋቅሮች ከቋንቋው አጠቃቀም ወይም አገልግሎት ጋር መዛመድ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንንም ማድረግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ ገለጻዎችን፣ ምሳሌዎችንና መልመጃዎችን ለተማሪዎች በማቅረብ ማለማመድ ይገባል፡፡ በሌላ አገላለጽ አዲስ ሰዋስዋዊ ይዘትን ለተማሪዎች ስናቀርብ ቅርጽ ብቻ ሳይሆን አገልግሎትንም ልናስተምር እንደሚገባ፤ ፍች ብቻ ሳይሆን አጠቃቀሙንም ልናሳይ እንደሚገባ ልብ ማለት አለብን፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ ስንመዝነው የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቅርጽ ወይም በመዋቅር ላይ ብቻ ያነጣጠረ መሆን እንደሌለበት እንገነዘባለን፡፡ ይልቁንም የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጾች ወይም መዋቅሮች፣ በፍችና በአጠቃቀም ወይም በአገልግሎት ላይ መሆን አለበት፡፡ ይህም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሙሉ እውቀትና ብቁ ተግባቦት እንዲኖራቸው ከማስቻሉም በላይ ዘመናዊ የሰዋስው ትምህርት ክንውን በአንድ እጅ ለማጨብጨብ የሚሞክር አለመሆኑን ያሳያል፡፡

### 2.2.1 የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ሚናና አስፈላጊነት

ባየ (1987፣iv) የሰዋስው ትምህርት በተለይም ለሁለተኛ ቋንቋ ያለውን ጠቀሜታ አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> በክፍል ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር ግን የተለየ ጥቅም አለው፡፡ ...የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ከአዲስ የቋንቋ ስርአት ጋር ከማስተዋወቅ አንስቶ በሁለተኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ ይረዳቸዋል፡፡ አንድ የቋንቋ አጠቃቀም እንደ ሁኔታው ከሌላው የተሻለ ብቃት እንዳለው ለመረዳትና ለመጠቀምም ያስችላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የቋንቋውን ትምህርት ያፋጥናል፤ ይላሉ፡፡

Ubanya (1955፣26-27) ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ረገድ የሚታዩ ሶስት አይነት ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፡፡

1. የቋንቋ ሁለት ተማሪ ለቋንቋ መማር የሚመጣው የመጀመሪያ ቋንቋውን ክህሎት ይዞ ነው፡፡ ሌላ ቋንቋ ከመማር በፊት አንድን ቋንቋ ማወቅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪው የንግግር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ልምዶችን ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ሊያሸጋግር ይችላል፡፡ ሽግግሩ አወንታዊና አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡
2. ቋንቋ ሁለትን የሚማሩት አብዛኛውን ጊዜ በአገልግሎት ላይ በሌለበት አካባቢ ነው፡፡ ይህ ለተወላጅ ተናጋሪዎች መጋለጥ ያለመቻል ችግር ነው፡፡ የቋንቋው ትምህርት እንዳይፋጠን እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡
3. ከቋንቋ አንድ ይልቅ ቋንቋ ሁለት የሚያጠና ሰው በአገር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ አካባቢ ሊጠቀምበት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በቋንቋ ክሂሎችና እውቀቶች ቢያንስ ዝቅተኛ ችሎታ ይሻል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ሁለት ተማሪ ቋንቋውን በአገር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ከሚጠቀሙበት ሰዎች ጋር ለመግባባት የሚችልበት ደረጃ ለመድረስ የመጀመሪያ ቋንቋውን ጣልቃ ገብነትና ለሁለተኛ ቋንቋው ተወላጅ ተናጋሪዎች መጋለጥ ያለመቻል ችግሮችን መጋፈጥ መቻል አለበት፡፡

የ Ubanya ገለጻ ጠቅለል ባለመልኩ የሚያስገነዝበን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ አላማ ቋንቋውን ከሚጠቀሙበት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር መግባባት ለመቻል ነው፡፡ ይህንንም ማድረግ ይቻለው ዘንድ መሰረታዊ የሆኑ የቋንቋው ክሂሎችና እውቀቶች ያስፈልጉታል፡፡ በእርግጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሰዋስውን ትምህርት የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም እንደ Ubanya ገለጻ አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን ከሚጠቀሙበት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር አብሮ ለመጠቀም ወይም ለመግባባት ይቻለው ዘንድ ለዚህ የሚያበቃውን የሁለተኛ ቋንቋውን መሰረታዊ የሰዋስው እውቀት መገብየት መቻል አለበት፡፡ ይህ ሊሆን ከቻለ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርአት ጠብቆ በቀላሉ ለመግባባትና በቋንቋው ለመጠቀም ይችላል፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያ ቋንቋውን ሰዋስዋዊ ጣልቃ ገብነት ለመቋቋም ይረዳዋል፡፡ በአጠቃላይ እንደ Ubanya ገለጻ መሠረታዊ የሰዋስው ትምህርት ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ጠቃሚና ተገቢም ነው፡፡

እንዲሁም Cross(1991) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘትን አስመልክተው የሚከተለውን ይላሉ፡፡ ይዘት ተማሪው እንዲማረው የሚፈለገው ርዕሰ ጉዳይ ወይም ቁም ነገር ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ርዕሰ ጉዳይ ነው የተተለመውን አላማ ከግብ ሊያደርሰው የሚችለው፡፡ ከዚህ አንጻር ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ማዳመጥ፣ንግግር፣

ንባብ፣ጽህፈት፣እንዲሁም ሰዋስዋዊ መዋቅርና ስነጽሁፍን በይዘትነት በማቅረብ ማስተማር ይቻላል ይላሉ፡፡ ከ Cross ገለጻ ሰዋስዋዊ መዋቅር ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ከተገነዘብን ሰዋስው ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ያለው ሚናና አስፈላጊነት በምንም አይነት መልኩ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ አይችልም፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለጻ መገንዘብ እንደሚቻለው የሁለተኛን ቋንቋ ሰዋስው ሚናና አስፈላጊነት በሚከተሉት መንገዶች አጠቃሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህም ተማሪዎች ስለሌሎች ቋንቋዎች ተፈጥሮና ባህርይ ግንዛቤ እንዲያገኙ፤ ከራሳቸው ቋንቋ ጋር ማገናዘብ እንዲችሉ፣ ተገቢና ተቀባይነት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ወይም የሰመረ ተግባቦት መፍጠር እንዲችሉ፣ የንባብ፣ የጽሁፍና የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩና በቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡

### 2.2.2 የሰዋስው ትምህርት ግብአት

ለሁለተኛ ቋንቋ የሰዋስው ትምህርት የሚቀርቡ ስነልሳናዊ ግብአቶች መሰረት እንደሚደረገው የቋንቋ ማስተማር ስልተትወራ አይነት የተለያዩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ውጤታዊ ስልተ-ትወራን መሠረት የሚያደርጉ ወገኖች የታላሚውን ቋንቋ ቅርጻዊ ስርአት ወይም ቅርጻዊ ስርአቱንና ፍቺውን ከስነልሳን ትንታኔዎች አንጻር በጥንቃቄ መርጠውና አደራጅተው ያቀርባሉ፡፡ በአንጻሩ ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልተ-ትወራን የሚከተሉ ወገኖች ስነልሳናዊ ግብአቶችን ሳይሆን ክንዋኔዎችን ወይም አውዶችን ከተማሪው የመማር አላማና ዳራዊ ገጠመኝ አንጻር መርጠው ያቀርባሉ፡፡ ውጤት ወሂደት የቋንቋ ማስተማር ስልተ-ትወራን የሚከተሉ ወገኖች ደግሞ ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የስነልሳን ትንታኔዎችንና የተማሪውን ፍላጎት ወይም ዳራዊ ገጠመኝ መሰረት አድርገው ስነልሳናዊና አውዳዊ ግብአቶችን መርጠው በይዘትነት ያቀርባሉ (Leech፣1994፤Batston፣1994፤Nunan፣1988)፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት መስጠት ያለበት ከስነልሳናዉያን ትንታኔና ከማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ስርአት አንጻር ባሉት ሰዋስዋዊ ገጽታዎች ላይ ነው፡፡ ‹‹ሰዋስዋዊ ገጽታ›› የሚለው የቋንቋን ቅርጻዊ ስርአትና ፍች የሚመለከት ነው፡፡

ከውጤት-ወሂደት የቋንቋ ማስተማር ስልተ-ትወራ አንጻር ሲታይ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በግብአትነት መቅረብ ያለበት ሰዋስዋዊ ገጽታ ከስነልሳናዉያን ትንታኔ አንጻር ያለውን ቅርጻዊ ስርአትና ፍቺውን ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ስርአትንም ማካተት እንዳለበት የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ (Harmer፣1991፤Batston፣1994)።

### 2.2.2.1 ቅርጻዊ ሰዋስው

ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የታላሚው ቋንቋ ሰዋስው በይዘትነት ሊቀርብ እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ(Batston፣1994)። በ Batston ገለጻ መሰረት ቅርጻዊ ሰዋስው የቋንቋውን ቅርጻዊ ስርአት የሚመለከት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ Harmer(1991) ይህንኑ ሀሳብ የሰዋስው ቅርጽ (grammatical form) በማለት ገልጸውታል። ከዚህ አንጻር ሲታይ ቅርጻዊ ሰዋስው የሚለው ፍችን ሳያካትት ያለውን የቋንቋውን ስርአት ብቻ የሚመለከት ነው ለማለት ያስችላል።

ቅርጻዊ ሰዋስው ከቃላት ተለይቶ ብቻውን ያለ ነገር አይደለም። በ Batston(1994) ገለጻ መሰረት ቅርጻዊ ሰዋስውና ቃላት ተለያይተው ያሉ ነገሮች ሳይሆኑ እርስ በርስ ተሳስረው የሚገኙ ነገሮች ናቸው። በመሰረቱ ሰዋስው ማለት ድምጾች ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላት ተቀናጅተው ሀረግን ወይም አረፍተ ነገርን የሚመሰርቱበት ስርአት እስከሆነ ድረስ ቅርጻዊ ሰዋስውና ቃላት ወይም አረፍተ ነገር ተለያይተው ያሉ ነገሮች ናቸው ለማለት አያስችልም (Ur፣1996)።

ቅርጻዊ ሰዋስው በቃላት ላይ የሚገጠም ባእድ ነገር ሳይሆን አንዱ አቢይ የቋንቋ አካል እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ። ምሁራኑ እንደሚሉት ቅርጻዊ ሰዋስው እንዲሁ ተራ የሆነ የቋንቋ አደረጃጀት ስርአት ሳይሆን አንዱ አቢይ ተዋቃሪ የቋንቋ እውቀት ነው። ይህም በመሆኑ ይህ አቢይ የቋንቋ አካል ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በግብአትነት ቀርቦ ሊለማመዱት እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን የሚስማሙበት ጉዳይ ነው (Batston፣1994፤Leech፣1994፤Ur፣1996) ።

### 2.2.2.2 ሰዋስዋዊ ፍች

በዚህ ጥናት ውስጥ ሰዋስዋዊ ፍች የሚለው ስያሜ ከቅርጻዊ ሰዋስው ስር የሚውለውን ፍች ይመለከታል፡፡ ይህን ጽንሰ ሀሳብ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡ ለምሳሌ Ur(1996፣76) ‹‹ሰዋስዋዊ ፍች›› ብለው ሲገልጹት፤ Celce-Murcia and Hills(1988፣9) ደግሞ ‹‹ስነ ትርጉማዊ ፍች›› ብለው ገልጸውታል፡፡ Celce-Murcia and Hills ስነ ትርጉማዊ ፍች በማለት ለሰየሙት ሰዋስዋዊ ጽንሰ ሀሳብ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል፣ ‹‹ስነ ትርጉማዊ ፍች የተባለው ከስነ ትርጉማዊ አተያይ አንጻር የሚቀርብ ብዙ ጊዜ ተፈጥሮአዊ የሆነ የቅርጻዊ ሰዋስው ፍች ሲሆን ይህም ጊዜን፣ቦታን፣ሁኔታን፣ድግግሞሽን፣ወዘተ የሚገልጽ ነው››፡፡ Ur በበኩላቸው ‹‹ሰዋስዋዊ ፍች›› የሚለው ስያሜ ገላጭ ስነ ልሳናውያን የሚሰጡትን አይነት ፍች የሚመለከት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ውጤታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልተ ትወራን የሚከተሉ ወገኖች ሰዋስዋዊ ፍችን በጥንቃቄ መርጠውና አደራጅተው በግብአትነት ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ያቀርባሉ (Cunningsworth፣1995፤Batston፣1994፤Ur፣1996)፡፡ በአንጻሩ ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልተ ትወራን የሚከተሉ ወገኖች ሰዋስዋዊ ፍችን በይዘትነት ማቅረብን አይደግፉም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በነዚህ ወገኖች እምነት የቋንቋ ትምህርት በውጤት ላይ ሳይሆን ወደ ውጤቱ በሚወስደው ሂደት ላይ ማተኮር አለበት፡፡ ሂደት ብለው የሚጠሩትም በአውድ ውስጥ በቋንቋ የመግባባት ልምምድን ነው፡፡ ከዚህም እምነታቸው በመነሳት ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በይዘትነት የሚያቀርቡት ቅርጻዊ ሰዋስውንና ፍቺውን ሳይሆን አውዶችን (ሁኔታዎችን፣ርዕሰ ጉዳዮችን፣ወዘተ) እንደሆነ ጥናቶቹ ይገልጻሉ፡፡ ነገረ ግን በመስኩ የተደረጉ የቅርብ ጊዜ ጥናቶችን መሰረት አድርገው ምሁራን የሚያስገነዝቡት የታላሚው ቋንቋ ስነ ልሳናዊ ግብአት (ቅርጻዊ ሰዋስውና ፍቺው) ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ አስፈላጊ ስለሆነ በጥንቃቄ ተመርጦና ተደራጅቶ መቅረብ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ስለ ታላሚው ቋንቋ ስነ ልሳናዊ ግብአት ምንም መሰረት የሌለውን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ አውድ ብቻ አቅርቦ ተግባቦት እንዲፈጥር/እንዲያደርግ ማስገደድ ፍርሀትና ጭንቀት ውስጥ እንዲገባ ከማድረግ ያለፈ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም (Leech፣1994) ፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ይህን የሊች ሀሳብ ይጋራሉ፡፡ Richards and Rodgers(1986) በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን መሰረት አድርገው እንደገለጹት አፍላቂ ክሂል በግንዛቤ ክሂል ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ሁኔታው ከቋንቋ ማፍለቅ ተግባር በፊት ግንዛቤን የመጨበጥ ሂደት ሊቀድም የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የተማሪዎቹ ግንዛቤያዊ ክሂል ሳይዳብር አጠቃቀም ሂደት ውስጥ እንዲገቡ የሚደረግ ከሆነ ግን ተፈጥሮአዊ የቋንቋ መማር ሂደትን የተከተለ ባለመሆኑ ውጤቱ ተማሪዎቹን ስጋትና ጥላቻ ስሜት ውስጥ ያስገባቸዋል፡፡ ስለዚህም የሰዋስዋዊ ፍች ግንዛቤን ለመመስረት እንዲያስችል ግብአቱ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡ ሰዋስዋዊ ፍች ለአውዳዊ የቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ምጣኔ ሆኖ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ እንደሚያገለግል Batston(1994) ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህም የሰዋስው ፍች ግንዛቤ ከአጠቃቀም ሂደት በፊት በተወሰነ ደረጃ መሰረት መጣል ስላለበት ለዚህ ተግባር የሚውል የሰዋስዋዊ ቅርጽና የፍች ግብአት ተመርጦ ሊቀርብ ይገባል፡፡

ብዙ ጊዜ ሰዋስዋውያን የሚያቀርቡት የቅርጻዊ ሰዋስው ፍች ሰፊ ስርጭት ያለውን ነው፡፡ ስርጭቱ ሲበዛ ውስን የሆኑትን የቅርጻዊ ሰዋስው ፍችዎችን ከግምት ውስጥ ላያስገቡ ይችላሉ፡፡ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የሚቀርብ ሰዋስዋዊ ፍች ግን ሁለቱንም ያካተተ መሆን እንዳለበት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት በአውዳዊ አጠቃቀም ጊዜ ስርጭታቸው ሰፊ የሆኑት ብቻ ሳይሆኑ ውስኖቹም ተማሪውን ያጋጥሙታል የሚልነው(Celce-Murcia and Hills፣1998፤ Batston፣1994)፡፡

### 2.2.2.3 የቋንቋ አጠቃቀም ስርአት

የቋንቋውን አጠቃቀም ከሚወስኑት ነገሮች አንዱ ማህበረ-ባህላዊ ተላውጦዎች ናቸው (Batston፣1994)፡፡ በ Batston ገለጻ መሰረት ማህበራዊ ርቀት ወይም ቅርበት የሰዋስውን ፍች ወይም አጠቃቀም ይወስናል፡፡ ማህበራዊ ርቀት/ቅርበት ሲባልም በተራክቦ አድራጊ ግለሰቦች መሀከል ያለው የማህበራዊ ደረጃ/እርከን ልዩነትና የቅርበት ደረጃን ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ፡- በልጅና በአዋቂ፣ በተራ ሰውና በባለስልጣን፣ በተራ ግለሰቦች መሀከል፣ወዘተ ያለውን የማህበረሰባዊ ርቀት/ቅርበት ደረጃንም ለማመላከት በተግባቦት ውስጥ ያገለግላል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ለታላሚው ቋንቋ የአጠቃቀም

ስርአት እንግዳ ስለሆነ በጥንቃቄ ተመርጠውና ተደራጅተው በይዘትነት ሊቀርቡለት ይገባል።

ሌላው የቋንቋ አጠቃቀም ምርጫን የሚወስነው ስነልቦናዊ ርቀት ነው። በ Batston(1994) ገለጻ መሰረት በአመለካከታችን ወይም በስሜታችን መሀከል ያለው የርቀት/የቅርበት ደረጃ የቅርጻዊ ሰዋስው አጠቃቀማችንን ይወስናል። ለምሳሌ እውናዊ ድርጊቱ ያለፈ ሆኖ ትዝታው ግን አሁንም ከእኛ ጋር ያለን ነገር/ጉዳይ ለመግለጽ የምንጠቀምበት የግስ ቅርጽ የአለፈ ጊዜ አመልካቹን ሳይሆን የአሁን ጊዜ አመልካቹን ነው። በአንጻሩ ድርጊቱም ትዝታውም ከኛ የራቀ ከሆነ ሃላፊ ጊዜ ቅርጽን እንጠቀማለን። የዚህ አይነት የቋንቋ አጠቃቀም ስርአቶች በይዘትነት ተመርጠውና ተደራጅተው ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ መቅረብ እንዳለባቸው ምሁራኑ ያስገነዝባሉ (Batston፣1994፤ Leech፣1994) ።

የወገናዊነት ልዩነትም የቋንቋ አጠቃቀም ምርጫን እንደሚወስን Celce-Murcia and Hills(1988) ይገልጻሉ። በምሁራኑ ገለጻ መሰረት የምንደግፈውን ወይም የምንቀበለውን አመለካከት ለመግለጽ የአሁን ጊዜ ቅርጽን ስንጠቀም፤ የማንደግፈውን ለመግለጽ ግን ብዙ ጊዜ የሃላፊ ጊዜ ቅርጽን እንጠቀማለን። እነዚህ ምሁራን አያይዘው እንደሚሉት ከሆነ አጽንኦትም የቋንቋ አጠቃቃም ምርጫን ይወስናል። ለምሳሌ በጣም አስፈላጊ የሆነን ነገር/ጉዳይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስጥ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ማስገባት የተለመደ ነው። በመሆኑም ይህን መሰል የቋንቋ አጠቃቀም ስርአቶች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በስርአት ተመርጠውና ተደራጅተው በግብአትነት መቅረብ ይኖርባቸዋል ይላሉ ።

## 2.3 በሰዋስው ትምህርት ላይ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች

Mitchell(1994) እና Ur(1996) እንደሚያስረዱት በሰዋስው ትምህርት ላይ ከሚሰነዘሩ አስተያየቶች ውስጥ በእጅጉ አከራካሪ የሆነው ሰዋስውን እናስተምር ወይስ አናስተምር የሚለው ርዕሰ ጉዳይ ነው። ክርክሩም ረዘም ያለ ጊዜ አስቆጥሯል። የቋንቋ ትምህርት ሊቃውንትም ለሁለት ተከፍለው በአንደኛው ወገን ሰዋስው በትምህርትነት መሰጠት እንዳለበት ሲገልጹ በሌላኛው ወገን ያሉት ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስው በትምህርትነት መሰጠት እንደሌለበት ይገልጻሉ። ቆየት ያሉ የቋንቋ ማስተማር

ክንውኖችን ስንመለከት በ19ኛው ክፍለ ዘመን በአፍ መፍቻና በውጭ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የተጠናከረና ግልጽ የሆነ የሰዋስው ትምህርት ይሰጥ ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወይም ሂደት ውስጥ ለሰዋስው ይዘት ትኩረት ተነፍጎት ይስተዋላል።

Larsen-Freeman(1991) እና Tonkyn(1994) እንደሚገልጹት ከቀደምት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ የሆነው ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ የቋንቋው ትምህርት የመጨረሻ ግብ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ማስጠናት ነበር። በተጨማሪም የተማረ ሰው መለኪያ ተደርገው የሚታዩትን የንባብና የጽሁፍ ክሂሎችን በቋንቋው ሰዋስው አማካኝነት ለማስተማር ሙከራ ይደረግ ነበር። ሆኖም ከ1960ዎቹ ወዲህ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ሰዋስውን በትምህርትነት መሰጠቱ ጥያቄ ውስጥ መግባት ጀመረ። ጥያቄ ውስጥ መግባት ብቻም ሳይሆን ሰዋስው በትምህርት ቤቶች ውስጥ መሰጠቱን አስመልክቶ ሰፋት ያለው ተቃውሞ መነሳት ጀመረ። የተቃውሞው መነሻም በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ ሰዋስውን ከመስጠት ይልቅ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ሊያዳብሩ ለሚችሉ ተግባቦታዊ ክንውኖች ትኩረት ብንሰጥ ይሻላል የሚል ነበር።

Larsen-Freeman(1991)፣Tonkyn(1994)እና Mitchell(1994) እንደሚያስረዱት በ20ኛው ክፍለ ዘመን ለታየው በቋንቋ ክፍሎች ውስጥ የሰዋስው ቦታ ማጣት በክፍለ ዘመኑ የፈለቁ የተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አስተዋጽኦ አላቸው። ለዚህም ተግባቦታዊ ዘዴን፣ተፈጥሮአዊ ዘዴንና ሀሳብ ሰጪ ዘዴን መጥቀስ ይቻላል። ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በክፍል ውስጥ እውናዊ የተግባቦት አውዶችን በመፍጠር ታላሚውን ቋንቋ ማስተማር ላይ ያለመ ነው። በዚህ ዘዴ አተያይ ተግባቦት ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት አያሻውም ተብሎ ይታመናል። ተፈጥሮአዊ ዘዴ ደግሞ ተማሪዎች ከሰዋስዋዊ ህግጋት ይልቅ አሁን ካሉበት ደረጃ ከፍ ያሉ ተረድቶአዊ ግብአቶችን ቢያገኙ ይሻላል በማለት ፈጽሞ ለሰዋስው ትምህርት ትኩረት ሲሰጥ አይታይም።

ሆኖም ከላይ የቀረቡት አመለካከቶች የየራሳቸው ድክመት እንዳላቸው ማስተዋል አያዳግትም። የቋንቋ ትምህርት የመጨረሻ ግብ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአት ማስጠናት መሆን የለበትም። ምክንያቱም ቀደም ሲል በሰዋስው ትምህርት ትኩረት ላይ

ለማሳየት እንደተሞከረው በቋንቋ ትምህርት ክንውን ውስጥ ለተማሪዎች የተለያዩ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ስርአቶችን በማስተማር እንዴት ለተግባቦታዊ አገልግሎት እንደሚያውሏቸው ማሳየት ይኖርብናል፡፡ በሌላ በኩል በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ ተግባቦታዊ ክንውኖችን ብቻ እናቅርብ የሚለውም ሀሳብ ተገቢ አይደለም፡፡ Krashen(1987) ስለ ቋንቋ መማር ሲገልጹ ስለታላሚው ቋንቋ ሆን ብሎ ማወቅ፣ ሰዋስውን፣ ህግጋትና ስርአቱን ማጥናትና መነጋገር/መግባባት መቻልን የሚመለከት ነው ብለዋል፡፡ በተጨማሪም Tonkyn(1994) እንደሚያስረዱት በተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የሚሰጥ የቋንቋ ፈተና ብቁ ተናጋሪና ጸሃፊን ለመለየት ከተቀመጡ መስፈርቶች ውስጥ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት አንዱ ሆኖ ይገኛል፡፡

Harmer(1987) በበኩላቸው ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የቋንቋ ትምህርት ትኩረት ከሰዋስው ይልቅ ለተግባቦት እያደላ መምጣቱን ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም በአስረጅነት የሚጠቅሱት የቋንቋ መምህራንና ምሁራን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለቋንቋ አገልግሎትና ተግባቦታዊ ብቃት ቦታ እየሰጡ መምጣታቸውን ነው፡፡ ሀርመር አያይዘውም እንደሚያስረዱት አንዳንድ ሰዎች የአንድን ቋንቋ ሰዋስው ለተማሪዎች ማስተማር ቋንቋውን ለመጠቀም አያግዛቸውም ብለው ያስባሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ ግብዣ ማቅረብ፣ ይቅርታ መጠየቅ፣ማስተዋወቅ፣ ወዘተ የመሳሰሉ የቋንቋ አገልግሎቶችን ለማስተማር ከሰዋስው ይልቅ ፍችን ወይም አገልግሎትን ብናስተምር ይሻላል ብለው ያስባሉ፡፡ ሆኖም ከዚህ አመለካከት ፊት ለፊት ትልቅ እክል ተጋርጦ እናገኛለን፡፡ ይኸውም በቋንቋ አገልግሎት ውስጥ የምናገኘው ማንኛውም አረፍተ ነገር ከተለያዩ ሰዋስዋዊ ቅንጣቶች የተገነባ መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ‹‹እኔ አበበ እባላለሁ፡፡›› በማለት እራሳችንን ለማስተዋወቅ በምንሞክርበት ወቅት የምንገለገልበት ተራ አረፍተ ነገር እንኳ ተውላጠ ስም፣ የተጸውኦ ስምና ማሰሪያ አንቀጽ/ግስ አካቶ ይዟል፡፡

እንዲሁም Ur(1988) እንደሚያስረዱት ከ1960ዎቹ ወዲህ ሰዋስውን ከማስተማርና ከማለማመድ ይልቅ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ለሚኖራቸው ተግባቦታዊ ብቃት ትኩረት ብንሰጥና ሰዋስዋዊ ህግጋትንም ከተለያዩ ተግባቦታዊ ክንውኖች ውስጥ እንዲገነዘቡ ብናደርግ ይሻላል የሚሉ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማዳበር ብናልም እንኳ ይህንን ከግብ ለማድረስ

የሚደረጉ ልምምዶችና የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች የግድ ተግባቦታዊ ብቻ መሆን የለባቸውም። ምክንያቱም ተግባቦታዊ ብቃት በክፍል ውስጥ በሚደረጉ ተግባቦታዊ ክንውኖች ብቻ ላይመጣ ይችላልና ነው። ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የታላሚው ቋንቋ ሰዋስውና የተለያዩ ተግባቦታዊ ክንውኖች ተቀናጅተው ሊቀርቡ ይገባል።

በአጠቃላይ በሰዋስው ትምህርት ላይ የተለያዩ ምሁራን የሰነዘሯቸውን አስተያየቶች ስንመለከት ሶስት ወገኖችን እናስተውላለን። የመጀመሪያዎቹ ወገኖች የቋንቋ ትምህርት አላማም ሆነ ግብ የተማሪዎችን ሰዋስዋዊ ብቃት ማበልጸግ ስለሆነ ሰዋስው በትምህርትነት መሰጠት አለበት የሚሉ ናቸው። ሁለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ ይህንን ሀሳብ በመቃረን ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ መቅረብ እንደሌለበት ይገልጻሉ። ከሰዋስው ይልቅ ተግባቦታዊ ክንውኖች በትምህርት ይዘትነት መቅረብ አለባቸው በማለት አጥብቀው ይከራከራሉ። ሶስተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ የሁለቱን ተቃራኒ ወገኖች ሀሳብ በማስታረቅ የቀረቡ ናቸው። እንደነዚህ ወገኖች እምነት በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ ሰዋስዋዊ ይዘቶችና ተግባቦታዊ ክንውኖች ተቀናጅተው ሊቀርቡ ይገባል።

በሶስተኛ ደረጃ የቀረቡት ወገኖች እንደሚያስረዱት በቋንቋ ክፍሎች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ማቅረብና አገልግሎታቸውንም ማለማመድ ይኖርብናል። ይህ ደግሞ ተቀባይነት ያለው አተያይ ይመስላል። ምክንያቱም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የተሟላ ችሎታ እንዲኖራቸው የምንፈልግ ከሆነ ሰዋስዋዊ እውቀት ወይም ግብአት ሊያገኙ ይገባል። በማስከተልም ሰዋስዋዊ እውቀታቸውን እንዴት ባለመልኩ ለተግባቦት ሊያውሉት እንደሚችሉ እናሳያቸዋለን። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አላማችን የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማዳበር ነውና ተግባቦታዊ ክንውኖችን ብቻ እንምረጥ ብንል በአንድ እጅ ለማጨብጨብ እየሞከርን መሆኑን ልብ ልንል ያሻል። በተጨማሪም ተግባቦታዊ ችሎታን ያዳብራሉ እያልን የምናቀርባቸው እያንዳንዳቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጾች መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም።

እንዲሁም Tonkyn (1994) እና Mitchell (1994) እንደሚያስረዱት ከ1990ዎቹ ወዲህ መደበኛ የሰዋስው ትምህርት በትምህርት ቤቶች ውስጥ መሰጠቱ በጥርጣሬና በጥላቻ አይን መታየቱ እየቀነሰ የመጣ ይመስላል፡፡ ሰዋስውን በአፍ መፍቻ፣በሁለተኛና በውጪ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ ማስተማሩ የራሱ የሆኑ ጠቀሜታዎችና አዎንታዊ ሚናዎች እንዳሉት ስለታመነበት ትኩረት እያገኘ መሆኑን እነዚሁ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

## 2.4 በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት

ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ መሰጠቱ አዎንታዊ ሚናዎች እንዳሉትና አስፈላጊም እንደሆነ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ ይህ ከሆነ ቀጣዩ ተግባር ተገቢ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን መምረጥ ይሆናል፡፡ ተገቢ ይዘቶችን መምረጥ ይቻል ዘንድም የቋንቋውን ትምህርት አላማ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ዳራ፣ ደረጃ፣ ወዘተ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ የተመረጡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችም መርሃ ትምህርትን መሠረት አድርገው በሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው ይቀርባሉ፡፡በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥም ይዘቶቹ በገለጻ፣ በምሳሌና በመልመጃ መልክ ሊገኙ ይችላሉ (Harmer፣1987፤Ur፣1988፤Cunningsworth፣1995)፡፡

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሲቀርቡም በዘፈቀደ ሳይሆን ሊከተሏቸው የሚገቡ የአቀራረብና የአደረጃጀት መርሆች አሉ፡፡ በእርግጥ እነዚህ መርሆች ለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ ተብለው የተነደፉ አይደሉም፡፡ መርሆቹ ለሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችም ሆነ ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አኳያ ለማየት ተሞክሯል፡፡

### 2.4.1 በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

የትምህርት ይዘቶችን የአቀራረብ መርሆች አስመልክቶ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል በዚህ ጥናት ውስጥ በዋናነት ግልጽነት፣ ትክክለኛነት፣ ተገቢነትና ተመጣጣኝነት/ሚዛናዊነት

የሚሉት ተተኳሪ ሆነው ተወስደዋል፡፡ በማስከተልም እነዚህን የአቀራረብ መርሆች ከሰዋስው ትምህርት ጋር በማዛመድ ተራ በተራ ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡

### 2.4.1.1 ግልጽነት

ከአንድ የትምህርት ይዘት ጥሩ አቀራረብ መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ግልጽነት ነው፡፡ አንድ የትምህርት ይዘት ጥሩ አቀራረብ አለው የሚባለው ግልጽ ሆኖ ሲቀርብ ነው ማለት ነው፡፡ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አንጻርም ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት በመረዳት ረገድ ምንም እክል ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ ሊያጋጥማቸው አይገባም፤ ወይም የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከአቀራረብ አንጻር ለመረዳት አስቸጋሪ መሆን የለበትም፡፡ ይህንንም ማድረግ ይቻል ዘንድ የቀረቡ ገለጻዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትዕዛዞችና መልመጃዎች ግልጽና የማያጠራጥሩ እንዲሆኑ ይመከራል፡፡ ይህም ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ ተካተው የቀረቡላቸውን የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎችንና ምሳሌዎችን ለመረዳት እንዲሁም መልመጃዎችን ለመስራት በሚሞክሩበት ወቅት መምህራቸው ወይም የሚረዳቸው ሰው ባጠገባቸው ባይኖር እንኳ ቢያንስ ከግልጽነት አንጻር የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያቃልልላቸው ይችላል(Harmer፣1987)፡፡

Swan(1994) በበኩላቸው ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ግልጽ መሆን እንዳለባቸው አበክረው ይገልጻሉ፡፡ የምናቀርበው ይዘት ግልጽነት ይኖረው ዘንድ አቀራረባችን ተገቢውን ቅደም ተከተል የጠበቀ፣ ምሳሌዎችን ያካተተ፣ ለዋና ዋና ነጥቦች አጽንኦት የሰጠ፣ አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮችን ያስወገደ መሆን አለበት፡፡ የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ስለሚያቀርቧቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቂ ግንዛቤ አለመኖር አቀራረባቸው ግልጽነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ አዘጋጆች ስለሚያቀርቧቸው ይዘቶች በቂ ግንዛቤ ወይም እውቀት እንዲኖራቸውና ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉ መልኩ በገለጻ ወይም በምሳሌዎች በመታገዝ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

Sheldon (1988) እና Edge (1993) እንደሚያስረዱት በክፍል ስራነትም ይሁን በቤት ስራነት የሚሰጡ መልመጃዎች ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመልመጃዎች

ስር ተካተው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሊሰሩ የሚችሉበትን መንገድ የሚያሳይ ግልጽ ምሳሌ ለተማሪዎች መቅረብ አለበት። ይህም በተማሪዎች ላይ ግርታ እንዳይፈጠር ይረዳል።

### 2.4.1.2 ትክክለኛነት

Swan(1994) እንደሚያስረዱት ትክክለኛነት እውነተኛ የቋንቋውን ስነልሳናዊ ባህሪ ወይም የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበትን ይዘት ይመለከታል። ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ትክክልና እውነተኛ ሊሆኑ ይገባል። በእርግጥ የታላሚውን ቋንቋ አንዳንድ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ትክክለኛ ቅርጽ ማሳየቱ ከተማሪዎች እድሜና የትምህርት ደረጃ አንጻር ከባድና ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ይህም ሆኖ ግን በተቻለ መጠን ተማሪዎች የቋንቋውን ትክክለኛ ስነልሳናዊ ባህሪ እንዲያውቁ ያስፈልጋል።

Edge(1993) በበኩላቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ ሳይሆኑ በአጠቃላይ በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙ የትምህርት ይዘቶች ከሚሰጡት መረጃ አንጻር ትክክለኛ መሆን እንዳለባቸው ይገልጻሉ። ይህም ይዘቶቹ ለተማሪዎች ስህተት እንዳያስተምሩ ወይም የቋንቋውን ትክክለኛ ስነልሳናዊ ባህሪ የማያሳይ መረጃ እንዳይሰጡ ያስችላቸዋል።

ከገለጻዎቹ በመነሳት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለማቅረብ ስንሞክር በተለይ ትክክለኛና ከስህተት የጸዱ ግብአቶችን ለተማሪዎች ለማቅረብ ጥረት ማድረግ እንዳለብን ልብ ልንል ይገባል። ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ይዘትም የቋንቋውን እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ስነልሳናዊ ባህሪ የሚያሳይና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበት ወይም የሚቀበለው ነው። ይህም በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች በሚቀርብ ሰዋስዋዊ ይዘትና ከክፍል ውጪ የቋንቋው ተናጋሪዎች በሚገለገሉበት መካከል ልዩነት እንዳይፈጠር ያግዛል።

### 2.4.1.3 ተመጣጣኝነት

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ከቋንቋው ክሂል ዘርፎች(ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብ፣መጻፍ)፣ሰዋስውና ስነጽሁፍ ይዘቶች ውስጥ ተመጣጥነው መሆን አለበት። ይህም መሆኑ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚኖራቸውን ችሎታና እውቀት የተሟላ

ያደርገዋል፡፡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችም ከታላሚው ቋንቋ ልዩልዩ የሰዋስው ክፍሎች ውስጥ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የተውጣጡ እንዲሆኑ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ በዚህም መሠረት ይዘቶቹ ከቋንቋው የደምጽ ስርአት፣ የምዕላድና የቃል ክፍል፣ የአገባብና የፍች ስርአት ውስጥ የተውጣጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ይዘቶችም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በሰንጠረዥ፣ በገለጻ፣ በምሳሌና በመልመጃዎች በመደገፍ ይቀርባሉ፡፡ መልመጃዎችም በአዛምድ፣ ክፍት ቦታውን በመሙላት፣ የተጀመረውን በመጨረስ፣ የተዘበራረቁትን ቃላት/አረፍተ ነገሮች በማስተካከል፣ አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ፣ ወዘተ መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ (Harmer፣1987፤Tonkyn፣1994)፡፡

ከቀረበው ገለጻ በመነሳት የይዘት ብቻም ሳይሆን የአቀራረብ መመጣጠን ወይም ሚዛናዊነት መኖር አለበት ማለት ነው፡፡ ይህም ሊፈጠር የሚችለውን መሰላቸትና ፍትሃዊ ያልሆነ (ለተወሰኑ ይዘቶች ብቻ ትኩረት የሚሰጥ) የአቀራረብ ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግ ያስችላል፡፡ በእርግጥ በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ዘወትር የተመጣጠኑ ወይም ሁሉንም የሰዋስው ክፍሎች በእኩል ደረጃ የሚያቀርቡ እንዲሆኑ ለማድረግ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ አልፎ አልፎ ለአንዳንድ የሰዋስው ክፍሎች እንደየጠቃሚነታቸው እየታየ የበለጠ ትኩረት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በተቻለ መጠን ይዘቶቹ ሁሉንም የሰዋስው ክፍሎች የሚዳስሱ እንዲሆኑ ይመከራል፡፡

### 2.4.1.4 ተገቢነት

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች እድሜ፣ብስለት፣ የቋንቋ ችሎታ፣ የቀደመ እውቀት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ፣ ወዘተ አንጻር ተመጣጣኝ ወይም የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡ ይዘቶቹ ከተማሪዎች የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ አስቸጋሪ ወይም ከባድ ሆነው መዘጋጀት የለባቸውም (Sheldon፣1988፤Robinson፣1991)፡፡ ተገቢነት ያላቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ደረጃ፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር የተጣጣሙ በመሆናቸው ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸው ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በተማሪዎች ዘንድ ግርታና የመሰላቸት ሁኔታ እንዳይፈጠር ያግዛሉ፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሳት ሰዋስዋዊ

የትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች እድሜ፣ ችሎታ፣ የቀደመ እውቀት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር ተጣጥመው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

Harmer(1987) ተገቢነትን አስመልክተው የሚሰጡት ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አንጻር ነው፡፡ በዚህ መሰረት የአንድ ቋንቋ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የቋንቋ ቅርጾች ፍችና አጠቃቀም ለማስተማር የሚያስችሉ ወይም ተገቢ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ትምህርት አላማዎች ከግብ የሚያደርሱ መሆን እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ Swan(1994) በበኩላቸው ተገቢነትን የሚገልጹት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ዙሪያ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት ከመቻላቸው፣ ተማሪዎች ያለባቸውን ሰዋስዋዊ ችግር ከመፍታትና በአጠቃላይ ተማሪዎቹ ይዘቶቹን በዛ ደረጃ ሊማሯቸው አስፈላጊ ከመሆናቸው አንጻር ነው፡፡

በአጠቃላይ ተገቢነትን አስመልክተው የተሰጡ ገለዎችን ስንመለከት ሁለት አንድምታ እንዳላቸው ማስተዋል ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ገለጻ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተማሪዎች ደረጃ፣ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ ወዘተ ጋር መጣጣም እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው ገለጻ ደግሞ ይዘቶቹ የቋንቋውን ትምህርት አላማ ከግብ የሚያደርሱና ተማሪዎች ሊማሯቸው ወይም ሊያውቋቸው የሚገቡ መሆን እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ ይህም ተገቢነት በአጠቃላይ ከተማሪዎች ሁኔታ፣ ከትምህርቱ አላማና አስፈላጊነት አንጻር ሊታይ እንደሚችል ያመላክታል፡፡

### 2.4.2 በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

አደረጃጀት በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለባቸው፣ የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት፣ የትኛው መከተል እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ እንዲሁም ይዘቶቹ እንዴት ባለ መንገድ ተደጋግመውና ጥልቀት እየጨመሩ መቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ ከዚህም በመነሳት አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ፣ተጨባጭ ከሆነው ወደ ረቂቁ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

ወይም ተገላቢጦሻቸውን እንዲሁም ድግግሞሽንና ጥልቀትን ይመለከታል ማለት ይቻላል (Nunan፣1988፤Cunningsworth፣1995)።

በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት መሰረት እንደሚያደርገው የሰዋስው ማቅረቢያ ወይም ማስተማሪያ ስልተ ትወራ አይነት የተለያየ ነው። ውጤታዊ ስልተ ትወራን መሰረት የሚያደርጉ ወገኖች የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደራጅተው ያቀርባሉ። ሂደታዊ ስልተ ትወራን የሚከተሉ ወገኖች ደግሞ የተማሪውን ፍላጎትና ዳራዊ እውቀት መሰረት አድርገው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደራጅተው ሲያቀርቡ፤ ውጤት-ወሂደት የሰዋስው ማስተማር ስልተ ትወራን የሚከተሉ ወገኖች ግን ሁለቱንም የአደረጃጀትስልቶችይከተላሉ(Cunningsworth፣1995፤Batston፣1994፤Leech፣1994)። Tyler(1949) እና Taba(1962) እንደሚያስረዱት የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች ቅንጅታዊ ውጤት ማስገኘት ይችሉ ዘንድ እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ሊደራጁ ይገባል። አደረጃጀታቸውም ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነት የጠበቀ እንዲሆን ያስፈልጋል። ተዋረዳዊ ግንኙነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች የሚኖራቸውን ግንኙነት ያሳያል። ለምሳሌ በአምስተኛ ክፍል የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በስድስተኛ ክፍል ከቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት የይዘቶቹን ተዋረዳዊ ግንኙነት ያሳያል። ይህም ስድስተኛ ክፍል የቀረቡ ይዘቶች በአምስተኛ ክፍል የቀረቡትን መሰረት አድርገው የሚገነቡ እንደሆነ ያሳያል። በሌላ በኩል የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች ከአምስተኛ ክፍል የእንግሊዝኛ፣ የስነዜጋ፣ ወዘተ ትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት የይዘቶቹን ወይም የትምህርት ልምዶቹን ጎናዊ ግንኙነት ያሳያል። ይህም በደረጃው የሚቀርቡ የትምህርት አይነቶች እርስ በርስ እንዲደጋገፉ ያስችላቸዋል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሚሆነው የአደረጃጀት ስልት የይዘቶችን ተዋረዳዊ ግንኙነት የሚያሳየው ነው። ጎናዊ ግንኙነት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ትስስር የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ትኩረት ውጪ ነው። በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ ወደሚሆነው ተዋረዳዊ አደረጃጀት ስንመለስ በስሩ በዋናነት ተከታታይነት፣

ቀጣይነት/ተለጣጣቂነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣የሚሉ የአደረጃጀት ስልቶችን እናገኛለን። በማስከተል እነዚህን በቅደም ተከተል እናያለን።

### 2.4.2.1 ተከታታይነት

ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች በዛው የክፍል ደረጃ ተደጋግመው መቅረባቸውን ይመለከታል። ለምሳሌ በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበ ይዘት በዛው መጽሐፍ ሌሎች ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግሞ መቅረብ እንዳለበት የሚጠቁም ነው። ይዘቱ ተደጋግሞ ሲቀርብ ግን ስፋቱና ጥልቀቱ እየጨመረ መሆን አለበት። በሌላ አገላለጽ በምዕራፍ አንድ የቀረበው በቀጣይ ምዕራፍ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ የቅለት ደረጃ ሊኖረው አይገባም (Tyler፣1949፤Taba፣1962)።

ተከታታይነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በምን አይነት ቅደም ተከተል ሊደራጁና ከተማሪዎች እድገት አንጻር ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ሊቀርቡ እንደሚገባ የሚያሳይ ነው። በተከታታይነት ውስጥ ድግግሞሽ ጠቀሜታ አለው። አንድ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ይዘት አንድ ጊዜ ብቻ መቅረቡ በቂ አይደለም። ይልቁንም ተማሪዎች ይዘቱን በተለያዩ ምዕራፎችና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊያገኙት ይገባል። ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቱን በሚገባ እንዲረዱት፣ እንዲካኑትና በተገቢ ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያውሉት ያስችላቸዋል። ድግግሞሹ በተለይም ለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠቀሜታ አለው። ምክንያቱም ሰዋስዋዊ ቅርጾች በአንድ ጊዜ ትምህርት ላይያዙ ይችላሉና (Larsen-Freeman፣1991፤Cunningsworth፣1995)።

ከገለጻዎቹ መረዳት እንደሚቻለው በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል ደረጃ ተደጋግመው ሊቀርቡ ይገባል። መደጋገም ብቻም ሳይሆን ኋላ የቀረቡት ቀድመዋቸው ከቀረቡት በይዘት ጠለቅ፣ በሰልና ጠጠር ማለት ይኖርባቸዋል። ይህም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በስፋትና በጥልቀት ለማስተማር ይረዳል። ተማሪዎችም የሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ቅርጽ፣ ፍችና አጠቃቀማቸውን በደንብ እንዲያውቁና በአገልግሎት ላይ እንዲያውሏቸው ያስችላል። እንዲሁም ተማሪዎች

ለውጥና መሻሻል የሌለው ተደጋጋሚ ስራ እንዳይሰሩ፣ እንዳይሰላቹና ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ያስችላል።

### 2.4.2.2 ቀጣይነት

ቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር ይገናኛል። ሆኖም ቀጣይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኝ አይደለም። ቀጣይነት አንድ የትምህርት ይዘት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተደጋግሞ መምጣት እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ድግግሞሽ ብቻም ሳይሆን ቀደም ሲል ለማየት እንደተሞከረው ይዘቶቹ እየጠለቁና እየሰፉ መሄድ አለባቸው (Tyler፣1949፤Taba፣1962)። ለምሳሌ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተውላጠ ስሞችን ልናስተምር አቀድን እንበል፤ በዚህ መሠረት በቅድሚያ ለአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ነጻ ተውላጠ ስሞችን በማቅረብ ከመደብ፣ ከጾታና ከቁጥር አንጻር በተደጋጋሚ እናለማምዳቸዋለን። በማስከተልም በስድስተኛ፣ በሰባተኛና በስምንተኛ ክፍሎች በግስ ላይ እየተቀጠሉ ባለቤትን፣ተሳቢን የሚያመለክቱ አጸፋ ተውላጠ ስሞችን በተከታታይ ልናስተምራቸው እንችላለን።

Nunan(1988) በበኩላቸው ቀጣይነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ፣ሳይቆራረጡ እርስ በእርስ ተሳስረው መደራጀት እንዳለባቸው የሚያሳይ እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህ ቀጣይነታቸው ወይም ተለጣጣቂነታቸው ግን ከክፍል ወደ ክፍል እያደገና ጥልቀት እየጨመረ የሚሄድ ነው።

በአጠቃላይ ስንመለከተው ቀጣይነት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከክፍል ወደ ክፍል ተደጋግመው መቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል። ይህም ይዘቶቹ ሳይቆራረጡ ቀጣይነት ባለው መልኩና እርስ በእርሳቸው ተሳስረው ወይም ቀድመው የቀረቡት ቀጥሎ ለሚመጡት መሰረት ሆነው እንዲደራጁ ያስችላል። ይህ መሆኑ ደግሞ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ቅርጾቹን በተደጋጋሚ እንዲለማመዷቸውና በደንብ እንዲካኗቸው እድል ይሰጣል። ሌላው ሰዋስዋዊ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶቹ ከክፍል ወደ ክፍል ጥልቀትና ስፋት እየጨመሩ መደራጀት እንዳለባቸው ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል። ይህም ለምሳሌ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በሰባተኛ ክፍል ውስጥ ካሉት ጠለቅና ጠጠር ብለው መቅረብ እንዳለባቸው

ያሳያል። ይህ ካልሆነ ግን አላስፈላጊ ድግግሞሽ እንዲፈጠር ከማድረጋቸውም በላይ አሰልቺ መሆናቸው አይቀሬ ነው።

## 2.4.2.3 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ አይቀርብም። በቅድሚያ ህግጋቱን ሊያሳዩ የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ። ተማሪዎችም የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በደንብ በማጤን የቋንቋው ህግጋት ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገምታሉ። ከዛም ግምታቸውን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ምላሾችን ከመምህራቸው ያገኛሉ። ይህ የአደረጃጀት ስልት የህጻናትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለማመድ የተከተለና ተፈጥሮአዊ እንደሆነ መምህራን ይናገራሉ (Cunningsworth፣1995)።

Harmer(1987) እና Larsen-Freeman(1991) በበኩላቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ህግጋት እንዲያወጡ የሚያበረታታ ነው። በዚህ ስልት አንድ አዲስ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ሲቀርብ ምንም አይነት ገለጻ አይደረግም። ዋነኛ ትኩረቱም ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ምሳሌዎች በመነሳት ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያስችሏቸውን ሰዋስዋዊ መረጃዎች እንዲለዩ ማስቻል ነው። ሆኖም ከተማሪዎች እድሜና የትምህርት ደረጃ፣ለትምህርት ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ረቂቅነት፣ወዘተ አንጻር ይህንን የአደረጃጀት ስልት መጠቀሙ አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለ መምህራን ይናገራሉ። ስለዚህም በሌላ የአደረጃጀት ስልት ሊታገዝ ይገባል። በማስከተልም ይህንኑ እናያለን።

## 2.4.2.4 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል። ከገለጻው በመነሳትም ህግጋቱን በተግባር ላይ ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ። ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል። ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም። ምክንያቱም ተማሪዎች በገለጻ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ

አዳጋች ሊሆንበቻው ይችላል፡፡ ስለዚህም ገለጻው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል (Cunningsworth፣1995)፡፡

Harmer(1987) እና Larsen-Freeman(1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልትን አስመልክተው ያቀረቡት ገለጻ ከዚህ በላይ ከቀረበው ገለጻ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ በእነሱ አገላለጽ በዚህ የአደረጃጀት ስልት ለተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል፡፡ ገለጻውንም መሠረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር ወደመለማመድ ያመራሉ፡፡ Stevick(1986) እንደሚያስረዱት ገለጻ ተማሪዎች ለሚያነሷቸው ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትና ተማሪዎችን ለማገዝ አንዱ መንገድ ነው፡፡ አላማውም ተማሪዎች ቋንቋውን ለተግባቦት በሚጠቀሙበት ወቅት ተገቢና ትክክለኛ ቅርጾችን በፍጥነትና በትክክል መምረጥ እንዲችሉ ለመርዳት ነው፡፡ ሆኖም ብቻውን በቂ ባለመሆኑ በደጋፊ ምሳሌዎች ሊታገዝ ይገባል፡፡

ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይም ሆነ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልቶችን በማወዳደር ይሄኛው ወይም ያኛው ይበልጣል፣ ይሄኛው ወይም ያኛው ትክክል ነው ማለት አይቻልም፡፡ ተማሪዎች እንደየባህሪያቸው በሁለቱ ስልቶች ሊማሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ሁለቱንም በማቀናጀት ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡

## 2.5 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ጌታሁን አማረ (1993) ‹‹በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለአምስተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ›› በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ይገኛል፡፡ ይህ ጥናት ትኩረቱ ከሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት አንጻር መገምገም ሲሆን ለደረጃው የተዘጋጁትንም መርሃ ትምህርትና የፍሰት ሰንጠረዥ መሠረት አድርጓል፡፡

ሁሉባንተ አደመ (1994) ‹‹በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተዘጋጁ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አደረጃጀት ግምገማ›› በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪያቸው ማሟያ ጥናት አቅርበዋል፡፡

የጌታሁንና የሁሉባንተ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በተመረጡት የክፍል ደረጃዎችና ይዘውት ከተነሱት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነሱ ትኩረት ባደረጉበት ክልል ውስጥ አማርኛ በስፋት እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጥበት ክልል በመሆኑና በዚህ ጥናት ተተኳሪ ክልል ውስጥ ግን አማርኛ በስፋት የሚሰጠው እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመሆኑ፤ እንዲሁም የዚህ ጥናት አቢይ ትኩረት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ በመሆኑ ይህን ጥናት በተለይም በክልል ደረጃ ሲታይ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ተስፋዬ በቀለ (1993) ‹‹በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለስምንተኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ትኩረት መጽሀፉ ለቋንቋው ቅርጻዊ ስርአትና ፍች ትኩረት መስጠት ወይም አለመስጠቱን፣እንዲሁም የሰዋስዋዊ መልመጃዎችን አደረጃጀት መገምገም ነው፡፡ ይህ ጥናት ይዞት በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰል እንጂ ትኩረት በተሰጠው ክልልም ሆነ በአላማ ይህ ጥናት ከተስፋዬ ጥናት የተለየ ነው፡፡

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) ‹‹በአዲስ አበባ ከተማና አማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፋቸውን አቅርበዋል፡፡ በዚህ ጥናታቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚጠቀሙባቸው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስውን ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በማነጻጸር ተመሳስሎና ልዩነታቸውን አሳይተዋል፡፡ ጥናቱ ይዞት በተነሳው ርዕሰ ጉዳይና የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት ፍተሻን በተመለከተ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ በትኩረት ክልሎቹና አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት በሚሰጥበት ደረጃው፣ በእርከኑ ያሉትን ሁሉንም ክፍሎች በማካተትና በአላማ ይህ ጥናት ከሐዋዝ ጥናት ይለያል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ጉዳያቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ወይም ንጽጽራዊ ጥናት ይሁኑ እንጂ ተተኳሪ በሆኑት ክልል፣ አልፎ አልፎ በክፍል ደረጃ/እርከን እና አላማ አንጻር ሲታዩ ከዚህ ጥናት ጋር አይመሳሰሉም ወይም ይለያያሉ። ይህ ጥናት በዋነኝነት ትኩረት ያደረገው በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ላይ ነው። በመሆኑም ይህን ጥናት ከላይ ከቀረቡት የተለየ ያደርገዋል።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የአጠናን ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ተዘጋጅተው በስራ ላይ ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ናቸው፡፡ እንዲሁም ከመጻህፍቱ አዘጋጆች በቃል መጠይቅ፣ በመጻህፍቱ ከሚያስተምሩ የየደረጃዎቹ መምህራንና በመጻህፍቱ ከሚገለገሉ የየደረጃዎቹ ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የሚገኙ ምላሾችና በየደረጃው መሰረት ያደረጓቸው መርሐ ትምህርቶች የጥናቱ ደጋፊ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡

### 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

#### 3.2.1 የሰነድ ግምገማ

በዚህ ጥናት ውስጥ አቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው የሰነድ ግምገማ ነው፡፡ የሚገመገሙትም ሰነዶች በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ተዘጋጅተው በስራ ላይ ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ናቸው፡፡ ግምገማው የሚካሄደው ክለሳ ድርሳን ውስጥ በቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ላይ ተመርኩዞ ሲሆን፤ አጥኚው እነዚህን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት ትኩረት ሰጥቶ ለመገምገም ተሞክሯል፡፡

#### 3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት አጥኚው በክለሳ ድርሳን ውስጥ በቀረቡት ንድፈ ሀሳቦች መሰረትነት የመማሪያ መጻህፍቱን ለመገምገም ከሞከረ በኋላ በመማሪያ መጻህፍቱ የሚገለገሉባቸውን መምህራንና ተማሪዎች አስተያየት በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት በመውሰድ ትንተናውን ለማጠናከር ጥረት ያደርጋል፡፡ መምህራንና ተማሪዎችም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ስለ ሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ያላቸውን አስተያየት ማወቅ ይቻል ዘንድ የጽሁፍ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህም

መሰረት ለመምህራን አስራ ሦስት ዝግና አንድ ክፍት በድምሩ አስራ አራት ጥያቄ የቀረበላቸው ሲሆን፤ ለተማሪዎች ደግሞ አስራ አንድ ዝግና አንድ ክፍት በድምሩ አስራ ሁለት ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ለሁለቱም አካላት የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች ጭብጥ የሚያጠነጥነው በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ ነው፡፡

የጽሁፍ መጠይቆቹ በክለሳ ድርሳን የቀረቡ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ በአጥኚው ከተዘጋጁ በኋላ በአቻ አማርኛን የማስተማር ስነዘዴ ድህረ ምረቃ ተማሪዎች እንዲሁም በአማካሪ መምህር አማካይነት ተገምግመው በተገኙት ምጋቤ ምላሾች መሠረት ተሻሽለዋል፡፡ ከግምገማው በኋላም በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን የበና ፀማይ ወረዳ ዋና ከተማ በሆነችው ቀይ አፈር ከተማ ውስጥ በሚገኝና በኢላማ ናሙና በተመረጠ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀይ አፈር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት) ውስጥ በተደረገ ሙከራ የጽሁፍ መጠይቆቹን ለመፈተሽ ተሞክሮ የየደረጃዎቹ መምህራንና ተማሪዎች በቀላሉ ሊሞሏቸው መቻላቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 3.2.3 ቃለ መጠይቅ

አጥኚው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ንድፈ ሀሳቦች ላይ ተመስርቶ መጻህፍቱን ከገመገመ በኋላ ከየደረጃዎቹ መጻህፍት አዘጋጆች በቃለ መጠይቅ አማካይነት ምላሻቸውን በመውሰድ የግምገማ ውጤቱን ለማጠናከር ይጠቀምበታል፡፡ የመጻህፍቱ አዘጋጆችም በመጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት በተመለከተ ያላቸውን አስተያየት ማወቅ ይቻል ዘንድ ለመነሻ የሚሆኑ አስራ አንድ ጥያቄዎች በአጥኚው ተዘጋጅተው በአማካሪው ከተገመገሙ በኋላ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተሻሽለው ለመጻህፍቱ አዘጋጆች በቃለ መጠይቅነት ቀርበዋል፡፡

## 3.3 የናሙና አወሳሰድ

### 3.3.1 የመማሪያ መጻህፍቱ ናሙና አወሳሰድ

በእርከኑ ያሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ብዛት አራት ነው፡፡ በመሆኑም በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ አራቱም ተወስደው ይገመገማሉ፡፡ አራቱንም በተከታታይ

መውሰድ ያስፈለገበት ምክንያት በሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀታቸው ያላቸውን ቀጣይነት በአግባቡ ለመገምገም ስለሚያስችል ነው፡፡

### 3.3.2 የዞንና የከተማ ናሙና አወሳሰድ

የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በስሩ አስራ አራት ዞኖችን፣ አራት ልዩ ወረዳዎችንና አንድ የከተማ አስተዳደር አካቶ ይዟል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አጥኚው የደቡብ ኦሞ ዞንን በአመቺ የናሙና ስልት መርጧል፡፡ ይህ ዞን ሊመረጥ የቻለበት አቢይ ምክንያት አጥኚው ከሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ይበልጥ በቅርበት የሚያውቀው በመሆኑና በየደረጃው ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነውን ትብብር በቀላሉ የሚያደርጉለት አካላት በመኖራቸው ነው፡፡

የደቡብ ኦሞ ዞን በስሩ ስምንት ወረዳዎችንና አንድ የከተማ አስተዳደር የያዘ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አጥኚው የዞኑ ዋና ከተማ የሆነችውን ጂንካ ከተማ አስተዳደር በአመቺ ናሙና ስልት ሊመርጥ ችሏል፡፡ ይህች ከተማ የተመረጠችበትም አቢይ ምክንያት ከሌሎች የዞኑ አካባቢዎች ይልቅ በዚህች ከተማ ውስጥ በርከት ያሉ ነባር መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስለሚገኙባት ነው፡፡

### 3.3.3. የትምህርት ቤቶች ናሙና አወሳሰድ

በጂንካ ከተማ አስተዳደር ውስጥ አራት የመንግስትና ሁለት የግል በድምሩ ስድስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከአራቱ የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ እና ሁለቱ የግል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃቸው እስከ አራተኛ ክፍል ብቻ የተወሰነ ስለሆነ ከዚህ ጥናት ትኩረት ውጪ ሆነዋል፡፡ ቀሪዎቹ ሦስት የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚስተምሩ ሆነው በመገኘታቸው የዚህ ጥናት አካል ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ካላቸው የተማሪ ብዛት አንጻር ሦስቱንም ትምህርት ቤቶች ማካተቱ አጥኚው ጀማሪ እንደመሆኑ መጠን ጥናቱን አስቸጋሪና ውስብስብ እንዳያደርገው በማሰብ በተራ የዕጣ ናሙና ስልት ሁለቱ ትምህርት ቤቶች ብቻ ተወስደዋል፡፡ እነዚህም ትምህርት ቤቶች፡- ቁራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ኀርጎቻ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

## 3.3.4 የመምህራን ናሙና አወሳሰድ

በጂንካ ከተማ አስተዳደር ለዚህ ጥናት በተመረጡ ሁለት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ  ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን ብዛት ሁለት ወንዶችና አራት ሴቶች በድምሩ ስድስት ብቻ በመሆኑ ጠቅላይ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን በመጠቀምና ሁሉንም በመውሰድ የዚህ ጥናት አካል ማድረግ ተችሏል፡፡ መጠይቅ የሞሉ የየትምህርት ቤቶቹ መምህራን አጠቃላይ መረጃ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ሰፍሯል፡፡

ሠንጠረዥ አንድ፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የመምህራን ብዛት | ጾታ | የትምህርት ደረጃ | የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቁራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1<br>1<br>1 | ሴ<br>ወ<br>ወ | 12+2<br>››<br>›› | 5ኛ<br>6ኛ<br>7ኛ እና 8ኛ | 26 አመት<br>22 አመት<br>18 አመት |
| 2 | ጎርጎቻ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1<br>1<br>1 | ሴ<br>ሴ<br>ሴ | 12+2<br>››<br>›› | 5ኛ<br>6ኛ<br>7ኛ እና 8ኛ | 17 አመት<br>17 አመት<br>15 አመት |
| | ጠቅላላ ድምር | 6 | - | - | - | - |

## 3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በጂንካ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙት አራት የመንግስትና ሁለት የግል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሦስቱ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ብቻ ለዚህ ጥናት አመቺ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች ብዛት ጥናቱን አስቸጋሪና ውስብስብ እንዳያደርገው በመስጋት ከሦስቱ ትምህርት ቤቶች ሁለቱን ብቻ በተራ የዕጣ ናሙና ለመውሰድ ተችሏል፡፡ አሁንም ቢሆን የሁለቱንም ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአጠቃላይ ወስዶ ማጥናት ከአቅም በላይ ስለሚሆን ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሲባል ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሰላሳ ፐርሰንት (30%) ተማሪዎች ከየክፍል ደረጃው

በተራ የዕጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ ቀጥሎ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 3.3.5.1 ቂራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ 144 የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች በሶስት የመማሪያ ክፍሎች/ሴክሽን፤ 138 የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሶስት የመማሪያ ክፍሎች/ሴክሽን፤ 106 የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍሎች/ሴክሽን እና 98 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍሎች/ሴክሽን የሚማሩ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል 486 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለጥናቱ አመቺነት ሲባል ከየክፍል ደረጃው የተወሰዱት ተማሪዎች ሰላሳ ፐርሰንት (30%) ብቻ ናቸው፡፡ ቀጥሎ መጠይቅ የሞሉ ተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር ጠቅለል ባለ መልኩ በሰንጠረዥ እናያለን፡፡

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የቂራ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር፡፡

| የክፍል ደረጃ | | | | | | | | | | | | አጠቃላይ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5ኛ | | | 6ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | | | |
| ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 25 | 18 | 43 | 27 | 14 | 41 | 20 | 12 | 32 | 18 | 11 | 29 | 90 | 55 | 145 |

### 3.3.5.2 ጎርጎቻ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ 135 የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች በሶስት የመማሪያ ክፍሎች፤ 122 የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሦስት የመማሪያ ክፍሎች፤ 102 የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍሎች እና 89 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍሎች የሚማሩ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ድምር 448 ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለጥናቱ አመቺነት ሲባል ከየክፍል ደረጃው በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች ሰላሳ ፐርሰንት (30%) ብቻ ናቸው፡፡ ቀጥሎ መጠይቅ የሞሉ ተማሪዎችን

የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር ጠቅለል ባለ መልኩ በሰንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ሰንጠረዥ ሦስት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የጎርጎቻ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር

| የክፍል ደረጃ | | | | | | | | | | | | አጠቃላይ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5ኛ | | | 6ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | | | |
| ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 24 | 17 | 41 | 21 | 16 | 37 | 18 | 13 | 31 | 19 | 8 | 27 | 82 | 54 | 136 |

ሠንጠረዥ አራት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና የጾታ ስብጥር

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | 5ኛ ክፍል | | | 6ኛ ክፍል | | | 7ኛ ክፍል | | | 8ኛ ክፍል | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ቁራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 25 | 18 | 43 | 27 | 14 | 41 | 20 | 12 | 32 | 18 | 11 | 29 |
| 2 | ጎርጎቻ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 24 | 17 | 41 | 21 | 16 | 37 | 18 | 13 | 31 | 19 | 8 | 27 |
| | ጠቅላላ ድምር | 49 | 35 | 84 | 48 | 30 | 78 | 38 | 25 | 63 | 37 | 19 | 56 |

ሠንጠረዥ አምስት፡- የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛትና የጾታ ስብጥር

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | ወ | ሴ | ድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቁራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 90 | 55 | 145 |
| 2 | ጎርጎቻ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 82 | 54 | 136 |
| | ጠቅላላ ድምር | 172 | 109 | 281 |

### 3.3.6 የመጻህፍቱ አዘጋጆች ናሙና አወሳሰድ

በጥናቱ ተተኳሪ እርከን ያሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ብዛት አራት ነው፡፡ ከ7ኛ ክፍሉ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በስተቀር ሌሎቹን የመማሪያ መጻህፍት የተለያዩ ሁለት ሁለት ባለሙያዎች አዘጋጅተዋቸዋል፡፡ በ7ኛ ክፍሉ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለ መጽሐፉ አዘጋጆች ማንነት ምንም የተሰጠ መረጃ የለም፡፡ አጥኚው በክልሉ ትምህርት ቢሮ ስርአተ ትምህርት ዝግጅትና ጥናትና ምርምር ክፍል ውስጥ በነበረው የቆይታ ጊዜ ስለመጽሀፉ አዘጋጆች ማንነት ጠይቆ ያገኘው ምላሽም በሃላፊዎች መለዋወጥና በመረጃ አያያዝ ችግር ምክንያት የመጽሐፉ አዘጋጆች ማንነት ሊታወቅ አለመቻሉን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የሶስቱ መጻህፍት (የ5ኛ፣ የ6ኛ እና የ8ኛ) አዘጋጆች ስም መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ቢኖርም አድራሻቸውን ማወቅና ማግኘት የተቻለው የሁለት አዘጋጆችን ብቻ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ሲሆን አድራሻው ሐዋሳ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ መምህርና የሐዋሳ ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ ሌላዋ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ስትሆን የይርጋለም ከተማ ነዋሪና የይርጋለም ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት መምህርት ናት፡፡ አጥኚው በአድራሻቸው መሰረት ሁለቱንም በማግኘት በቃለ መጠይቁ ለማሳተፍ የቻለ ሲሆን፤ የ5ኛ ክፍሉን ሁለቱን፤ የ6ኛ ክፍሉን አንዱን እና የ8ኛ ክፍሉን አንዱን አዘጋጆች በተለያዩ ምክንያቶች (በህመም፣ በጡረታ፣ ሀገር ለቆ በመውጣት፣ ወዘተ) ማግኘት ስላልተቻለ በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አልቻለም፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት በዋነኝነት ገላጭ የምርምር ዘዴን ይጠቀማል፡፡ ይህንን የምርምር ዘዴ በመጠቀምም በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብና ከአደረጃጀት ንድፈ ሀሳቦች አንጻር እየታዩ ይተነተናሉ፡፡ በየደረጃው ከተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶች ጋር ያላቸው ተዛማጅነትም በዚሁ ስልት ይታያል፡፡ እንዲሁም መጠናዊ (አሃዛዊ) የምርምር ዘዴን በመጠቀም ከመምህራንና ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾችን በመቶኛ (በፐርሰንት) በማስላት ገለጻውን ለማጠናከር ይሞከራል፡፡

ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች አምስት አምስት አማራጮች አሏቸው። እነሱም፡- 5-በጣም እስማማለሁ፣ 4-እስማማለሁ፣ 3-መወሰን ያስቸግረኛል፣ 2-አልስማማምና 1-በጣም አልስማማም የሚሉ ናቸው። ለትንተናው አመቺነት ሲባልም በጥናቱ ውስጥ አምስተኛና አራተኛ ምርጫዎችን አዎንታዊ በማለት፣ ሶስተኛውን እንዳለ በመውሰድና፣ ሁለተኛና አንደኛ ምርጫዎችን ደግሞ አሉታዊ በማለት ተሰባስበዋል። ስለዚህም መምህራንና ተማሪዎች የሰጧቸው ምላሾች አዎንታዊ፣ መወሰን ያስቸግረኛልና አሉታዊ ወደሚሉ ሶስት ምርጫዎች ተሰባስበው በቁጥርና በመቶኛ በማስላት ተተንትነዋል።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃዎች ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በክለሳ ድርሳን ውስጥ ከቀረቡ የአቀራረብና የአደረጃጀት ንድፈ ሀሳቦች አንጻር እየተፈተሹ ይተነተናሉ፡፡ ትንተናውን ከመጻህፍቱ አዘጋጆች በቃለ መጠይቅ፣ ከየደረጃዎቹ መምህራንና ተማሪዎች ደግሞ በጽሁፍ መጠይቅ በተገኙ ምላሾች፣ እንዲሁም ከየደረጃዎቹ መርሃ ትምህርቶች በተገኙ መረጃዎች ለማጠናከር ጥረት ይደረጋል፡፡ በቅድሚያ ግን ስለ መማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ ገጽታ አጠር ያለ የቅኝት ዘገባ ይቀርባል፡፡

### 4.1 የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ ቅኝት

የመማሪያ መጻህፍቱ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ባለመብትነት የአምስተኛና የስድስተኛ ክፍሎቹ በ1998 ዓ.ም፣ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍሎቹ ደግሞ በ1997 ዓ.ም ታትመው የቀረቡና እስከ አሁን ድረስ በስራ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በመማሪያ መጻህፍቱ ውጫዊ ሽፋን የፊት ለፊት ገጽ ላይ የክፍል ደረጃዎቹ ከተጠቀሱ በኋላ ‹‹አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ›› የሚል ርዕስ የተሰጣቸው ሲሆን፤ ከመጻህፍቱ የጀርባ ሽፋን በስተግርጌ ደግሞ ዋጋቸው ይገኛል፡፡ ከውጫዊ ሽፋን ወደ እያንዳንዱ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጣዊ ገጽ ሲገባ በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ መጻህፍቱ ለነማን ወይም ለምን አይነት ተማሪዎች (ለመጀመሪያ ወይም ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች) እንደተዘጋጁ የሚገልጽ ምንም አይነት መረጃ አይገኝባቸውም፡፡ የእያንዳንዱ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጣዊ ገጽታ በአጭሩ ሲቃኝ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሀ. የአምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ የፊት ለፊት/ውጫዊ ሽፋን ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ የመጽሐፉን ባለመብት፣የታተመበትን ዘመን፣አዘጋጆቹንና አርታኢውን/ኤዲተሩን የሚጠቁሙ መረጃዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ ደግሞ ስለ ቋንቋ ምንነት ባጭሩ የተጻፈ መግቢያ ይገኛል፡፡ ይህ የመማሪያ መጽሐፍ 110 ገጾች፣ ሰላሳ ሦስት

ምዕራፎች/ምንባቦችና ዘጠና ዘጠኝ መልመጃዎችን አካቶ ይዟል። ከሰላሳ ሦስቱ ምዕራፎች በሃያ ሁለቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተውባቸዋል።

**ለ. የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

እንደ አምስተኛ ክፍሉ ሁሉ በዚህም የመማሪያ መጽሐፍ ውጫዊ የፊት ለፊት ሽፋን ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ የመጽሐፉን ባለመብት፣የህትመት ዘመን፣አዘጋጆቹንና አርታኢውን የሚጠቁሙ መረጃዎች የሚገኙ ሲሆን፤ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ ደግሞ ስለ ደረጃው የቋንቋ ትምህርት አላማ በአጭሩ የተጻፈ መግቢያ ያስነብባል። ይህ የመማሪያ መጽሐፍ 114 ገጾች፣ሃያ አራት ምዕራፎች/ምንባቦችና ስልሳ አምስት መልመጃዎች ያሉት ሲሆን፤ ከሃያ አራቱ ምዕራፎች በአስራ ሶስቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተውባቸዋል።

**ሐ. የሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ የፊት ለፊት ሽፋን ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ የመጽሐፉን ባለ መብትና የህትመት ዘመን ብቻ የሚገልጹ መረጃዎች የሚገኙ ሲሆን፤ የመጽሀፉን አዘጋጆችና አርታኢውን በተመለከተ ምንም መረጃ የለውም። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ የደረጃውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ በአጭሩ የሚገልጽ መግቢያ ይገኛል።ይህ የመማሪያ መጽሐፍ 125 ገጾች፣ሃያ ስምንት ምዕራፎች/ምንባቦችና ሰማኒያ መልመጃዎችን ይዞ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህንን መጽሐፍ ከሌሎቹ ልዩ የሚያደርገው በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተው መገኘታቸው ነው።

**መ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

ከላይ እንደተገለጹት ሁሉ በዚህም የመማሪያ መጽሐፍ የመጀመሪያ የውስጥ ገጽ ላይ የመጽሐፉን ባለመብት፣የህትመት ዘመን፣አዘጋጆቹንና አርታኢውን የሚጠቁሙ መረጃዎች የሚገኙ ሲሆን፤ከዚህ ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ ደግሞ የደረጃውን የቋንቋ ትምህርት አላማ አካቷል። ይህ የመማሪያ መጽሐፍ 238 ገጾች፣ሰላሳ ምዕራፎች/ምንባቦችና አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ መልመጃዎችን አካቶ የያዘ ሲሆን፤ ከሰላሳዎቹ ምዕራፎች በአስራ ስምንቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ።

ሌላው በተተኳሪ የመማሪያ መጻሀፍቱ ውስጥ የሚታየው የወል ባህርይ በእያንዳንዱ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችም ሆኑ ሌሎች ይዘቶች (ክሂሎችና ስነጽሁፍ) በልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልቶች መቅረብ መቻላቸው ነው፡፡ ይኸውም ለምሳሌ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በገለጻ፣በምሳሌዎችና በመልመጃዎች መልክ የቀረቡ ሲሆን፤ መልመጃዎች ደግሞ በእውነት ሐሰት፣ በምርጫ፣ በአዛምድ፣ ባዶ ቦታ በመሙላት፣ በሰንጠረዥ፣ የተዘበራረቁትን በማስተካከል፣ በጽሁፍ፣ በውይይት፣ በቃል በመመለስ፣ ወዘተ የአቀራረብ ስልቶች በሁሉም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ታይተዋል፡፡ የመማሪያ መጻህፍቱን አጠቃላይ ቅኝት በተመለከተ አጠር ባለ መልክ ማየት ይቻል ዘንድ የሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ ስድስት፡- የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ መረጃ

| መረጃዎች | የክፍል ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ | 8ኛ |
| የህትመት ዘመን | 1998ዓ.ም | 1998ዓ.ም | 1997ዓ.ም | 1997ዓ.ም |
| የገጽ ብዛት | 110 | 114 | 125 | 238 |
| የምዕራፍ/የምንባብ ብዛት | 33 | 24 | 28 | 30 |
| የመልመጃዎች ብዛት | 99 | 65 | 80 | 139 |
| የሰዋስው ትምህርት የቀረበባቸው ምዕራፎች/ምንባቦች ብዛት | 22 | 13 | 28 | 18 |
| ዋጋ | 4.65 | 5.15 | 4.50 | 6.90 |

## 4.2 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1 ከግልጽነት አንጻር

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጥሩ አቀራረብ አላቸው ለማለት ከሚያስችሉት መርሆዎች ውስጥ አንዱ ግልጽነት ነው፡፡ ይህንንም ማድረግ ይቻል ዘንድ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ገለጻዎች/ማስታወሻዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትዕዛዞችና የመልመጃ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ለመረዳት የማያስቸግሩ፣ ግርታን የማይፈጥሩ፣

የማያጠራጥሩና ውስብስብነት የሌላቸው እንዲሆኑ ይመከራል። ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ያላቸውን የግልጽነት ገጽታ ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል ለማስቃኘት ይሞከራል።

በማስቀደም ግን የመምህራንንና የተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች አጠቃለው የያዙ የተለያዩ ሁለት ሰንጠረዦች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ። ይህም የሆነበት አቢይ ምክንያት በእያንዳንዱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ርዕሰ ጉዳይ ትንታኔ ስር ትንታኔውን ለማጠናከር ሲባል በተደጋጋሚ ይቀርቡ የነበሩ በርካታ ሰንጠረዦችን ለማስቀረት ይጠቅማል ተብሎ ስለታመነበት ነው።

ሰንጠረዥ ሰባት፡- የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| ተቁ | ጥያቄዎች | መምህራኑ የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ፣ ብዛታቸውና ምላሾቻቸው | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ= 2 መምህራን | | | 6ኛ= 2 መምህራን | | | 7ኛ= 2መምህራን | | | 8ኛ= 2መምህራን | | |
| | | አዎ. | መ.ያ | አሉ. | አዎ. | መ.ያ | አሉ. | አዎ. | መ.ያ | አሉ. | አዎ. | መ.ያ | አሉ. |
| | | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር | በቁጥር |
| 1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች/ማስታወሻዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | - | 1 | 1 | - | - | 2 | - | - | 2 | 1 | - | 1 |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው | - | - | 2 | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 |
| 3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ምሳሌዎች ግልጽ ናቸው | - | 1 | 1 | - | - | 2 | - | - | 2 | - | 1 | 1 |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው | - | - | 2 | - | - | 2 | - | - | 2 | - | 1 | 1 |
| 5 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስህተት የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ | 1 | - | 1 | 1 | 1 | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 | - |
| 6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ስለ አማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ማወቅ የሚገባቸውን የሚያሳውቁ ናቸው | 1 | 1 | - | 1 | - | 1 | - | - | 2 | - | 1 | 1 |
| 7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች የመስራት አቅም ወይም የክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው | - | 1 | 1 | 1 | 1 | - | - | 1 | 1 | - | - | 2 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ የተውጣጡ ናቸው፡፡ | - | - | 2 | - | 1 | 1 | - | - | 2 | - | - | 2 |
| 9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ | - | - | 2 | - | - | 2 | - | - | 2 | - | - | 2 |
| 10 | በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ጨምረዋል፡፡ | - | 2 | - | - | 1 | 1 | - | - | 2 | - | - | 2 |
| 11 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ካሉበት የክፍል ደረጃ በፊት የተዋወቋቸው ናቸው | - | 1 | 1 | - | 2 | - | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 |
| 12 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርአት እራሳቸው በሂደት እንዲያውቁት በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው | 1 | 1 | - | 1 | - | 1 | - | - | 2 | - | - | 2 |
| 13 | በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎችንና ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርአት ለመለማመድ በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ | 1 | - | 1 | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 | 1 | 1 | - |

አዎ. = አዎንታዊ ማለት ነው

መ.ያ = መወሰን ያስቸግረኛል ማለት ነው

አሉ. = አሉታዊ ማለት ነው

# ሰንጠረዥ ስምንት፦ የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የመላሾች የክፍል ደረጃ፣ ብዛትና መልሶች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ= 84 ተማሪዎች | | | | | | 6ኛ= 78 ተማሪዎች | | | | | | 7ኛ= 63 ተማሪዎች | | | | | | 8ኛ=56 ተማሪዎች | | | | | |
| | | አዎ. | | መ.ያ | | አሉ. | | አዎ. | | መ.ያ | | አሉ. | | አዎ. | | መ.ያ | | አሉ. | | አዎ. | | መ.ያ | | አሉ. | |
| | | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % | ቁ. | % |
| 1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች/ማስታወሻዎች ገልጽ ናቸው፡፡ | 52 | 62 | 32 | 38 | - | - | 50 | 64 | 12 | 15 | 16 | 21 | 40 | 63 | 8 | 13 | 15 | 24 | 32 | 57 | - | - | 24 | 43 |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው | 41 | 49 | 13 | 15 | 30 | 36 | 38 | 49 | 7 | 9 | 33 | 42 | 30 | 48 | 11 | 17 | 22 | 35 | 28 | 50 | 7 | 13 | 21 | 37 |
| 3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ምሳሌዎች ግልጽ ናቸው | 35 | 43 | 14 | 17 | 34 | 40 | 49 | 63 | - | - | 29 | 37 | 41 | 65 | - | - | 22 | 35 | 29 | 52 | 8 | 14 | 19 | 34 |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው | 41 | 49 | 8 | 9 | 35 | 42 | 51 | 65 | 6 | 8 | 21 | 27 | 36 | 57 | 4 | 6 | 23 | 37 | 26 | 46 | 11 | 20 | 19 | 34 |
| 5 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ስለአማርኛ ቋንቋ ስርአት ማወቅ የሚገባኝን ነገር ያሳውቁኛል፡፡ | 65 | 77 | 6 | 7 | 13 | 16 | 57 | 73 | 7 | 9 | 14 | 18 | 51 | 81 | - | - | 12 | 19 | 40 | 71 | - | - | 16 | 29 |
| 6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታዬ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ | 40 | 48 | 12 | 14 | 32 | 38 | 40 | 51 | 10 | 13 | 28 | 36 | 35 | 56 | 5 | 8 | 23 | 36 | 29 | 52 | 7 | 13 | 20 | 35 |
| 7. | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ቀርበውልኛል፡፡ | 40 | 48 | 9 | 11 | 35 | 41 | 36 | 46 | - | - | 42 | 54 | 30 | 48 | 8 | 13 | 25 | 39 | 29 | 52 | 4 | 7 | 23 | 41 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አሁን ካለሁበት የክፍል ደረጃ በፊት ተዋውቂያቸው ነበር:: | 40 | 48 | 15 | 18 | 29 | 34 | 39 | 50 | 13 | 17 | 26 | 33 | 31 | 49 | 9 | 14 | 23 | 37 | 30 | 54 | - | - | 26 | 46 |
| 9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ካለፈው አመት ከበድ ያሉ ወይም የጠነከሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ:: | 45 | 54 | 13 | 15 | 26 | 31 | 32 | 41 | 16 | 21 | 30 | 38 | 32 | 51 | - | - | 31 | 49 | 26 | 46 | 8 | 14 | 22 | 40 |
| 10 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቋንቋውን ስርአት ራሴ በሂደት እንዳውቅ ወይም እንድደርስበት ለመለማመድ የሚያስችሉኝ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ:: | 28 | 33 | 16 | 19 | 40 | 48 | 39 | 50 | 6 | 8 | 33 | 42 | 30 | 48 | 11 | 17 | 22 | 35 | 27 | 48 | 5 | 9 | 24 | 43 |
| 11 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አስቀድመው ስለ ቋንቋው ስርአት ገለጻና ምሳሌዎችን በመስጠት የቋንቋውን ስርአት ወደ መለማመድ የሚያሸጋግሩኝ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ:: | 40 | 48 | 8 | 10 | 36 | 42 | 33 | 42 | 18 | 23 | 27 | 35 | 25 | 40 | 6 | 10 | 32 | 50 | 24 | 43 | 10 | 18 | 22 | 39 |

አዎ. = አዎንታዊ ማለት ነው

መ.ያ = መወሰን ያስቸግረኛል ማለት ነው

አሉ. = አሉታዊ ማለት ነው

ቁ. = በቁጥር ማለት ነው

%. = በመቶኛ ማለት ነው

## 4.2 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1 ከግልጽነት አንጻር

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት የአማርኛ መማሪያ መጻሀፍት ውስጥ ተካተው በሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ አልፎ አልፎ ጎላ ብለው የሚታዩ የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዞች፣ ምሳሌዎችና ጥያቄዎች የግልጽነት ችግሮች መኖራቸውን በተደረገው ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ የመልመጃ ትዕዛዝ ግልጽነት ችግሮች ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል፤ የምሳሌ ግልጽነት ችግሮች 7ኛና 8ኛ ክፍል፤ እንዲሁም የጥያቄ ግልጽነት ችግሮች 5ኛና 6ኛ ክፍል ታይተዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል እነዚህን ጎላ ጎላ ያሉ የግልጽነት ችግሮች ከየደረጃዎቹ መማሪያ መጻህፍት አስረጅ በመውሰድ በቅደም ተከተል ለማሳየት ይሞከራል፡፡

**ሀ. የመልመጃ ትዕዛዞች ግልጽነት ችግሮች**

2. በምሳሌው መሰረት ከትክክለኛው ተመሳሳይ ጋር

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 2.1 አስፈላጊ | ሀ. አይሆንም |
| 2.2 ለማጠንከር | ለ. ሌሎች |

. . . /5ኛ ክፍል፣ገጽ፣13/

ከዚህ በላይ ከ5ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተወስዶ በአስረጅነት የቀረበው መልመጃ ትዕዛዝ ሲፈተሽ አንደኛ፣ምንም የተሰጠ ምሳሌ በሌለበት ‹‹በምሳሌው መሰረት…›› ብሎ ይጀምራል፤ ሁለተኛ፣ ተማሪዎች በ‹‹ሀ›› እና በ ‹‹ለ›› ስር ያሉትን ቃላት/ሐረጋት ከትክክለኛው ተመሳሳይ ጋር ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የተገለጸ ነገር የለም፤ ወይም ትዕዛዙ መቋጫ የለውም፡፡ ‹‹በምሳሌው መሰረት ከትክክለኛው ተመሳሳይ ጋር›› ብሎ የሚያቆም ያልተሟላ ትዕዛዝ ነው፡፡ በ5ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዝን ግልጽነት በተመለከተ ይህ ለአብነት ቀረበ እንጂ ተመሳሳይ የትዕዛዝ ግልጽነት ችግሮች በመጽሐፉ ገጽ፡- 2፣3፣ እና 5 ላይም ይገኛሉ፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞችን ግልጽነት በተመለከተ በደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣መጠይቅ ቁጥር ሁለት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ

መጠይቅ ሁለቱም መምህራን የሰጡት ምላሽ አሉታዊ ነው፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች አልፎ አልፎ የግልጽነት ችግር እንደሚታይባቸው የሚጠቁም ነው፡፡

ሀ. ከዚህ ቀጥሎ የተዘበራረቁና ሲነበቡም ትርጉም የማይሰጡ ቃላት
ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ቃላት ቅንብራቸውን አስተካከላችሁ አረፍተ ነገር
መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ጥያቄ፡- ትምህርት ተጀመረ የአመቱ፡፡

መልስ፡- የአመቱ ትምህርት ተጀመረ፡፡

1. ደመቀች ወላጅ ስለቀረች ከትምህርት ቤት አምጪ ተባለች፡፡

. . . /6ኛ ክፍል፣ገጽ፣3/

ከዚህ በላይ ከ6ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተወስዶ በአስረጅነት የቀረበው የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዝ ሲፈተሽ አደናጋሪና ግልጽነት የጎደለው ሆኖ ይገኛል፡፡ አንድ የተሟላ አረፍተ ነገር ሊመሰርቱ የሚችሉ ቃላት በምሳሌውም ሆነ በመልመጃው ጥያቄዎች (ለምሳሌ፡- ጥያቄ ተራ ቁጥር 1) ውስጥ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቆ ይታያል፡፡ ከዚህ አንጻር ብቻ ያየነው እንደሆነ የመልመጃው ትዕዛዝ ግልጽ መስሎ ሊታየን ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ‹‹…ሲነበቡም ትርጉም የማይሰጡ ቃላት…›› የሚለው የትዕዛዙ አካል ሲመረመር ግን የመልመጃውን ትዕዛዝ ግልጽነት ይሸረሽረዋል፡፡ ምክንያቱም በምሳሌውም ሆነ በጥያቄ ተራ ቁጥር 1 ላይ ማየት እንደሚቻለው ቃላቱ ተዘበራርቀው ቀረቡ እንጂ በተናጠል ሲታዩ እያንዳንዳቸው ትርጉም የሌላቸው ሆነው አይገኙም፡፡ ወይም ደግሞ ጥያቄው ትእዛዙ የሚለውን ጉዳይ ይዞ መገኘት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ገጽ 4 ላይም ሌላ የትዕዛዝ ግልጽነት ችግር ታይቷል፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው፡፡››* (ሰንጠረዥ ስምንት፣ መጠይቅ ቁጥር ሁለት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ 49% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽነት እንዳላቸው ቢጠቁሙም፤ በአንጻሩ ደግሞ 9% ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩ ሲሆን፤ 42% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዛቱ የግልጽነት ችግር እንደሚታይባቸው ይገልጻሉ፡፡ በጥቅሉ ሲታይ በመማሪያ

መጽሐፉ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ሙሉ በሙሉም ባይሆን አልፎ አልፎ የግልጽነት ችግር እንደሚታይባቸው ያስገነዝባል፡፡

7. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የስም ረጃጅም ፀጉር አለው፡፡

7.1 ወንዱ አጋዘን አንገቱ ላይ ረጃጅም ፀጉር አለው፡፡

7.2 የአጋዘን ምግብ ቀንበጥና ጨቅላ የዛፍ ቅርንጫፍ ነው፡፡

. . . /7ኛ ክፍል፤ገጽ፣16/

ከዚህ በላይ በአስረጅነት የቀረበው መልመጃ ከ7ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ገጽ 16 የተወሰደ ነው፡፡ ተማሪዎች ከላይ በአስረጅነት የቀረበውን መልመጃ ትዕዛዝ በምንም አይነት መልኩ መረዳት ይችላሉ ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ይህ በሀሳብ የማይገናኙ ቃላትን/ሐረጋትን የያዘ ‹‹ትእዛዝ›› ነው፡፡ ይህ አይነቱ ግድፈት ከበድ ያለ የግልጽነት ችግር ከመፍጠሩም በላይ ምን ለማለት እንደፈለገ ለመገመት እንኳ ከባድ ነው፡፡ ከተማሪዎች ደረጃና አቅም አኳያ ሲታይ ይቻላል ብሎ ለማሰብ ቢከብድም ከጥያቄዎቹ (7.1፣7.2፣ወዘተ) ለመገመት እንደሚቻለው ‹‹ትዕዛዙ›› ሊማለት የፈለገው የሚከተለውን ሆኖ ይገኛል፤‹‹ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የስም ገላጭ የሆኑትን ለዩ/ለይታችሁ አሳዩ፡፡›› ሀሳቡ ይህ ከሆነ ወይም በዚህ መልክ ከተስተካከለ ተማሪዎች ያለምንም መደናገር ወደ ተግባራቸው ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከዚህ ውጭ ጎላ ያለ የግልጽነት ችግር የሚታይበት የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዝ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ በደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር ሁለት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ አንድ መምህር/ት ለመወሰን እንደተቸገሩ ሲገልጹ፤ አንድ መምህር/ት ግን አሉታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች የግልጽነት ችግር ይታይባቸዋል ይላሉ፡፡

3. በሚከተለው ምሳሌ መሰረት ከግስ የተገኘ ስምንና የስም ገላጭን መስርቱ፡፡

ሀ. አወቀ

ለ. አረሰ

. . . /8ኛ ክፍል፤ገጽ፣12/

ከዚህ በላይ ከ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተወስዶ በአስረጅነት ከቀረበው መልመጃ ትዕዛዝ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች መጀመሪያ ምሳሌ ያገኛሉ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ከቀረቡላቸው ቃላት (ግሶች) በምሳሌው መሰረት ስምንና የስም

ገላጮችን ይመሰርታሉ። ይሁን እንጂ ከትዕዛዙ ቀጥሎ ምንም የተሰጠ ምሳሌ የለም። ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ያደናግራል፤ወይም ደግሞ መልመጃውን በቀላሉና ሳይቸገሩ መስራት እንዳይችሉ ያደርጋል ማለት ነው። ተማሪዎች በቀረበላቸው ምሳሌ መሰረት መልመጃውን እንዲሰሩ ከታዘዙ በኋላ ምንም ምሳሌ ሳያቀርቡ መቅረት ተገቢ አይደለም። ምንም እንኳ ሁልጊዜ ምሳሌ መቅረብ አለበት ተብሎ ባይታመንም። በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መጠነኛ የሆነ የግልጽነት ችግር የሚታይበት ሌላ የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዝ በገጽ 6 ላይም ይታያል። ይህን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው።››* (ሰንጠረዥ ስምንት፣ መጠይቅ ቁጥር ሁለት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ መጠይቁን ከሞሉት ከአጠቃላዩ 56 ተማሪዎች ውስጥ 50% ተማሪዎች አዎንዊ ምላሽ ቢሰጡም፤በአንጻሩ ደግሞ 13% ተማሪዎች ለመወሰን መቸገራቸውንና 37% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትዕዛዞች የግልጽነት ችግር ይታይባቸዋል ሲሉ ይገልጻሉ።

## ለ. የምሳሌዎች ግልጽነት ችግሮች

ከ5ኛ እስከ 7ኛ ክፍል ባሉት አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ይህ ነው የሚባል የግልጽነት ችግር የሚታይባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ምሳሌዎች የሉም። በ8ኛ ክፍል አንድ መልመጃ ላይ ጎላ ያለ የግልጽነት ችግር የሚታይበት የሰዋስዋዊ መልመጃ ምሳሌ አለና ይህን ቀጥሎ እንይ።

3. የሚከተሉት ቃላት ቅጥያዎችን በመውሰድ የተመሰረቱ ናቸው። በቀረቡት ምሳሌዎች መሰረት ዋና ቃልና ቅጥያዎቹን በመለየት ጻፉ።

| | ቃላት | ዋና ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | 3.1 ደብተር | ደብተር | - ህ |
| | 3.2 ቃላት | ቃል | - ኣት |

. . . /8ኛ ክፍል፤ገጽ፣7)

ከዚህ በላይ በአስረጅነት በቀረበው መልመጃ ምሳሌዎች ውስጥ ግልጽ ያልሆነና ተማሪዎችን ግር ሊያሰኝ የሚችል ሁኔታ ተከስቶ ይታያል። ይኸውም በምሳሌነት በቀረበው (3.1) ውስጥ ‹‹ቃላት›› በሚለው ስር ያለው ‹‹ደብተር›› የሚለው ቃል ‹‹ደብተርህ›› ተብሎ ሊቀመጥ ይገባው ነበር። ነገር ግን የሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣

ወንዴ ጾታ ባለቤትነትን የምታመለክተው ቅጥያ (-ህ) ቃሉ (ደብተር) ላይ ተቀጥላ ሳትታይ ‹‹ቅጥያ›› በሚለው ስር ግን ወጥታለች ወይም ተለይታ ትታያለች። ይህ ስህተት ነው፤ተማሪዎችንም ሊያደናግር ይችላል። የዚህ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዷ፣ *‹‹በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው? ለምሳሌ ከግልጽነት አኳያ?››* በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ *‹‹የግልጽነት ችግር አለበት ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ምንም ልምድና ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ የተዘጋጀ እንደመሆኑ የተለያዩ የግልጽነት ችግሮች ተፈጥረዋል። ይህንን ራሴም መጽሐፉ ከታተመ በኋላ አይቼው አረጋግጫለሁ።››* የሚል ነው። አዘጋጇ ይህን ይበሉ እንጂ በዚህ የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከላይ ከቀረበው ውጭ የምሳሌ ግልጽነት ችግር የሚታይበት ሰዋስዋዊ ይዘት አልተገኘም።

## ሐ. የጥያቄዎች ግልጽነት ችግሮች

ትኩረት በተደረገባቸው አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስዋዊ ጥያቄዎችን የግልጽነት ችግሮች በተመለከተ በተደረገው ፍተሻ በ5ኛና በ6ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ጎላ ጎላ ያሉ የግልጽነት ችግሮች የሚታዩባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የተገኙ ሲሆን፣ በ7ኛና በ8ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ግን ይህ ችግር አልታየም። ቀጥሎ ከ5ኛና ከ6ኛ ክፍል አስረጅ በመውሰድ የሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ጥያቄዎች የግልጽነት ችግሮች በቅደም ተከተል ለማሳየት ይሞከራል።

ጥንድ ጥንድ እየሆንን በመወያየት ትክክለኛውን አረፍተ ነገር እየለየን እንጽፋለን።

ምሳሌ፡- ሀ. የጠጣኋቸው ውሃዎች ይጣፍጣሉ።

ለ. የጠጣሁት ውሃ ይጣፍጣል።

ትክክለኛው አረፍተ ነገር ‹‹ለ›› ነው።

1. ዘቢደር ———— በላች።

ሀ. እንቁላል ለ. እንቁላሎች

2. ኡፋይሴ ————ሰራች።

ሀ. ወጥ ለ. ወጦች

. . . /5ኛ ክፍል፤ገጽ፣3/

ከላይ በቀረበው አስረጅ ውስጥ እንደሚታየው ትዕዛዙና ጥያቄዎቹ ወይም ምሳሌዎቹና ጥያቄዎቹ አይናበቡም። በትዕዛዙና በምሳሌዎቹ መሰረት ከሆነ በጥያቄዎቹ ውስጥ ትክክልና ስህተት የሆኑ አረፍተ ነገሮች ተደባልቀው ከቀረቡ በኋላ ተማሪዎች ትክክለኛ የሆኑትን አረፍተ ነገሮች እየለዩ መጻፍ ነበረባቸው/ይኖርባቸዋል። በመሆኑም በአስረጁ

ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች አቀማመጥ ትክክል ወይም ግልጽ አይደለም፡፡ የተቀመጡት ጥያቄዎች የሚያመለክቱት ተገቢ ቃላት በመምረጥ ጅምር አረፍተ ነገሮችን የማሟላት ሁኔታን ነው እንጂ ትዕዛዙ እንደሚለውና ምሳሌው እንደሚያሳየው ትክክለኛውን አረፍተ ነገር ትክክል ካልነው ለይቶ የመጻፍን ሁኔታ አይደለም፡፡ በመሆኑም ጥያቄው የግልጽነት ችግር አለበት፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣መጠይቅ ቁጥር አራት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የሁለቱም መምህራን አሉታዊ ነው፡፡ መምህራኑ ይህን ይበሉ እንጂ በዚህ የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከላይ በአስረጅነት ከቀረበው ውጭ የግልጽነት ችግር የሚታይበት ሌላ የሰዋስዋዊ መልመጃ ጥያቄ አልታየም፡፡

ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ትርጉም ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ሰዉዬው ስዕል ሳለ፡፡ /ስዕል ሰራ/

2. ልጅቷ ለሽንኩርት መክተፊያ ቢለዋውን ሳለች፡፡/ሞረደች/

3. ጓደኛዬ ጉንፋን ስለያዘው ሳለ፡፡/ ጎሮሮውን አጠራ/

1. ወይዘሮ ጀንበር በቃላቸው የማይጠኑ አባይ ሰው ናቸው፡፡

2. አባይ ለሙን አፈራችንን ለግብጽ ይሰጣል፡፡

. . . /6ኛ ክፍል፤ገጽ፣27/

ከዚህ በላይ በአስረጅነት የቀረበውን መልመጃ ስንመለከት ትዕዛዙ እንደሚለው በመልመጃው ጥያቄዎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት አናገኝም፡፡ እንደ ትዕዛዙ ሀሳብ ከሆነ በጥያቄዎቹ ውስጥ ትርጉም እንዲሰጣቸው የተፈለጉት ቃላት ከስራቸው ተሰምሮባቸው ሊገኙ በተገባ ነበር፡፡ ይህ ባለመሆኑ ደግሞ የመልመጃው ጥያቄዎች የግልጽነት ችግር ተስተውሎባቸዋል፡፡ ተማሪዎች የመልመጃውን ምሳሌዎች ተረድተው ወደ ጥያቄዎቹ ሲሸጋገሩ ግር መሰኘታቸው አይቀርም፡፡ የዚህ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዱ፣ *‹‹በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው? ለምሳሌ ከግልጽነት አኳያ?››* በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ *‹‹መጽሐፉን ለማዘጋጀት የተሰጠን ጊዜ በጣም አጭር ከመሆኑ የተነሳ የሩጫና የይድረስ ይደረስ ስራ ነው የሰራነው፡፡ በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የግልጽነት ችግርም ሆነ ሌሎች ስህተቶች አይኖሩም ብዬ አላምንም፡፡››* የሚል

ነው፡፡አዘጋጁ ይህን ይበሉ እንጂ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካተው በሚገኙት የሰዋስዋዊ መልመጃ ጥያቄዎች ላይ የጎላ የግልጽነት ችግር እንደማይታይ በምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.2.2 ከትክክለኛነት አንጻር

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው ትክክለኛነት እውነተኛውን የቋንቋውን ስነልሳናዊ ባህሪ ወይም የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበትን ይዘት የሚመለከት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ለተማሪዎች የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ትክክለኛና እውነተኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ ለተማሪዎች ስህተት የሚያስተምሩ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ በአጠቃላይ ትክክለኛነት በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሚሰጡት መረጃ አንጻር እውነተኛ መሆን እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በማስከተል በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ከዚህ ንድፈ ሀሳብ አንጻር ያላቸውን ገጽታ ለማሳየት ይሞከራል፡፡

ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ባሉ አራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሁለት አበይት የትክክለኛነት ወይም ችግሮች ታይተዋል፡፡ እነሱም የቃላትንና የሐረጋትን አሰያየም ወይም ስያሜ በተመለከተና ስለ ሰዋስዋዊ ይዘት ገለጻ ትክክለኛነት ችግሮች የቀረቡ ሲሆኑ፤ እነዚህን በቅደም ተከተል ከየደረጃዎቹ መማሪያ መጻህፍት አስረጅ በመውሰድ እናያለን፡፡

### ሀ. የቃላትና የሀረጋት ስያሜዎች ትክክለኛነት ችግሮች

1. ከዚህ በታች ካሉት ሐረጋት እየመረጥሁ በባዶ ቦታው ላይ በመጻፍ
   አረፍተ ነገሮችን እመሰርታለሁ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሥራ | ዝናብ | ቅራቅንቦ | ቀለዋጭ |
| ኤድስ | ዝንብ | በረዶ | - |

1.1 -------------- የሰውን ልጅ ያስከብራል፡፡

. . .    /5ኛ ክፍል፤ገጽ፣2/

በትዕዛዙ ውስጥ በግልጽ እንደሚታየው፣ ‹‹…ሐረጋት…›› የሚለው ቃል/ሀሳብ

በሰንጠረዡ ውስጥ የተዘረዘሩትን በትክክል የሚገልጽ ሆኖ የሚገኝ አይደለም። ይህ ተማሪዎች ስለ ቃላትና ሐረጋት ምንነት/ባህርይ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያዛባ ወይም የሚፈታተን ሆኖ የሚገኝ ነው። በሰንጠረዡ ውስጥ ተዘርዝረው የሚታዩት ስድስት ስሞችና አንድ ቅጽል ናቸው። በአጠቃላይ ሲታዩ ትክክለኛ መጠሪያ ሊሆናቸው የሚችለው ቃላት እንጂ ሐረጋት የሚለው አይደለም። በመሆኑም ወይ ትዕዛዙ ሊታረም፣ አለበለዚያ ደግሞ በሰንጠረዡ ውስጥ የተዘረዘሩት በሙሉ የሐረግነት ባህርይ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስህተት የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል።››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣መጠይቅ ቁጥር አምስት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ምንም እንኳ የአንድ መምህር/ት አዎንታዊ ቢሆንም፤አንድ መምህር/ት ግን አሉታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎችን ለስህተት የሚዳርጉ እንዳልሆኑ ወይም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርአት በትክክል የማቅረብ ችግር እንደማይታይባቸው ይገልጻሉ።በምልከታው ማረጋገጥ የተቻለው ግን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ሰዋስዋዊ ስያሜዎችን(ቃላት/ሀረጋት) በትክክለኛ ቦታቸው የመጠቀም ችግር እንደሚታይበት ነው። ለምሳሌ ከላይ በአስረጅነት ከቀረበው ሌላ በመጽሀፉ ገጽ 11 እና 23 ላይ ተመሳሳይ ችግሮች ታይተዋል።

ሐ. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በተመሳሳይ
ትርጉም ሊተኩ የሚችሉትን ምረጡ።

. . .

4. የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት ባለመዳረሱ የህዝብ ቁጥር ከፍ እያለ መጥቷል።

ሀ. እየጨመረ ለ. እየቀነሰ ሐ. እየተጋመሰ መ. እየሞላ

. . .

6. መድሐኒቱ ከበሽታ ሊፈውስ ይችላል።

ሀ. ሊከላከል ለ. ሊያድን ሐ. ሊስማማ መ. ሊያሻሽል

/6ኛ ክፍል፤ገጽ፣11/

ከላይ በአስረጅነት በቀረበው መልመጃ በጥያቄ ተራ ቁጥር 4 እና 6 በሚገኙት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ከስራቸው ተሰምሮባቸው የምናገኛቸው በመልመጃው ትዕዛዝ እንደተገለጸው ቃላትን ሳይሆን ሐረጋትን ወይም ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን ነው። በእርግጥ ይህ ቀላል ግድፈት ሊመስል ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ሁኔታ በ5ኛ ክፍሉ ውስጥ እንደተገለጸው ተማሪዎች ለቃላትና ለሐረጋት ወይም ለጥገኛ

አረፍተ ነገሮች ምንነት ያላቸው ግንዛቤ የተምታታ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይህን መሰል ስህተቶች በገጽ፡- 19፣25፣28፣30 እና 34 ላይ ይታያሉ፡፡

4. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ጅምር ዐ.ነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሄደት፣አጣዳፊ፣ክፉ ህመም፣ንቁ፣እንጂ፣የሚያስከብር፣ስለሚሆን፣ወሰንየለሽ

. . .    /7ኛ ክፍል፣ገጽ፣5/

ከላይ በቀረበው አስረጅ ውስጥ ተዘርዝረው የቀረቡት ትዕዛዙ እንደሚለው ቃላት ብቻ ሳይሆኑ ሐረግም ጭምር ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም ቃላትንና ሐረጋትን አቀላቅሎ አቅርቦ በአንዱ ብቻ መጥራት ተገቢ አይደለም፡፡ ያሳስታል፤ ግንዛቤን ያዛባል፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይህን መሰል ስህተቶች በገጽ፡- 10፣14፣21፣50 እና 73 ላይ በግልጽ ይታያሉ፡፡

በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ተመሳሳይ ችግር ይታያል፡፡ ለምሳሌ ያህል በአስረጅነት ለማየት፣‹‹ለሚከተሉት ቃላት ፍቺያቸውን ከቀረቡት አማራጮች ምረጡ፡፡›› ይልና ፍቺያቸው እንዲመረጥ ከተቀመጡት ውስጥ፣‹‹ይበል የሚያሰኝ፣በማይነጥፍ፣ የሚያለዝብ፣ መንገድ እያሳበሩ፣ ወዘተ›› የሚሉ ሐረጋት ይገኙበታል፤ (ገጽ፣22)፡፡ ይህን መሰል ስህተቶች በመጽሐፉ ገጽ፡- 29፣35፣52፣61 እና 169 ውስጥ በግልጽ ይታያሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ይህ ሰዋስዋዊ ስህተት ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚታይ የወል ችግር ነው ማለት ይቻላል፡፡ የመማሪያ መጻህፍቱን ተመሳሳይ ሰዎች ያዘጋጇቸው እስኪመስል ድረስ፤ ይሁን እንጂ መጻህፍቱን የተለያዩ ባለሙያዎች እንዳዘጋጇቸው በውስጣቸው የያዙት መረጃ ያመለክታል፡፡

### ለ. የሰዋስዋዊ ይዘት ገለጻ ትክክለኛነት ችግሮች

ጉልህ የሆኑ የሰዋስዋዊ ይዘት ገለጻ ትክክለኛነት ችግሮች የታዩት በ7ኛና በ8ኛ ክፍሎች አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ነው፡፡ እነዚህን ቀጥሎ ከየመጻህፍቱ አስረጅ በመውሰድ እናያለን፡፡

<u>የድምጽ መዋጥ</u>

በአማርኛ መነሻቸው ‹‹አ›› የሆኑ ቃላት ከፊታቸው ሌላ ተነባቢ ሲመጣ

ተነባቢው ወይም ቅጥያው ወደ ራብዕ ይለወጥና ‹‹አ›› ይዋጣል፡፡

ምሳሌ፡- አለፈ ከ + አለፈ = ካለፈ

የ + አለፈ = ያለፈ

በ + አለፈ = ባለፈ

ለ + አለፈ = ላለፈ

/7ኛ ክፍል፤ገጽ፣20/

በዚህ አስረጅ ውስጥ የተሰጠው ሰዋስዋዊ ገለጻና ምሳሌ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም በምሳሌው ላይ የምንመለከተው የተናባቢና የአናባቢ ክትትሎሽ ሳይሆን የአናባቢዎች ክትትሎሽ ነው። ክትትሎሹም ለምሳሌ ይህን ‹‹ክኧ-አልልፍኧ›› ይመስላል። ባየ(1987) እና ጌታሁን(1990) እንደሚገልጹት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በየትኛውም ቦታ የአናባቢዎች ክትትል አይፈቀድም። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም እንደ መፍትሔ ከሚታዩት አንዱ መግደፍ ነው። በዚህም መሰረት ‹‹ኧ›› ስትጎረድ/ስትገደፍ የ ‹‹ክ›› ድምጽ ከ ‹‹አ›› ጋር በሚኖራት ንክኪ ምክንያት ወደ ‹‹ካ›› ልትቀየር ችላለች። ‹‹አ››ም የተዋጠችው ‹‹ኧ›› በመጎረዷና ‹‹ክ›› ወደ ‹‹ካ›› በመቀየሯ ምክንያት ነው ማለት ነው። በመሆኑም ከላይ በአስረጅነት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ውስጥ የተሰጠው ገለጻና ምሳሌ ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይበት ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ወደ ተሳሳተ ግንዛቤ እንዲያመሩ የሚያደርግ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል። በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፤ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስህተት የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል።››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር አምስት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የአንድ መምህር/ት ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ሲሆን፤ የአንድ መምህር/ት ግን አዎንታዊ ሆኖ ይገኛል። ይሁን እንጂ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ የትክክለኛነት ችግር የሚታይበት ሰዋስዋዊ ገለጻ የለም።

<u>ጽሁፍን አሳጥሮና አስፋፍቶ መጻፍ</u>

1. የሚከተሉትን በአጽህሮተ- ጽሁፍ ጻፉ

ሀ. ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

ለ. የደቡብ ህዝቦች ልማት ማህበር

. . .

2. የሚከተሉትን በአጽህሮተ- ጽሁፍ የተጻፉትን አስፋፍታችሁ አንብቡ።

ሀ. ኢ.ሰ.መ.ጉ

ለ. ተ.መ.ድ

. . . /8ኛ ክፍል፤ገጽ፣206/

በርዕስ ጉዳዩ (ጽሁፍን አሳጥሮና አስፋፍቶ መጻፍ) መገለጽ የነበረበት ወይም ሊገለጽ የሚገባው ሃሳብ አንድን ጽሁፍ ዋና ይዘቱ ሳይለወጥ አሳጥሮ ወይም አስፋፍቶ ስለመጻፍ ሆኖ ሳለ፤ ከስሩ የቀረቡት መልመጃዎች ግን ከርዕስ ጉዳዩ ጋር አብረው የሚሄዱ ወይም የሚናበቡ ሆነው አይገኙም። ለምሳሌ፡- በጥያቄ ተራ ቁጥር 1 ‹‹የሚከተሉትን በአጽህሮተ-ጽሁፍ ጻፉ››፤በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 ደግሞ፣ ‹‹የሚከተሉትን በአጽህሮተ- ጽሁፍ የተጻፉትን አስፈፍታችሁ አንብቡ›› የሚሉና ከስራችው ከቀረቡት ጥያቄዎች ጋር አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ትዕዛዞች ሆነው እናገኛቸዋለን። የመልመጃው ጥያቄዎች በዋነኝነት የሚያተኩሩት በምህጻረ ቃላት አመሰራረት ሁኔታ ላይ ነው። ምህጻረ ቃል ቃልን ወይም ቃላትን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም አሳጥሮ የመጻፍ ስልት ሲሆን፤ አጽህሮተ-ጽሁፍ ግን አንድን ጽሁፍ ሃሳቡ ሳይቀየር ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦችን በአንድ ሦስተኛ ያህል አሳጥሮ መጻፍ ነው። በመሆኑም በአስረጁ የቀረበው ርዕስ ጉዳይም ሆነ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ውስጥ ያሉት አጠቃቀሞች የመልመጃ ጥያቄዎቹን በትክክል የሚገልጹ አይደሉም። የመልመጃ ጥያቄዎቹን በትክክል ሊገልጻቸው የሚችለው ርዕስ ‹‹ምህጻረ ቃላት›› ነው፤ ወይም ሊሆን ይገባዋል።

የዚህ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዷ፣ *‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው? ለምሳሌ ከትክክለኛነታቸው አንጻር ያላቸውን ሁኔታ ቢገልጹልኝ።››* በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ *‹‹ያቀረብናቸውን ይዘቶች ከትክክለኛነታቸው አኳያ ሳያቸው ያደረግነው ጥረት ከሞላ ጎደልም ቢሆን የተሳካ ይመስለኛል። ያን ያህል የጎላ ችግር ያለባቸው አይመስለኝም።››* የሚል ሆኖ ይገኛል።በተደረገው ምልከታም ማረጋገጥ የተቻለው ከላይ በአስረጅነት ከቀረበው ውጭ የትክክለኛነት ችግር የሚታይበት ሰዋስዋዊ ገለጻ እንደሌለ ነው።

## 4.2.3 ከተመጣጣኝነት/ሚዛናዊነት አንጻር

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከታላሚው ቋንቋ የስነ-ድምጽ፣ የስነ-ምዕላድ፣ የስነ-አገባብና የስነ-ፍች ሰዋስዋዊ ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ተውጣጥተው የቀረቡ መሆን እንዳለባቸው በክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ ተሞክሯል። በእርግጥ እንደ ቋንቋው ተማሪዎች አይነት (አፍ-ፈት፣የሁለተኛ

ቋንቋ ተማሪ)፣ የክፍልና የእውቀት ደረጃ፣ ፍላጎት፣ የቋንቋው ትምህርት አላማ፣ ወዘተ እንደ አስፈላጊነቱ ለአንዳንድ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ከሌሎቹ በበለጠ ትኩረት መስጠት ይቻላል። ሆኖም በተቻለ መጠን ይዘቶቹ ሁሉንም የሰዋስው ክፍሎች የሚዳስሱ እንዲሆኑና በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች (በገለጻዎች፣በምሳሌዎች፣በመልመጃዎች፣ወዘተ) መቅረብ እንዳለባቸው ይመከራል። ከዚህ ንድፈ ሀሳብ አንጻር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ምን አይነት ገጽታ እንዳላቸው በማስከተል ለመፈተሽ ይሞከራል። በቅድሚያ ግን ስለ መማሪያ መጻህፍቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ስርጭት ሁኔታ የሚገልጽ አንድ አጠቃላይ ሰንጠረዥ ቀጥሎ ይቀርባል።

**ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የስርጭት ሁኔታ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የቀረቡበት የክፍል ደረጃና የድግግሞሽ መጠን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ስነ-ደምጽ | 4 | 4.9 | 3 | 4.1 | 6 | 6.5 | 11 | 8.9 |
| 2 | ስነ-ምዕላድ | 25 | 30.5 | 28 | 40 | 20 | 21.5 | 44 | 35.5 |
| 3 | ስነ-አገባብ | 30 | 36.6 | 16 | 22.9 | 28 | 30.1 | 37 | 29.8 |
| 4 | ስነ-ፍች | 23 | 28.1 | 23 | 32.9 | 39 | 41.9 | 32 | 25.8 |
| | ጠቅላላ ድምር | 82 | 100 | 70 | 100 | 93 | 100 | 124 | 100 |

የአምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አራቱንም የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች አካቶ ይዟል። በመጽሐፉ ውስጥ ከስነ-ድምጽ፣ከስነ-ምዕላድ፣ከስነ-አገባብና ከስነ-ፍች የተውጣጡ ይዘቶች ይገኛሉ። ሆኖም ይዘቶቹ በሰንጠረዥ ዘጠኝ ላይ በግልጽ እንደሚታየው የመጠን ወይም የስርጭት ልዩነት ይታይባቸዋል። በመጽሐፉ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነ-አገባብ ሲሆን 36.6% ሽፋን አግኝቷል። በቅደም ተከተል ሲታይ ስነ-ምዕላድ 30.5%፣ ስነ-ፍች 28.1%፣ ስነ-ድምጽ ደግሞ 4.9% ሽፋን አግኝተዋል። ስነ-ድምጽ ከሁሉም እጅግ ዝቅተኛ ሽፋን ወይም ትኩረት እንደተሰጠው መገንዘብ ይቻላል። ከአቀራረብ አንጻር ስንመለከት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በገለጻ፣ በምሳሌዎችና በመልመጃ መልክ ቀርበዋል። መልመጃዎችም በእውነት ሐሰት፣ በምርጫ፣ በአዛምድ፣ ክፍት ቦታ በመሙላት፣ ሰንጠረዥ በማሟላት፣ የተዘበራረቁትን በማስተካከል፣ በጽሁፍ በመመለስ፣ በውይይት ቀርበዋል። ይህም በመጽሀፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልቶች ለማቅረብ ጥረት የተደረገ መሆኑን ያሳያል። በዚህ ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ የተውጣጡ ናቸው።››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር ስምንት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የሁለቱም መምህራን አሉታዊ ነው። ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ልዩ ልዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝ ድርሻ እንዳልተሰጣቸው የሚያስረዳ ሲሆን፤ በምልከታው ማስተዋል የተቻለውም ይህንኑ ነው።

በስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ዝቅተኛ ድርሻ የተሰጠው ስነ-ድምጽ ነው። 4.1% ብቻ ሽፋን አግኝቷል። በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነ-ምዕላድ ሲሆን፤ ይህም ከአጠቃላዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 40%ቱን ሸፍኗል። ስነ-ፍች 32.9%፣ ስነ-አገባብ ደግሞ 29.9% ሽፋን በቅደም ተከተል አግኝተዋል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ አቀራረብ ሲፈተሽ ከአምስተኛ ክፍሉ ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል። ይኸውም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በገለጻ፣ በምሳሌዎች፣ በሰንጠረዥና በመልመጃ መልክ የቀረቡ ሲሆን፤ መልመጃዎች ደግሞ በእውነት ሐሰት፣ በምርጫ፣ በአዛምድ፣ ክፍት ቦታ በመሙላት፣ የተዘበራረቁትን በማስተካከል፣ በጽሁፍ፣ በውይይት፣መልክ ተዘጋጅተው ቀርበዋል። በአጠቃላይ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቆሙትን ልዩ ልዩ የማቅረቢያ ስልቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለመተግበር ጥረት ተደርጓል። ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር ስምንት እንደሚያሳየው፣ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው*

*ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ የቀረቡ ናቸው፡፡››* በማለት ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ የአንድ መምህር/ት ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ሲሆን፤ የአንድ መምህር/ት ደግሞ አሉታዊ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝ ወይም ሚዛናዊ ሽፋን እንዳልተሰጣቸው ሲሆን፤ በምልከታውም ውጤት የታየው ይኸው ነው፡፡

በሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ ከፍተኛ ሽፋን ይዞ የምናገኘው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ስነ-ፍች ሲሆን፤ ይኸውም ከጠቅላላው 41.9% ነው፡፡ በቅደም ተከተል ሲታይ ስነ-አገባብ 30.1%፣ ስነ-ምዕላድ 21.5% እና ስነ-ድምጽ 6.5% ሽፋን እንደተሰጣቸው ከሰንጠረዥ ዘጠኝ መረዳት ይቻላል፡፡ አሃዛዊ መግለጫው እንደሚያመለክተው በሰዋስው የትምህርት ይዘት ክፍሎች መካከል የተመጣጠነ ሽፋን አይታይም፡፡ በተለይም ደግሞ ቀደም እንዳሉት የክፍል ደረጃዎች ሁሉ ስነ-ድምጽ በዚህ የክፍል ደረጃም ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ሲታይ ግን የጎላ ችግር ይታይበታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይኸውም ቀደም እንዳሉት የመማሪያ መጻህፍት ሁሉ በዚህም የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹን በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች ለማቅረብ ጥረት እንደተደረገ በመጽሐፉ ውስጥ ያላቸው አቀራረብ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህም ማለት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ የደረጃው መርሃ ትምህርት በሚጠቁመው መሰረት በገለጻ፣ ምሳሌዎችን በማቅረብ፣ በመልመጃ፣መልክ ወይም ስልቶች ቀርበው ይገኛሉ፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ የተውጣጡ ናቸው፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር ስምንት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለቱም አሉታዊ ምላሽ ነው የሰጡት፡፡ ይህም ማለት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝ ወይም ሚዛናዊ ሽፋን የላቸውም፡፡

በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከፍተኛ ሽፋን ተሰጥቶት የምናገኘው ሰዋስዋዊ ይዘት ስነ-ምዕላድ ነው፡፡ ከአጠቃላይ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ሽፋን ውስጥ 35.5% የሚሆነውን ድርሻ ይዟል፡፡ ስነ-አገባብ 29.8%፣ ስነ-ፍች 25.8% እና ስነ-ድምጽ 8.9% ድርሻ እንዳላቸው ከሰንጠረዥ ዘጠኝ መረዳት ይቻላል፡፡ ከሌሎቹ የሰዋስው ክፍሎች ሽፋን አኳያ ሲታይ በዚህም የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለስነ-ድምጽ ዝቅተኛ ትኩረት ወይም ሽፋን ነው የተሰጠው፡፡ በሁሉም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የታየ የወል ችግር ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በአጠቃላይ ሲታይ በዚህ ጥናት ተተኳሪ መጻህፍት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ወይም ትኩረት የተሰጠው ሰዋስዋዊ ክፍል ከመጽሐፍ መጽሐፍ ይለያይ እንጂ በሁሉም ውስጥ ዝቅተኛ ሽፋን ወይም ትኩረት የተሰጠው ለስነ-ድምጽ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም አጠቃላይ ተተኳሪ መጻህፍቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አመጣጥነው ከማቅረብ አኳያ የጋራ የሆነ ችግር እንዳለባቸው ያሳያል፡፡

በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀደም እንዳሉት የክፍል ደረጃዎች ሁሉ በገለጻ/ማብራሪያ፣ ምሳሌዎችን በማቅረብና በመልመጃዎች መልክ የቀረቡ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በልዩ ልዩ ስልቶች ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን መጠቀሙ ደግሞ ለተለያዩ ይዘቶች ተገቢ የሆነውን የማቅረቢያ ስልት/ዘዴ ከመጠቀሙ ወይም ከማሳወቁም በላይ አጠቃላይ ትምህርቱ ለተማሪዎች አሰልቺ እንዳይሆን በማስቻል ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ የተውጣጡ ናቸው፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር ስምንት) በማለት ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለቱም መምህራን የሰጡት ምላሽ አሉታዊ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎችን በተመጣጠነ ወይም ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለማቅረብ ጥረት አለመደረጉን ነው፡፡ ምልከታው ወይም ሰንጠረዥ ዘጠኝ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

### 4.2.4 ከተገቢነት አንጻር

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት አላቸው የሚባለው፡- ከተማሪዎች ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ የቀደመ እውቀት፣ ፍላጎት፣ወዘተ ጋር የሚጣጣሙ ሲሆኑ፤ የደረጃውን የቋንቋ ትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሲሆኑ፤ እንዲሁም ተማሪዎች ቋንቋውን በመጠቀም ረገድ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ሰዋስዋዊ ችግሮችን ለመፍታት እንዲያስችላቸው በየደረጃው ሊማሯቸው የሚገቡ ሲሆኑና በየደረጃው የተዘጋጁትን መርሃ ትምህርቶች መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ ተገቢነት አላቸው። ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ምን አይነት ገጽታ እንዳላቸው ቀጥሎ የእያንዳንዳቸውን በቅደም ተከተል እናያለን።

በአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ውስብስብና ከተማሪዎች የመስራት አቅም በላይ የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተዋል ለማለት አይቻልም። በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ገለጻዎች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች አልፎ አልፎ ከሚታይባቸው የግልጽነት ችግር በስተቀር ተማሪዎች በቀላሉ አንብበው ሊረዷቸውና ሊሰሯቸው የሚችሏቸው ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታዬ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው።››* (ሰንጠረዥ ስምንት፣ መጠይቅ ቁጥር ስድስት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ 48% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከመስራት ወይም ከመገንዘብ ችሎታቸው ጋር ተመጣጣኝ መሆናቸውን ገልጸዋል።ይሁን እንጂ ሰንጠረዥ ስምንት እንደሚያሳየው 14% ተማሪዎች ለመወሰን ተቸግረዋል፤እንዲሁም 38% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከመስራት ወይም ከመገንዘብ ችሎታቸው ጋር እንደማይመጣጠኑ ይገልጻሉ። ይህም የሚያመለክተው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ተገቢነት ፍጹም እንከን የለሽ አለመሆኑን ነው። በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ካሉት አስራ አምስት ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካል አስራ አራቱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተዋል። ይሁን እንጂ የመማሪያ መጽሐፉ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የማይታዩ ሰባት ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በተጨማሪነት አካቶ ይዞ ይገኛል፤ (ዝርዝሩን በ4.4 ላይ ይመልከቱ)። ይህም

ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ያለባቸውን የተገቢነት ችግር የሚጠቁም ነው።

በአምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካተው የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለደረጃው በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ውስጥ ከተነደፉላቸው የቋንቋ ትምህርት አለማዎችና ተማሪዎች ሊማሯቸው የሚገቡ ከመሆናቸው አንጻር ስንመለከታቸው ስነ-አገባብ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እናገኛለን። እንዲሁም ስነ-ምዕላድና ስነ-ፍች በቅደም ተከተል የተሻለ ትኩረት ተሰጥቷቸው ይታያል። ይሁን እንጂ ስነ-ድምጽ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶትና ተካቶ እያለ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ግን የተሰጠው ሽፋን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ ልዩ ልዩ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ሁሉ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸውና ተመጣጥነው በመቅረብ ተማሪዎች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ደጋግመው ሊለማመዷቸው በሚያስችላቸው መልኩ ተሰራጭተው ሊገኙ ይገባል። ከዚህም በመነሳት መጽሐፉ በደረጃው የተነደፉትን የሰዋስው ትምህርት አላማዎች ከግብ ከማድረስ አንጻር ድክመት እንዳለበትና ተማሪዎች ሊማሯቸው የሚገቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ሚዛናዊ የሆነ ትኩረት በመስጠት እንዳላቀረበ መገንዘብ ይቻላል። ይህም በአጠቃላይ የሚያመለክተው የመማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ፍትሃዊ ስርጭት ባለው መልኩ ከማቅረብ አንጻር የተገቢነት ችግር ወይም ድክመት ያለበት መሆኑን ነው።

በስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካተው የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ አይደሉም ማለት ይቻላል። ተማሪዎች በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሰዋስዋዊ ገለጻዎችና ምሳሌዎች ለመረዳትም ሆነ መልመጃዎችን ለመስራት የሚዳግታቸው ወይም ያን ያህል ከበድ ያለ ችግር የሚያጋጥማቸው መስሎ አይታይም። ከደረጃው ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽም የሚጠናክረው ይህንኑ ሀሳብ ነው። ሰንጠረዥ ስምንት፣ መጠይቅ ቁጥር ስድስት እንደሚያሳየው በዚህ ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታዬ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው።››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ምንም እንኳ የ36% ተማሪዎች አሉታዊ፣ የ13% ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን ያስቸግረኛል

የሚል ቢሆንም፤አብላጫዎቹ ወይም 51% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተማሪዎቹ የመገንዘብና የመስራት ችሎታ ጋር ተመጣጣኝነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎችም ቢሆኑ ድምጻቸው ሊዋጥ አይገባውምና ከነሱ ምላሽ አንጻር ሲታይ የመማሪያ መጽሐፉ ያካተታቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ፍጹም እንከን የለሽ ናቸው ለማለት አይቻልም፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ሰዋስዋዊ ይዘት አኳያ ሲታዩ ከተወሰኑ ይዘቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በ ‹‹4.4›› ላይ በዝርዝር ለማሳየት እንደተሞከረው ጥቂት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቢሆኑም መርሃ ትምህርቱን መሰረት ሳያደርጉ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ብቻ ተካተው መገኘታቸው ተገቢ አይደለም፤ ከመርሃ ትምህርቱ አፈንግጠዋልና፡፡

እንዲሁም በሰንጠረዥ ዘጠኝ ላይ እንደሚታየው ስነ-ምዕላድና ስነ-ፍች ከአጠቃላዩ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ውስጥ 72.9% ሽፋን ተሰጧቸው እናገኛለን፡፡ በአንጻሩ ስነ-አገባብና ስነ-ድምጽ ደግሞ 27% ብቻ ድርሻ ይዘዋል፡፡ስነ-ድምጽ ከሁሉም ይዘቶች በጣም ዝቅተኛ የሆነ ሽፋን እንደተሰጠው ሰንጠረዡ ያሳያል፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት የመማሪያ መጽሐፉ በደረጃው የተነደፉትን የቋንቋ ትምህርት አላማዎች ከግብ ከማድረስ አንጻርና ተማሪዎች እንዲማሯቸው የሚጠበቁ ይዘቶችን በበቂና በተመጣጣኝ ሁኔታ ከማቅረብ አኳያ ሲታይ ድክመት ወይም የተገቢነት ጥያቄ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

በሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ ሆነው የሚታዩ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው ከሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ ጥቂት ይዘቶች አንደኛ፣ ከአምስተኛና ከስድስተኛ ክፍል ጀምሮ ቀጣይነታቸውን ወይም ተለጣጣቂነታቸውን ሳይጠብቁ፤ ሁለተኛ ደግሞ በደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት ሳያደርጉ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ብቻ

ታይተዋል(በ4.4 ላይ ቀርቧል)፡፡በዚህ ላይ እነዚህ ይዘቶች ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለአብነት የሚከተለውን ከመጽሐፉ የተወሰደ አስረጅ እንመልከት፡፡

4. በምሳሌው መሰረት ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት
የድምጽ ውህደቱን ለይታችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. አዘገነ   አስ + ዘገነ

ለ. አሰማ   አስ + ሰማ

4.1 አሰለፈ
4.2 አሳበደ
. . .  /7ኛ ክፍል፣ገጽ፣20/

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ይዘት አንደኛ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንጂ በደረጃው መርሃ ትምህርት ውስጥ ተካቶ አይታይም፡፡ ሁለተኛ፣ በአምስተኛም ሆነ በስድስተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ይህን መሰል ይዘት አይገኝም፡፡ በመሆኑም ይህ ይዘት ከታች ባሉት የክፍል ደረጃዎች ምንም አይነት መነሻ መሰረት ሳይኖረው ወይም ቀጣይነትንና ተለጣጣቂነትን ሳይጠብቅ በዚህ የክፍል ደረጃ ለዚያውም በደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት ሳያደርግ መቅረቡ ተገቢነቱን አጠያያቂ አድርጎታል፡፡

ሰንጠረዥ ስምንት፣ መጠይቅ ቁጥር ስድስት እንደሚያሳየው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣‹‹*በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታዬ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡*›› በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ 56% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከመስራት ወይም ከመገንዘብ ችሎታቸው ጋር ተመጣጣኝ መሆናቸውን ቢገልጹም፤ በአንጻሩ ደግሞ 8% ተማሪዎች ለመወሰን ተቸግረናል በማለት፣ 36% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታቸው ጋር እንደማይመጣጠኑ ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተገቢነት ችግር እንደሚታይባቸው ያመላክታል፡፡ ሌላው ደግሞ ሰንጠረዥ ዘጠኝ እንደሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች (ስነ-ድምጽ፣ ስነ-ምዕላድ፣ ስነ-አገባብና ስነ-ፍች) ተመጣጣኝ ስርጭት ወይም ሽፋን አይታይባቸውም፡፡ በተለይም

ደግሞ ለስነ-ድምጽ ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት የዚህ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍም ችግር ሆኗል። ይህም መጽሐፉ በደረጃው የተነደፉ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን ከግብ ከማድረስና ተገቢ ወይም ፍትሐዊ ስርጭት ያላቸውን ሰዋስዋዊ ክፍሎች ለተማሪዎች ከማቅረብ አኳያ ሲፈተሽ ቀደም እንዳሉት የመማሪያ መጻህፍት ሁሉ ከድክመት ወይም ከተገቢነት ችግር የጸዳ እንዳይሆን አድርጎታል።

በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከጥቂት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በስተቀር የአብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ገለጻዎች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ሲጤኑ ከተማሪዎች የመገንዘብና የመስራት ችሎታ ጋር የሚመጣጠኑ ናቸው ለማለት ያስደፍራል። ይሁን እንጂ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የደረጃውን መርሃ ትምህርት መሰረት ያላደረጉ (በ4.4 ላይ ቀርቧል) የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ይገኛሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን ቀደም ባሉት የመማሪያ መጻህፍትም ውስጥ ምንም ቀጣይነትና ተለጣጣቂነት የላቸውም። ለምሳሌ ከስነ-ድምጽ ስለ ድምጽ መገደፍ ወይም መጎረድና ስለጥብቀት (ገጽ፣60) ላይ የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምንም አይነት መርሃ ትምህርታዊ መሰረት የላቸውም፤ ቀጣይነትንና ተለጣጣቂነትን ጠብቀው የመጡ ወይም የቀረቡም አይደሉም። የደረጃውን መርሃ ትምህርት ስናይ ስነ-ድምጽ በሚለው ሰዋስዋዊ ይዘት ስር አቅርቦ የምናገኘው በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላትን የተመለከተ ብቻ ነው። በመሆኑም ይህን መሰል ይዘቶች ተማሪዎችን ግር ማሰኘታቸውና መፈታተናቸው አይቀርም።

ሰንጠረዥ ስምንት፣መጠይቅ ቁጥር ስድስት እንደሚያመለክተው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታዬ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው።››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ 52% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታቸው ጋር ተመጣጣኝ እንደሆኑ ቢገልጹም፣13% ተማሪዎች ለመወሰን መቸገራቸውን ያመለከቱ ሲሆን፣ 35% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች የመገንዘብ ወይም የመስራት አቅማቸውን እንደሚፈታተኑ ያስገነዝባሉ።

ሰንጠረዥ ዘጠኝ እንደሚያሳየው የመማሪያ መጽሐፉ ልዩ ልዩ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎችን (ስነ-ድምጽ፣ ስነ-ምዕላድ፣ስነ-አገባብና ስነ-ፍች) በተመጣጣኝ ወይም ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የማቅረብ ችግርም ተስተውሎበታል። በመሆኑም የመማሪያ መጽሐፉ በደረጃው መርሃ ትምህርት ውስጥ የተነደፉትን የሰዋስው ወይም የቋንቋ ትምህርት አላማዎች ከግብ ከማድረስ አንጻርና ተማሪዎች እንደሚሯቸው የሚጠበቁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ሚዛናዊ ወይም ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ከማቅረብ አኳያ ሲታይ ቀደም እንዳሉት የመማሪያ መጻህፍት ሁሉ ድክመት ይታይበታል።

የዚህ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዷ፣*‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው? ለምሳሌ ከተገቢነት አኳያ?››* በሚል ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ *‹‹ይዘቶቹ የተገቢነት ችግር አለባቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ትምህርቱን የሚጀምሩት ከ3ኛ ክፍል ነው፤ሁለተኛ ቋንቋቸው ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያቀረብናቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለተማሪዎቹ የሚመጥኑ አይመስለኝም። የመጽሐፉን አዘገጃጀት አሁን ላይ ሆኜ ሳየው ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አዘገጃጀት ብዙም የተለየ ሁኔታ ያለው አይደለም።››* የሚል ሆኖ ይገኛል።

## 4.3 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው አደረጃጀት በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለባቸው፣ የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት፣ እንዴት ባለ መንገድ ተደጋግመውና ጥልቀት እየጨመሩ መቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል። በዚህ ጥናት ውስጥም በዋነኛነት ተከታታይነት፣ ቀጣይነት/ ተለጣጣቂነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሉት የአደረጃጀት መርሆዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚታዩ ይሆናል።

### 4.3.1 ከተከታታይነት አንጻር

ተከታታይነት ለአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል ደረጃ በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው መቅረብ እንዳለባቸውና ድግግሞሻቸውም ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹን በሚገባ እንዲረዷቸው፣ እንዲካኗቸውና በተገቢ ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያውሏቸው ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ምን አይነት ገጽታ እንዳላቸው በማስከተል እናያለን፡፡ በቅድሚያ ግን በአራቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችንና የድግግሞሽ መጠን የሚያሳይ አንድ አጠቃላይ ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

## ሰንጠረዥ አስር፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የድግግሞሽ መጠን

| በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ይዘቶቹ የቀረቡበት የክፍል ደረጃና የድግግሞሽ መጠን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | |
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| **ስነ- ድምጽ** | | | | | | | | |
| - በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት | 4 | 4.9 | 3 | 4.3 | 3 | 3.2 | 7 | 5.6 |
| - ድምጸ-ልሳናዊ ሂደት | - | - | - | - | 3 | 3.2 | 4 | 3.2 |
| **ስነ- ምዕላድ** | | | | | | | | |
| - ጥገኛ ምዕላዶች/ቅድመ፣ ድህረና ውስጠ አምድ ቅጥያዎች | 4 | 4.9 | 3 | 4.3 | 2 | 2.2 | 11 | 8.9 |
| - የቃላት እርባታ | 4 | 4.9 | 1 | 1.4 | 2 | 2.2 | 5 | 4 |
| - የቃላት ምስረታ | 4 | 4.9 | 4 | 5.7 | 6 | 6.5 | 5 | 4 |
| - ስም | 4 | 4.9 | 5 | 7.1 | 2 | 2.2 | 4 | 3.2 |
| - ግስ | 2 | 2.4 | 4 | 5.7 | 1 | 1.1 | 4 | 3.2 |
| - ቅጽል | - | - | - | - | 1 | 1.1 | 5 | 4 |
| - ተውሳከ ግስ | - | - | - | - | - | - | 1 | 0.8 |
| - መስተዋድድ | - | - | - | - | - | - | 1 | 0.8 |
| - የስም ገላጮች | 4 | 4.9 | 5 | 7.1 | 3 | 3.2 | 4 | 3.2 |
| - የግስ/የማሰሪያ አንቀጽ ገላጮች | 3 | 3.7 | 4 | 5.7 | 3 | 3.2 | 4 | 3.2 |
| **ስነ- አገባብ** | | | | | | | | |
| -የአያያዥ ቃላት/ሐረጋት አጠቃቀም | 3 | 3.7 | 4 | 5.7 | 2 | 2.2 | 5 | 4 |
| - የሐረግ ምስረታ | 4 | 4.9 | 3 | 4.3 | 3 | 3.2 | 4 | 3.2 |
| - የአረፍተ ነገር ምስረታ | 5 | 6.1 | 2 | 2.9 | 20 | 21.5 | 17 | 13.7 |
| -የተጓደሉ አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላት | 9 | 11 | 4 | 5.7 | 1 | 1.1 | 7 | 5.6 |
| -የተዘበራረቁ ቃላትን በቅደም ተከተል በማሰለፍ ትክክለኛ አረፍተ ነገር መገንባት | 4 | 4.9 | 1 | 1.4 | 2 | 2.2 | 2 | 1.6 |
| - ሰዋስዋዊ ግድፈት ያለባቸውን አረፍተ ነገሮች አቃንቶ መጻፍ | 3 | 3.7 | 2 | 2.9 | - | - | 3 | 2.4 |
| - የተዘበራረቁ ቃላትን ቅደም ተከተል ማስያዝ | 2 | 2.4 | - | - | - | - | - | - |
| **ስነ- ፍች** | | | | | | | | |
| - የቅጥያዎች/ የአጻፋዎች ፍች | - | - | - | - | - | - | 2 | 1.6 |
| - የቃላት ተመሳሳይ ፍች | 9 | 11 | 6 | 8.6 | 11 | 11.8 | 10 | 8.1 |
| - የቃላት ተቃራኒ ፍች | 3 | 3.7 | 4 | 5.7 | 3 | 3.2 | 5 | 4 |
| -የቃላትቀጥተኛ (እማሬያዊ/መዝገበ ቃላዊ) ፍች | 2 | 2.4 | 1 | 1.4 | 2 | 2.2 | 1 | 0.8 |
| - የቃላት ፍካሬያዊ ፍች | - | - | - | - | - | - | 1 | 0.8 |
| - የቃላት አውዳዊ/ አገባባዊ ፍች | 6 | 7.3 | 7 | 10 | 14 | 15.1 | 10 | 8.1 |
| - የሐረጋት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች | 1 | 1.2 | 4 | 5.7 | 8 | 8.6 | 2 | 1.6 |
| - የአረፍተ ነገር አውዳዊ/ አገባባዊ ፍች | 2 | 2.4 | 1 | 1.4 | 1 | 1.1 | - | - |
| - የአንድን አረፍተ ነገር ሀሳብ በሌሎች አባባሎች መግለጽ | - | - | - | - | - | - | 1 | 0.8 |
| **ጠቅላላ ድምር** | 82 | 100 | 70 | 100 | 93 | 100 | 124 | 100 |

### ሀ. የአምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በአምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከስነ- አገባብ ውስጥ የተጓደሉ አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላት የሚለውና ከስነ-ፍች ውስጥ ደግሞ የቃላት ተመሳሳይ ፍች ነው፡፡ እነዚህ ይዘቶች እያንዳንዳቸው በመጽሐፉ ውስጥ ዘጠኝ ዘጠኝ ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን ይህም ከጠቅላላው 22% መሆኑ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበው የቃላት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች ሲሆን፤ ይህም ከጠቅላላው 7.3% ሽፋን ይዟል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ በመጽሐፉ ውስጥ አምስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት የአረፍተ ነገር ምስረታ ሲሆን፤ ይህም ከአጠቃላዩ ይዘቶች ውስጥ ያለው ሽፋን 6.1% ነው፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ሃያ አንድ ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ አስራ ሰባቱ ወይም ከግማሽ በላይ የሆኑት ይዘቶች ከፍተኛው ከቀረበበት የድግግሞሽ መጠን ግማሽ በታች (አራት ጊዜና ከዛ በታች) ብቻ ተደጋግመው የቀረቡ ሆነው ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም አንድ ይዘት (የሐረጋት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች) በመጽሐፉ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርቧል፡፡ ከዚህም በመነሳት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተከታታይነት ድክመት ይታይባቸዋል ለማለት ያስደፍራል፡፡

ከፍተኛ ድግግሞሽ ባላቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶችና ዝቅተኛ ድግግሞሽ ባላቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ያለው የድግግሞሽ መጠን ልዩነት ሰፊ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሁሉም ይዘቶች እኩል የድግግሞሽ መጠን ይኑራቸው ብሎ ማሰብ ባይቻልም በበቂ ሁኔታ ተደጋግመው ያልቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መኖራቸውን ከሰንጠረዥ አስር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹን በተደጋጋሚ እንዳይለማመዷቸውና በሚገባ እንዳይካኗቸው ያደርጋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ ወይም እየጨመሩ ቀርበዋል ወይስ አልቀረቡም የሚለውን ሁኔታ ለማጤን ይቻል ዘንድ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ከመጽሐፉ በአስረጅነት የተወሰዱ

ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንመልከት፡፡

1. በምሳሌው መሰረት መነሻና መድረሻ ቅጥዎችን እየለየን

   በመጻፍ ዋናውን ቃል ለመምህራችን እናሳያለን፡፡

   ምሳሌ:- የሰውን    የ = መነሻ ቅጥያ

   - ን = መድረሻ ቅጥያ

   ሰው = ዋናው ቃል

   1.1በሽታን

   1.2ከሰለቸው

. . . /5ኛ ክፍል፤ገጽ፣22/

ሐ. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ዋናውን ቃል/ ስርው-ቃሉን፣

   መነሻ ቅጥያውንና መድረሻ ቅጥያውን እየለየን እንጽፋለን፡፡

| ምሳሌ:- ስርው-ቃል | | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| ሰለበላች | በላ | ስለ- | -ች |

1. ስለመጣን
2. ከብድር

. . . /5ኛ ክፍል፤ገጽ፣26/

በአስረጅነት ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘት መልመጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በይዘቶቹ መካከል ከአቀራረብም ሆነ ከክብደት አንጻር ልዩነት ይታይባቸዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ ሌሎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችም ቢሆኑ በተለያዩ ገጾች ወይም ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ከመቅረባቸው በስተቀር እየጠጠሩ ወይም ከበድ እያሉ የመሄድ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ ስለዚህም ይህን ሁኔታ ሳይጠብቁ ይዘቶቹን ዝም ብሎ መደጋገሙ ተማሪዎችን ከሚያሰለች በስተቀር ፋይዳ ያለው ሊሆን አይችልም፡፡ ይህን አስመልክቶ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ጨምረዋል፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር አስር) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለቱም መምህራን የሰጡት ምላሽ ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህ የመምህራኑ ምላሽ አጠራጣሪ ሁኔታን የሚያመላክት ስለሆነ፤ በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ይሄዳሉ ለማለት የማያስደፍር ሲሆን፤ ይህም ሀሳብ በምልከታው የተደረሰበትን ድምዳሜ የሚያጠናክር ነው፡፡

ለ. የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ

በስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሃያ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከፍ ባለ ሁኔታ ተደጋግመው የቀረቡት የቃላት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች ሰባት ጊዜ፣የቃላት ተመሳሳይ ፍች ስድስት ጊዜ እና ከቃል ክፍሎች ስምና ከስነ-ምዕላድ የስም ገላጮች እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ጊዜ ሆነው፤እነዚህ ከአጠቃላዩ ውስጥ 33.4% ሽፋን ይዘዋል፡፡ ከቀሪዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ ሰባት ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እያንዳንዳቸው አራት አራት ጊዜ የተደጋገሙ ሲሆን፤ እነዚህ ደግሞ ከአጠቃላዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ 39.9%ቱን ይሸፍናሉ፡፡ ሶስት የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ደግሞ እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ጊዜ የተደጋገሙ ሲሆን፤ ከአጠቃላዩ ውስጥ 12.9% ድርሻ አላቸው፡፡ እንዲሁም ሁለት ሰዋስዋዊ ይዘቶች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ ብቻ፤ አራት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ጊዜ ብቻ እንደቀረቡ ከሰንጠረዥ አስር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ተደጋግመው ያልቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን ያሳያል፡፡

የዚህ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት አንዱ፣*‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው? ለምሳሌ ከተከታታይነት አኳያ?››* በሚል ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣*‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ተከታታይነት ጠብቀናል ብዬ ልልህ አልችልም፡፡ ደረጃ በደረጃም እያሳደግናቸው የሄድን አይመስለኝም፡፡ ይህንን ሁኔታ ከኔ ጋር አብሮ ያዘጋጀውን ሰው ካገኘኸው ሊያረጋግጥልህ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ተከታታይነትን በተመለከተ ሀሳቡም አልነበረንም፡፡››* የሚል ነው፡፡ ስለዚህም በመጽሐፉ አዘጋጆች አዕምሮ ውስጥ ያልነበረ ሀሳብ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይተገበራል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይመስላል፡፡

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቢሆኑ ከገጽ ገጽ ወይም ከምዕራፍ ምዕራፍ ስፋትና ጥልቀት ወይም ክብደት እየጨመሩ ከመሄድ አንጻር ሲፈተሹ ድክመት የሚስተዋልባቸው ሆነው የሚገኙ ናቸው፡፡ በአስረጅነት የሚከተሉትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንመልከት፡፡

ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን

ቃላት ትርጉም ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ሰውዬው ስዕል ሳለ፡፡/ስዕል ሰራ/

2. ልጅቷ ለሽንኩርት መክተፊያ ቢለዋውን ሳለች፡፡/ሞረደች/

3. ጓደኛዬ ጎንፋን ስለያዘው ሳለ፡፡/ ጎሮሮውን አጠራ/

1. ወይዘሮ ጀንበር በቃላቸው የማይጠኑ አባይ ሰው ናቸው፡፡

2. አባይ ለሙን አፈራችንን ለግብጽ ይሰጣል፡፡

. . .

(በቃላቱ ላይ አልተሰመረም፡፡ ስህተት ከምንጩ)

/6ኛ ክፍል፤ገጽ፣27/

ሀ. የተሰመረባቸው ቃላት ሊኖራቸው የሚችለውን ትርጉም

ስሩና በቡድን ተወያዩ፡፡

1. በሬው ሰባ፡፡ ____________

2. በሬው ሰባ ብር ተሸጠ፡፡ ____________

. . . /6ኛ ክፍል፤ገጽ፣34/

በቀረቡት ሁለቱም አስረጀች ውስጥ መመልከት እንደሚቻለው ተማሪዎች የሚጠብቅና የሚላላ ድምጽ ያላቸው ቃላት የገቡባቸውን አረፍተ ነገሮች በማየት የቃላቱን ትርጉም እንዲጽፉ/ሰርተው በቡድን እንዲወያዩ የሚያዙ ናቸው፡፡ በአቀራረብ ረገድ ያየን እንደሆነ የመጀመሪያው ምሳሌ ማካተቱ፤ ሁለተኛው ደግሞ ምሳሌ የሌለው ከመሆኑ በስተቀር ምንም አይነት የይዘት ስፋትና ጥልቀት ወይም ደግሞ ክብደት እየጨመሩ የመሄድ ሁኔታ ይታይባቸዋል ለማለት አያስችልም፡፡ ተማሪዎች በሁለቱም መልመጃዎች ውስጥ ያሉት ቃላት የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾች ያሏቸው መሆናቸውን በማጤን ወይም ደግሞ ከአገባባቸው/ ከአውዱ ሊኖራቸው የሚችለውን ትርጉም በመገንዘብ መልመጃዎቹን ምንም ሳይቸገሩ ሊሰሯቸው እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፣መጠይቅ ቁጥር አስር እንደሚያሳየው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ጨምረዋል፡፡››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ የአንድ መምህር/ት ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ሲሆን፤ የአንድ መምህር/ት ደግሞ አሉታዊ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም

የሚያስገነዝበው በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ይሔዳሉ ለማለት እንደማያስችል ነው።

**ሐ. የሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

በሰንጠረዥ አስር ላይ እንደሚታየው በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከፍተኛውን የድግግሞሽ መጠን የያዘው የአረፍተ ነገር ምስረታ ነው። ይዘቱ በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ሃያ ጊዜ (21.5%)ተደጋግሞ ቀርቧል። በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበው የቃላት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች ሲሆን፤ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ አስራ አራት ጊዜ (15.1%) ተደጋግሟል። በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የምናገኘው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት የቃላት ተመሳሳይ ፍች ነው። ይኸውም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አስራ አንድ ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን ከአጠቃላዩ ውስጥ 11.8% ሽፋን ይዞ ይገኛል። በመማሪያ መጸሐፉ ውስጥ የሐረጋት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች ስምንት ጊዜ፤ የቃላት ምስረታ ስድስት ጊዜ፤ በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት፣ ድምጸ-ልሳናዊ ሂደት፣ የስም ገላጮች፣የግስ ገላጮች፣ ሐረግ ምስረታና የቃላት ተቃራኒ ፍች እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ጊዜ፤ ጥገኛ ምዕላዶች (ቅጥያዎች)፣የቃላት እርባታ፣ ስም፣ አያያዥ ቃላት/ሐረጋት፣ የተዘበራረቁ ቃላትን በቅደም ተከተል በማሰለፍ ትክክለኛ አረፍተ ነገር መገንባትና የቃላት ቀጥተኛ (እማሬያዊ/መዝገበ ቃላዊ) ፍች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ፤ እንዲሁም ግስ፣ ቅጽል፣ የተጓደሉ አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላትና የአረፍተ ነገር አውዳዊ/አገባባዊ ፍች እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርበው እንደሚገኙ ሰንጠረዥ አስር ያሳያል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በአጠቃለይ ሃያ አንድ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተው የሚገኙ ቢሆንም ከሰንጠረዡም ሆነ ከዚህ ትንታኔ መገንዘብ የሚቻለው አንድ አምስተኛ ያህሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የቀረቡት። ሌሎቹም ቢሆኑ ከፍተኛ የድግግሞሽ መጠን (ሃያ ጊዜ) ካላቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች አንጻር ሲታዩ እጅግ ዝቅተኛ የሆነ የድግግሞሽ መጠን ነው ያላቸው። ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ በርካታ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቂ የሆነ ክትትል/ ድግግሞሽ እንደሌላቸው ወይም የተከታታይነት ድክመት እንደሚታይባቸው ያሳያል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶችም ቢሆኑ ስፋትና ጥልቀታቸው ወይም የክብደት መጠናቸው ከምዕራፍ ምዕራፍ እየጨመረ እንደማይሄድ ከሚከተሉት ከመጽሐፉ ውስጥ በአስረጅነት ከተወሰዱት ይዘቶች መረዳት ይቻላል፡፡

6. ቀጥሎ የተሰጠውን ምሳሌ በደንብ አስተውሉ፡፡

ምሳሌ፡- እጅ + ኦች = እጆች

ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ያሉትን ቃላት ተንትኗቸው፡፡

6.1 ልጆች

6.2 በጎች

. . .

(በቅጥያዋ (ኦች) አጠገብ ጭረት አለመኖር ስህተት ከምንጩ)

/7ኛ ክፍል፤ገጽ፣21/

ሐ. የሚከተሉትን ቃላት መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችና ዋና ቃል ለይታችሁ አሳዩ፡፡

| ምሳሌ፡- ቃል | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ | ዋና ቃል |
|---|---|---|---|
| ከቤታችሁ | ከ | ኣችሁ | ቤት |

1. ቀልዶች
2. ከመጣች

. . .

(ቅጥያዎች አጠገብ ጭረት አለመኖር ስህተት ከምንጩ)

/7ኛ ክፍል፤ገጽ፣32/

ከመጽሐፉ የተለያዩ ገጾች በአስረጅነት የተወሰዱት ተመሳሳይ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል መጠነኛ የሆነ የአቀራረብ ልዩነት ከመኖሩ/ከመታየቱ በስተቀር ስፋትና ጥልቀታቸውን በተመለከተ ሁለተኛው ከመጀመሪያው ያን ያህል ከባድ ነው ወይም ጠለቅ ያለ ማስተዋልን ይጠይቃል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አይታይበትም፡፡ ተማሪዎች ምሳሌዎቹን በማየት ብቻ በቀላሉ ሊሰሯቸው የሚችሉ ይዘቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር አስር ላይ እንደሚታየው ይህን አስመልክቶ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣‹‹*በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ጨምረዋል፡፡*›› በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለቱም መምህራን የሰጡት ምላሽ አሉታዊ ነው፡፡ከመምህራኑ ምላሽ ብቻም ሳይሆን ከምልከታውም ማስተዋል የተቻለው በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡም

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቢሆኑ ስፋትና ጥልቀት ይታይባቸዋል ብሎ ለመደምደም እንደማይቻል ነው፡፡

***መ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ***

ሰንጠረዥ አስር እንደሚያሳየው በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሃያ ስድስት የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቀርበው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ተደጋግሞ የምናገኘው የአረፍተ ነገር ምስረታ ነው፡፡ ይህ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አስራ ሰባት ጊዜ ወይም ከአጠቃላዩ 13.7% ያህል ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የምናገኘው ጥገኛ ምዕላዶችን (ቅጥያዎችን) በተመለከተ የቀረበው ይዘት ሲሆን ይህም አስራ አንድ ጊዜ (8.9%) ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሦስተኛ ደረጃ ተደጋግመው የምናገኛቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቃላት ተመሳሳይ ፍችና የቃላት አውዳዊ/አገባባዊ ፍች ናቸው፡፡ እነዚህ ይዘቶች እያንዳንዳቸው በመጽሐፉ ውስጥ አስር አስር ጊዜ ተደጋግመው የሚገኙ ሲሆን ከአጠቃላዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በድምሩ 16.2% ሽፋን አላቸው፡፡ ከቀሪዎቹ አብዛኛዎቹ ይዘቶች ውስጥ ሁለት ይዘቶች ሰባት ሰባት ጊዜ፤ አምስት ይዘቶች አምስት አምስት ጊዜ፤ አምስት ይዘቶች አራት አራት ጊዜ፤አንድ ይዘት ሦስት ጊዜ፤ ሦስት ይዘቶች ሁለት ሁለት ጊዜና አምስት ይዘቶች ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ እንደቀረቡ ከሰንጠረዥ አስር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ያላቸው ድግግሞሽ ወይም ተከታታይነት ከፍተኛ ድግግሞሽ ካላቸው ጋር ሲነጻጸር እጅግ ዝቅተኛ ቢሆንም አንድ አምስተኛ የሚሆኑት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርበው መታየታቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያላቸው ተከታታይነት እጅግ ደካማ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፣መጠይቅ ቁጥር ዘጠኝ ላይ እንደሚታየው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሁለቱም መምህራን ምላሽ አሉታዊ ሆኖ ይታያል፡፡ እንዲሁም የዚህ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዷ፣ *‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው? ለምሳሌ*

*አተከታታነት አኳያ?›› በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ ‹‹አንድ ይዘት ተከታታይነት ከሌለው በተማሪዎች ዘንድ በቀላሉ ሊረሳ ስለሚችል በመጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ እንዲደጋገም ለማድረግ ሞክረናል፡፡ ነገር ግን ለሁሉም ይዘቶች ድግግሞሽ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥተናል ብዬ አላምንም፡፡ የስፋትና የጥልቀት ወይም የክብደት ደረጃ እየጨመረ የመሄድ ሁኔታን አላገናዘብንም ወይም ግምት ውስጥ አላስገባንም፡፡ ያው እንደነገርኩህ ይሄ ከዝግጅት ጊዜው እጥረት አኳያ የተፈጠረ ችግር ነው፡፡ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው ያዘጋጀነው፡፡››* የሚል ሆኖ ይገኛል፡፡ እኝህ አዘጋጅ የሰጡት ምላሽ የሚያስገነዝበው አንደኛ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስዋዊ ይዘቶች ተከታታይነት ድክመት ያለበት መሆኑን፤ ሁለተኛ ደግሞ ምንም እንኳ ይዘቶቹ ተከታታይነት እንዲኖራቸው ጥረት ቢደረግም ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የመሄድ ሁኔታቸው ፍጹም ግምት ውስጥ ያልገባ መሆኑን ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የይዘቶቹን ተከታታይነት በተመለከተ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ የስፋትና የጥልቀት ሁኔታዎችን ደግሞ ቀጥሎ ከመጽሐፉ አስረጅ በመውሰድ እንይ፡፡

1. በምድብ ‹‹ሀ›› ስር ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጎች ከምድብ ‹‹ለ›› ስር

   በትርጉም ተመሳሳያቸውን ምረጡ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.1 በዘፈቀደ | ሀ. ካቀዱት |
| 1.2 ጠፈር | ለ. እርባና |

. . . /8ኛ ክፍል፣ገጽ፣9/

ሐ. በምድብ ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሐረጎች ከምድብ ‹‹ለ›› ስር

   ፍቺያቸውን ወይም በትርጉም ተመሳሳያቸውን በመምረጥ አዛምዱ

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ከስኬት ወዲህ ማዶ | ሀ. ጉድለት |
| 2. በአሉታዊ መልኩ መገመት | ለ. የፍርሃት ጽንስ |

. . . /8ኛ ክፍል፣ ገጽ፣73/

1. በምድብ ‹‹ሀ›› ስር ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን

ከምድብ ‹‹ለ›› እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.1 ኡደት | ሀ. በብዛት |
| 1.2 ደራ | ለ. ቦርጭ |

. . . /8ኛ ክፍል፣ገጽ፣193/

ከዚህ በላይ ከመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ውስጥ ተወስደው በአስረጅነት የቀረቡትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ልብ ብለን ስንመለከት የስፋትና የጥልቀት ቀርፆ የአቀራረብ እንኳ ልዩነት አናገኝባቸውም፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሌሎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችም ቢሆኑ ተደጋግመው ይቅረቡ እንጂ ይህን መሰል አሰልቺ አቀራረብና ድግግሞሽ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ይህን በመሰለ ሁኔታ ይዘቶችን ደጋግሞ ማቅረብ ተማሪዎችንም ሆነ መምህሩን ከሚያሰለች በስተቀር ሌላ ምንም ጠቃሚ ፋይዳ ጠብ ሊለው አይችልም፡፡

## 4.3.2 ከቀጣይነት አንጻር

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ውስጥ ለማብራራት እንደተሞከረው ቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ወይም ተከታታይነት ባላቸው የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ተደጋግመው ወይም ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ ተደራጅተው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ የይዘቶቹ ቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት ግን ከክፍል ክፍል እያደገና ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ መሄድ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስዋዊ ይዘቶችን ቀጣይነት አስመልክቶ ያላቸው ገጽታ በሚከተለው መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ከሰንጠረዥ አስር መረዳት እንደሚቻለው ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በአጠቃላይ ሃያ ሰባት የተለያዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ቀርበው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ይዘቶች መካከል አስራ ዘጠኙ በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ ያለ ምንም መቆራረጥ በቀጣይነት ወይም በተለጣጣቂነት ቀርበዋል፡፡ አብዛኞዎቹ ይዘቶች በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ ተደራጅተው መገኘታቸው እንደ ጠንካራ ጎን ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከሃያ ሰባቱ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ ስምንቱ በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ በቀጣይነት ተደራጅቶ የመቅረብ ድክመት እንደሚታይባቸው አሁንም ከሰንጠረዥ አስር መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ድምጸ-ልሳናዊ ሂደት በሰባተኛና በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ብቻ እንጂ በአምስተኛና በስድስተና ክፍሎቹ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ስለ ቅጽልም እንደዚሁ በሰባተኛና በስምንተኛ ክፍሎች ውስጥ ብቻ ነው የምናገኘው፡፡ ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድ፣ የቅጥያዎችና የአጻፋዎች ፍች፣የቃላት ፍካሬያዊ ፍችና የአንድን አረፍተ ነገር ሀሳብ በሌሎች አባባሎች ወይም አገላለጾች መግለጽ የሚሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በሙሉ ቀርበው የሚገኙት በስምንተኛ ክፍሉ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ የተዘበራረቁ ቃላትን ቅደም ተከተል ማስያዝ የሚለው ይዘት በአምስተኛ ክፍል ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡ እንዲሁም የአረፍተ ነገር አውዳዊ/አገባባዊ ፍች የሚለው ሰዋስዋዊ ይዘት ከአምስተኛ እስከ ሰባተኛ ክፍል ባሉት አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ብቻ እንጂ በስምንተኛ ክፍሉ ውስጥ ቀጣይነቱን ጠብቆ አይታይም፡፡ በአጠቃላይ አምስት የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በምንም አይነት መልኩ ቀጣይነታቸውን ሳይጠብቁ በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ ቀርበው ይገኛሉ፡፡ ይህ እንግዲህ በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት በተመለከተ ድክመት እንዳለ የሚያሳይ ነው፤ (ዝርዝሩን ሰንጠረዥ አስር ላይ ይመልከቱ)፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱትና በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት ድክመት ወይም መቆራረጥ ይታይባቸዋል ከተባሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል የተወሰኑት ለየደረጃው በተዘጋጁ መርሃ ትምህርቶች ውስጥም ያልተካተቱ ወይም የሌሉ ይዘቶች ናቸው፡፡ በእርግጥ በተተኳሪ መጻህፍቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና በየደረጃው መሰረት ባደረጓቸው መርሃ ትምህርቶች ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ያለው ተዛማጅነት በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ አካባቢ (በ4.4 ላይ) የሚዳሰስ ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ ስምንት፣መጠይቅ ቁጥር ስምንት ላይ እንደሚታየው የሰዋስዋዊ ይዘቶችን ቀጣይነት አስመልክቶ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አሁን ካለሁበት የክፍል ደረጃ በፊት ተዋውቂያቸው ነበር፡፡››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የ54% ተማሪዎች አዎንታዊ ሲሆን፣የ46% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ነው፡፡ ምንም እንኳ መጠይቁን ከሞሉት 56 ተማሪዎች ከግማሽ በላይ (30 ተማሪዎች) የሚሆኑት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ቢሆንም ከእነዚህ የሚጠጋጋ ቁጥር ያላቸው (26 ተማሪዎች)

ደግሞ አሉታዊ ምላሽ መስጠታቸው የሚያስገነዝበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የቀጣይነት ወይም የተለጣጣቂነት ድክመት የሚታይባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ የተማሪዎቹ ምላሽ የተደረገውን ምልከታ የሚያጠናክረው ሆኖ ይገኛል፡፡

እንዲሁም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስዋዊ ይዘቶችን ቀጣይነት አስመልክቶ የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዱ፣ *‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው? ለምሳሌ ከቀጣይነት ወይም ከተለጣጣቂነት አኳያ?››* በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ *‹‹የአምስተኛ ክፍሉን ያየን ይመስለኛል፤ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍሎቹን ግን አላየንም፡፡ ከአዘጋጆቹም ጋር ተናብበን አልሰራንም፡፡ ይህ በይዘቶች ተለጣጣቂነት ላይ ክፍተት ይፈጠራል ብዬ አምናለሁ፡፡››* የሚል ሲሆን፤ በተመሳሳይ መልኩ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዷ ይኸው ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ፣ *‹‹ተለጣጣቂነትን ጠብቋል ማለት አይቻልም፡፡ በተለይ ከአምስተኛ እስከ ሰባተኛ ክፍል ያሉትን መጻህፍት አላየንም፤ ከነዚህ መጻህፍት አዘጋጆች ጋርም ተወያይተን አልሰራንም፡፡ እኛ ያዘጋጀነው የስምንተኛ ክፍሉን መርሃ ትምህርት ብቻ በማየት ነው፡፡ ከታች ካሉት ይልቅ እኛ ያየነው የዘጠነኛ ክፍሉን አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ወደ ፊት እንዳይቸገሩ በማለት ነው እንደዚህ ያደረግ ነው፡፡››* የሚል ነው፡፡

ከሁለቱም የተለያዩ ደረጃዎች መጻህፍት አዘጋጆች ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ባዘጋጁቸው የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ለተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት ምንም ትኩረት እንዳልተሰጠ ነው፡፡ በየክፍል ደረጃው ቀጣይነት ባለው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ ይዘቶች የክፍል ደረጃው እያደገ በሄደ ቁጥር የይዘቶቹ ስፋትና ጥልቀት ወይም ከባድነት እንደዚሁ እያደገ ወይም እየጨመረ መሄድ እንደሚገባው ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ቀጣይነታቸውን ጠብቀው የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ጥልቀታቸው እየጨመረ ወይም የክብደት ደረጃቸው እያደገ ሲደራጁ አይታዩም፡፡ ለዚህም አስረጅ ይሆን ዘንድ የሚከተሉትን ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ

ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተወሰዱትን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ቀጥሎ እንመልከት፡፡

2. ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ/ሲነገሩ የተለያዩ ትርጉሞችን የሚያመጡ ድምጾችን ወይም ፊደሎችን ያያዙ ቃላትን በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በጽሁፍ እንለያለን፡፡

ምሳሌ፡- ሰባ (ቁጥሩ) / ላልቶ ሲነበብ/

ሰባ( ወፈረ) /ጠብቆ ሲነበብ/

2.1 አለ፡፡ ላልቶ ሲነበብ ፍቺው ———— ነው፡፡

ጠብቆ ሲነበብ ———— ነው፡፡

. . . / አምስተኛ ክፍል፤ገጽ፣20/

ቃላት ላልተውና ጠብቀው ሲነበቡ የተለያየ ትርጉም ያስገኛሉ፡፡

ምሳሌ፡- ለጋ 1. ጠብቆ ሲነበብ መታ፣ አገነ ይሆናል፡፡

ላልቶ ሲነበብ ያልበሰለ፣ ቀንበጥ ማለት ይሆናል፡፡

ሀ. እንስራ 1. ጠብቆ ሲነበብ ———— ነው፡፡

2. ላልቶ ሲነበብ ———— ነው፡፡

. . . / ስድስተኛ ክፍል፤ገጽ፣27/

1. በአማርኛ በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት የፍቺ ልዩነት ያመጣል፡፡

ምሳሌ፡- ፖሊሶች አስቸጋሪውን ሌባ አድነው ያዙት፡፡/ ጠብቆ ሲነበብ/

- ሐኪሞቹ በሽተኛውን አድነው ወደ ቤቱ ሸኙት፡፡/ ላልቶ ሲነበብ/

1.1 አባይ፤ ———————— ፡፡/ ጠብቆ ሲነበብ/

———————— ፡፡/ላልቶ ሲነበብ/

. . . / ሰባተኛ ክፍል፤ገጽ፣19/

1. የሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን የፍቺ ልዩነት በቃል ተናገሩ፡፡

ምሳሌ፡- 1. በራ (ሲላላ)- ራስ መለጣ

(ሲጠብቅ)- ብርሃን ሰጠ/ መብራት

ሀ. ፍራሽ

ለ. አዛባ

. . . /ስምንተኛ ክፍል፤ገጽ፣54/

ከዚህ በላይ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ካሉት አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተወስደው በአስረጅነት ከቀረቡት ማየት እንደሚቻለው በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት ስለሚያመጣው የፍች ልዩነት ለማስተማር ታስቦ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በሁሉም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የጎላ የአደረጃጀት ልዩነት ሳይታይባቸው

ወይም ስፋትና ጥልቀት ሳይጨምሩ ቀርበው ይገኛሉ፡፡ ከአምስተኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል በቀጣይነት ቀርበው የሚገኙት እነዚህ ይዘቶች ከክብደት አንጻር ሲ.ታዩ/ሲ.መዘኑ አንድ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ምሳሌዎቹን በማየት ለመስራት የሚያዳግተው ነገር ይኖራል ብሎ ለመገመት አያስችሉም፡፡ በመሆኑም ይዘቶቹ ከደረጃ ደረጃ ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረና ከባድነታቸው እያደገ የመሄድ ሁኔታ አይታይባቸውም ወይም ከዚህ አንጻር ሲ.መዘኑ ድክመት አለባቸው፡፡

በየክፍል ደረጃው ያሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት አለመጨመር ወይም የክብደት ደረጃቸው እያደገ አለመሄድና በእጅጉ የመመሳሰል ሁኔታ በተማሪዎች ዘንድ ሊ.ፈጥር የሚችለው ችግር በቀላሉ ሊ.ታይ የሚችል አይደለም፡፡ ለተማሪዎች በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥም ሆነ ከክፍል ወደ ክፍል በሚሸጋገሩበት ወቅት የሚያጋጥሟቸው ተመሳሳይ ወይም የአቀራረብ ለውጥ እንኳ የሌላቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቋንቋውን ለመማር በሚኖራቸው የፍላጎትና የተነሳሽነት ስሜት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊ.ያሳድርባቸው እንደሚችል ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ ተመሳሳይ የትምህርት ይዘቶችና አቀራረቦች የመማር ፍላጎትን ይገድላሉ፤ የተነሳሽነት ስሜትን ያኮላሻሉ፤ አልፎ ተርፎም ትምህርቱ እንዲ.ጠላ ያደርጋሉ፡፡ እንዲ.ሁም ለጊዜ፣ ለገንዘብ፣ ለሰው ሃይል፣ ወዘተ ኪ.ሳራ ይዳርጋሉ፡፡ በመሆኑም በትምህርት ይዘቶች ዝግጅት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊ.ደረግ ይገባል፡፡

### 4.3.3 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንጻር

በክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚ.ህ የአደረጃጀት ስልት ምንም አይነት ሰዋስዋዊ ገለጻ ወይም ማብራሪያ የማይሰጥ ሲ.ሆን፤ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች ብቻ በመንተራስ የታላሚ.ውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት ወይም ስርአት ለይተው እንዲ.ያውቁና እንዲ.ለማመዱ የሚ.በረታቱበት ስልት ነው፡፡ በዚ.ህ ስልት ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን እየሰሩ፣ እየተለማመዱ፣ በሂደት የታላሚ.ውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአት ይካኑታል ማለት ነው፡፡በዚ.ህ ጥናት ተተኳሪ አራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ አብዛኞዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ይህን የአደረጃጀት ስልት ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን በተደረገው ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቀጥሎ

ከእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ አስረጅ በመውሰድ ለማሳየት ይሞከራል፡፡

### ሀ. የአምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ

በአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቅድሚያ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአት ወይም ህግ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች በሂደት ህግጋቱን ለይተው እንዲያውቋቸው የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ ተማሪዎቹ ምሳሌዎቹን ተከትለው የቀረቡ መልመጃዎችን ወይም ጥያቄዎችን በመስራት ህግጋቱን ይለማመዷቸዋል፤ በሂደትም ይካኗቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም የመማሪያ መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልትን የተከተሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዳቀረበ ያሳያል፡፡ በዋቢነት የሚከተለውን አስረጅ እንመልከት፡፡

ከዚህ በታች ያሉትን አያያዦች ተጠቅሜ የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን እጽፋለሁ፡፡

ቀጥሎ፣ከዚህ በኋላ፣ብሎም፣በመሆኑ፣ሆኖም፣ዳሩ ግን

ምሳሌ፡- ነገሩ ግራ አጋቢ በመሆኑ በጣም አዝኛለሁ፡፡

. . . /5ኛ ክፍል፤ገጽ፣32/

ከቀረበው አስረጅ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ምሳሌውን በማጤን ወይም በመከተልና የተሰጡትን አያያዦች በመጠቀም የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፤መልመጃውን ወይም ጥያቄዎቹን በመስራት ሂደት ውስጥ የአያያዦችን አጠቃቀም ስርአት ይለማመዳሉ፤ ብሎም ይካኑታል፡፡ ከመልመጃው ወይም ከጥያቄዎቹ አስቀድሞ የቀረበ ምንም አይነት ገለጻ/ማብራሪያ የለም፡፡ ይህም ይዘቱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልትን ተከትሎ መቅረቡን ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር አስራ ሁለት እንደሚያሳየው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣*‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርአት እራሳቸው በሂደት እንዲያውቁት በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው፡፡››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የአንድ መምህር/ት ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ሲሆን፤ የአንድ መምህር/ት ደግሞ አዎንታዊ ሆኖ ይገኛል፡፡ከምልከታው ማረጋገጥ የተቻለው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡት አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትን ተከትለው

የቀረቡ መሆናቸውን ነው፡፡

**ለ. የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

እንደ አምስተኛ ክፍሉ ሁሉ በስድስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ከዝርዝር ሰዋስዋዊ ባህሪያቸው ወደ አጠቃላይ ስልት የተደራጁ ናቸው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት/ስርአት የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ያቀረቡ ሲሆን፤ ተማሪዎቹ ምሳሌዎቹን በመመርኮዝ የመልመጃ ጥያቄዎቹን ይሰራሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ህግጋቱን እንዲለማመዷቸው እድል ከመስጠቱም በላይ ከልምምዱ ሂደት በኋላ የቋንቋውን ህግጋት/ስርአት ወደ መገንዘብ እንዲያመሩ ያበረታታቸዋል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተለውን ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተወሰደ የሰዋስው ትምህርት ይዘት መልመጃ እንይ፡፡

ለ. የተሰመረባቸው ቃላት በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ያላቸውን ትርጉም

እያያችሁ በምሳሌው መሰረት ስሩ፡፡

ምሳሌ፡- መልዕክት <u>አደረሰ</u>፣ አስተላለፈ፣ ነገረ

ልጅ <u>አደረሰ</u>፣ አጎለመሰ፣ አሳደገ

1. እህል <u>ሸመተ</u>፣ ___________

በሽታ <u>ሸመተ</u>፣ ___________

. . . /6ኛ ክፍል፤ገጽ፣16/

ከዚህ በላይ በአስረጅነት የቀረበውን ስንመለከት ተማሪዎች በመልመጃው ውስጥ የቀረበላቸውን ምሳሌ ብቻ በማስተዋል የቃላትን አውዳዊ/አገባባዊ ፍች ይናገራሉ/ይጽፋሉ፤ ይህም በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ወይም ስልት ተደራጅተው መቅረባቸውን ያሳየናል፡፡ ከምልከታው ማረጋገጥ የተቻለውም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡት አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን ነው፡፡ የዚህ ክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዱ፣*‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው? ለምሳሌ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልትን በተመለከተ?››* በማለት ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣*‹‹አንተ የአደረጃጀት ስልቶች ወይም መርሆዎች የምትላቸውን ሁሉ አልተከተልንም፡፡ እውነቱን ለመናገር ግንዛቤውም አልነበረንም፤ ልምዱም የለንም፡፡ እኛ ያዘጋጀነው ቀደም ሲል የነበሩትን የአማርኛ*

*መማሪያ መጻህፍት በሞዴልነት በመውሰድ ነው።››* የሚል ሆኖ ይገኛል። ከአዘጋጁ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት የቀረቡትም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቢሆኑ በዘፈቀደ እንጂ ታስቦባቸው የቀረቡ እንዳልሆኑ ነው።

**ሐ. የሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

በአምስተኛና በስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ እንዳየነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአደረጃጀት ስልት ቀርበው እናገኛለን። ለዚህም በአስረጅነት የሚከተለውን እንመልከት።

4. ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ ተመልክታችሁ የተሰጡትን ሀረጎች
 አሳጥራችሁ ጻፉ።
 ምሳሌ፡- ዘንድሮ የተሸለመችው ጎበዟ ተማሪ
 - የተሸለመችው ጎበዟ ተማሪ
 - ጎበዟ ተማሪ

ሀ. ዛሬ ጠዋት ከጓደኛው ጋር የመጣው ልጅ

ለ. ለበአል የተገዛ ነጭ ሙክት በግ

. . . /7ኛ ክፍል፤ገጽ፣25/

ተማሪዎች ከዚህ በላይ በአስረጅነት የቀረበውን ሰዋስዋዊ መልመጃ/ጥያቄዎች ምሳሌ በመመልከት ተስፋፍተው የተጻፉ ሀረጎችን በምሳሌው መሰረት አሳጥረው ይጽፋሉ ተብሎ ይጠበቃል/ይገመታል። ይህ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎቹን በሂደት የቋንቋውን ህግጋት ወደ መገንዘብ ደረጃ ሊያሸጋግራቸው እንደሚችልና እንደሚያበረታታቸውም ይታመናል። ይህን አስመልክቶ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣‹‹*በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርአት እራሳቸው በሂደት እንዲያውቁት በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው።››* (ሰንጠረዥ ሰባት፣መጠይቅ ቁጥር አስራ ሁለት) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የሁለቱም መምህራን አሉታዊ ሆኖ ይገኛል። ይህም የሚያስገነዝበው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሰሯቸው ወይም እንዲለማመዷቸው በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው የመቅረብ ድክመት የሚታይባቸው መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ ከምልከታው ማረጋገጥ የተቻለው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡት አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከዝርዝር

ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን ነው፡፡

**መ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ**

ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች እንዳየናቸው የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ሁሉ በዚህም መጽሐፍ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት ተደራጅተው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እናገኛለን፡፡ ተማሪዎች በተለያዩ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ውስጥ የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች ብቻ በማየት የተለያዩ ሰዋስዋዊ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ የሚያዙ በርካታ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይታያሉ፡፡ ቀጥሎ ከመጽሐፉ ውስጥ በአስረጅነት የተወሰደውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት እናያለን፡፡

4. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ባለቤቱን በቅንፍ ውስጥ
   ከተሰጠው ግስ ጋር አጣጥማችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. እኛ ቁርስ (በላ)
            እኛ ቁርስ በላን፡፡

4.1 እናንተ በጣም —————— ፡፡ (ተደሰተ)

4.2 አንተ ደብዳቤ —————— ፡፡ (ጻፈ)

. . . /8ኛ ክፍል፤ገጽ፣22/

በቀደሙት የክፍል ደረጃዎች እንደታየው ሁሉ በዚህም የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት መልመጃዎች በቅድሚያ ለተማሪዎች ምሳሌዎችን አቅርበዋል፡፡ ተማሪዎችም የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በመመርኮዝ የመልመጃ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡ ብሎም ከምሳሌዎቹና ከመልመጃ ጥያቄዎቹ በሂደት የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት ወደ መገንዘብ ይሸጋገራሉ፤ እንዲሁም ተግባራዊ ያደርጓቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህም መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አካቶ መያዙን ያመለክታል፡፡

የዚህ ክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዱ፣*‹‹በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጀሃቸው? ለምሳሌ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልትን በተመለከተ?››* በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣*‹‹ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስለሚሉት የአደረጃጀት ዘዴዎች እኔም ሆንኩ አብሮኝ የነበረው ባልደረባዬ ምንም የምናውቀው ጉዳይ አልነበረም፡፡ አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ሁለቱንም ስልቶች የተጠቀምን ይመስለኛል፡፡ ይህን ያደረግነው ግን እውቀቱ ወይም ግንዛቤው ኖሮን ሳይሆን ቀደም ሲል የነበረውን*

የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በዝግጅታችን ወቅት በሞዴልነት እንጠቀምበት ስለነበር ነው።›› የሚል ነው። ከአዘጋጁ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ጉዳይ ግምት ውስጥ እንዳልገባ ወይም ትኩረት እንዳልተሰጠው ነው። ሆኖም ምልከታው የሚያስገነዝበው በዚህም የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተካተው የቀረቡት አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን ነው።

## 4.3.4 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር

በዚህ የአደረጃጀት ስልት በቅድሚያ ስለ ታላሚው ቋንቋ ህግጋት ወይም ሰዋስዋዊ ስርአት የሚያሳይ ገለጻ ለተማሪዎች ይቀርብላቸዋል። ይህ ብቻም በቂ አይደለም ገለጻው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ መቅረብ መቻል አለበት። በማስከተል ተማሪዎች በገለጻ የቀረቡላቸውን ህግጋት በዝርዝር ወደ መለማመድ ያመራሉ። የዚህ ጥናት አቅራቢም በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት ስልት በሚፈትሽበት ጊዜ በአራቱም አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በዚህ ስልት ተደራጅተው የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መኖራቸውን አረጋግጧል። በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ ከየክፍል ደረጃው በአስረጅነት የተወሰዱትን እንመለከታለን።

*ሀ. አምስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ*

በአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አምስት ልዩ ልዩ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች ቀርበዋል። እነዚህም፡- ስለ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት (ገጽ፣15)፣ስለ ሐረግ (ገጽ፣26)፣ ስለ አረፍተ ነገር ምንነት (ገጽ፣28)፣ አሁንም ስለ አረፍተ ነገር (ገጽ፣29) እና ስለ ቃል ቀጥተኛና አገባባዊ ፍች (ገጽ፣32) የቀረቡት ናቸው። እነዚህ ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ገለጻዎች አስቀድመው ስለ ርዕስ ጉዳያቸው ገለጻ ከሰጡ በኋላ ምሳሌዎችን ያሳያሉ፤ በማስከተልም ተማሪዎች የሚለማመዱባቸውን ልዩ ልዩ መልመጃዎች ያቀርባሉ። ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት መደራጀታቸውን ያሳያል። እስኪ አንድ አስረጅ በመውሰድ ለመመልከት እንሞክር።

| |
|---|
| የቃልን ቀጥተኛና አገባባዊ ፍች መለየት<br>ቀጥተኛ ፍች፡- ከመዝገበ ቃላት የሚገኝ ፍች ነው፡፡በአድማጩና<br>በተናጋሪው መካከል በቀላሉ መግባባት የሚፈጥር ነው፡፡<br>ምሳሌ፡- በላ-ተመገበ፣ አፉ አደረገ<br>አገባባዊ ፍች፡- አንድ ቃል በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ሲገባ<br>የሚያመጣው ሰፊ ፍች ነው፡፡<br>ምሳሌ፡- ህጻኑ ሲያለቅስ አንጀቴን በላኝ፡፡ፍችው አሳዘነኝ<br>ይሆናል፡፡ |

1. ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ‹‹ውሃ›› ለሚለው ቃል አገባባዊ ፍች እንስጣለን፡፡
   1.1 ከጉዞ ብዛት የተነሳ ጉልበቴ ውሃ ሆነ፡፡ ፍችው —————— ነው፡፡
   1.2 ሌባው ሲሰርቅ በድንገት ስላየሁት ውሃ ሆነ፡፡ ፍችው ———— ነው፡፡

. . . /5ኛ ክፍል፣ገጽ፣32/

ከቀረበው አስረጅ መረዳት እንደሚቻለው በቅድሚያ ለተማሪዎች ስለ ቃላት ቀጥተኛና አገባባዊ ፍች ምንነት መረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ምሳሌዎችም ቀርበውላቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ተማሪዎች በቀረቡላቸው ልዩ ልዩ መልመጃዎች ውስጥ ልምምዳቸውን በመቀጠል ከሰዋስዋዊ ገለጻውና ከምሳሌዎቹ ያገኙትን ግንዛቤ ተግባራዊ እያደረጉ ይሄዳሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት የሰዋስው ትምህርት ይዘቱ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚለውን የአደረጃጀት መርህ ተከትሎ ቀርቧል ማለት ይቻላል፡፡ ሰንጠረዥ ስምንት፣ መጠይቅ ቁጥር አስራ አንድ ላይ ማየት እንደሚቻው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አስቀድመው ስለ ቋንቋው ስርአት ገለጻና ምሳሌዎችን በመስጠት የቋንቋውን ስርአት ወደ መለማመድ የሚያሸጋግሩኝ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ የ48% ተማሪዎች አዎንታዊ፣ የ10% ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚልና የ42% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ሆኖ ይገኛል፡፡ የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያስገነዝበው ምንም እንኳ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቢኖሩም በበቂ ሁኔታ ወይም መጠን የቀረቡ ናቸው ለማለት እንደማያስደፍር ነው፡፡ ይህም የተማሪዎቹ ሃሳብ በምልከታው የተደረሰበትን ድምዳሜ የሚያጠናክረው ሆኖ ይገኛል፡፡

ለ. የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ ስድስት የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች ቀርበው እናገኛለን፡፡ እነዚህም፡- ስለ ምህጻረ ቃላት (ገጽ፣7)፣ስለ ገላጮች/የስምና የግስ ገላጮች (ገጽ፣19-20)፣ ስለ ቃላት ጠባይ/ጠብቀውና ላልተው ስለሚነበቡና ስለ አገባባዊ ፍች (ገጽ፣27)፣ ስለ ቅጥያዎች (ገጽ፣29)፣ ስለ ቃል፣ ሐረግና ዐረፍተ ነገር ምንነት (ገጽ፣32) እና ስለ አያያዦች (ገጽ፣71) የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ሰዋስዋዊ ገለጻውን በምሳሌዎች አስደግፈው ካቀረቡ በኋላ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ሰዋስዋዊ ገለጻና ምሳሌዎች ተመርኩዘው ወደሚለማመዷቸው መልመጃዎች ይሸጋገራሉ፡፡ ይህም በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት መርህን ተከትለው የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ ቀጥሎ ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በአስረጅነት የተወሰደ አንድ ሰዋስዋዊ ገለጻ እናያለን፡፡

<u>ቅጥያዎች</u>

ቅጥያዎች፡- በአንድ ዋና ቃል ላይ የሚጨመሩና ለተለያየ ተግባር የምንገለገልባቸው ናቸው፡፡ ቅጥያዎች በቃል ላይ ካልተጨመሩ በስተቀር በራሳቸው ትርጉም የላቸውም፡፡

ምሳሌ፡- አል-፣ተ-፣ስለ-፣-ኦች፣-ን

ቅጥያዎች ለተለያየ ሰዋስዋዊ ተግባር በዋና ቃል ላይ ሲጨመሩ የትርጉም ለውጥ ያስከትላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ሠራ ዋና ቃሉ/የቃሉ ግንድ/ ቢሆን

1. ተሠራ /ተ-/ የድርጊት መፈጸምን የሚያሳይ መነሻ ቅጥያ ነው፡፡
2. አልሰራም / አል-ም/ ድርጊቱ አለመፈጸሙን ለማሳየት ከመነሻና ከመድረሻ የገቡ ቅጥያዎች ናቸው፡፡
3. ሠራች /-ች/ እንስት ጾታን ለማመልከት የገባ መድረሻ ቅጥያ ነው፡፡
4. ስለሰራች /ስለ-/ ምክንያትን አመልካች መነሻ ቅጥያ ነው፡

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ላይ መነሻና መድረሻ ቅጥያ በመጨመር የተለያዩ ፍቺዎችን እንዲያመለክቱ አድርጋችሁ ጻፉ፡፡

| ቃሉ | በመነሻ | በመድረሻ | በመነሻና በመድረሻ |
|---|---|---|---|
| 1. መጣ | ______ | ______ | ________ |
| 2.ሄደ | ______ | ______ | ________ |

. . . /6ኛ ክፍል፤ገጽ፣29/

ከላይ በአስረጅነት የቀረበውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ስንመለከት አስቀድሞ ስለ ቅጥያዎች ምንነትና ተግባር ገለጻ ከሰጠ በኋላ ገለጻውን በምሳሌዎች ያጠናክራል። ቀጥሎም ገለጻውንና ምሳሌዎቹን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችን ለተማሪዎች ያቀርባል። እንግዲህ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ገለጻውንና ምሳሌዎቹን ከተገነዘቡ ወይም መሰረት ካደረጉ በኋላ ነው ማለት ነው የመልመጃ ጥያቄዎቹን ወደ መስራት ወይም ሰዋስዋዊ ህግጋቱን ወደ መለማመድ የሚሸጋገሩት። ይህም ባጭሩ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልትን ወይም መርህን ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን ያሳየናል። ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር አስራ ሦስት እንደሚያሳየው በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣*‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎችንና ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርአት ለመለማመድ በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው ቀርበዋል።››* በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ የአንድ መምህር/ት ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ሲሆን፤ የአንድ መምህር/ት ደግሞ አሉታዊ ነው። ይህም ምላሽ የሚያስገነዝበው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በበቂ ሁኔታ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልትን ተከትለው መቅረብ ያለመቻላቸውን ሲሆን፤ በምልከታው ማረጋገጥ የተቻለውም ይህንኑ ነው።

ሐ. የሰባተኛ ክፍል አማርኛ *መማሪያ መጽሐፍ*

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አራት ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ገለጻዎች ተካተው ይገኛሉ። እነዚህም፡- ስለ ቅጥያዎች (ገጽ፣4) ፣ ስለሐረግ (ገጽ፣23)፣ስለ አረፍተ ነገር (ገጽ፣27) እና ስለ አያያዥ ቃላት (ገጽ፣62) የቀረቡት ናቸው። ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ስለ ያዙት ርዕሰ ጉዳይ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ ከሰጡ በኋላ ይህንኑ መሰረት ያደረጉ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ያቀርባሉ። በመሆኑም ተማሪዎች አስቀድመው ሰዋስዋዊ ገለጻዎቹንና ምሳሌዎቹን ካጤኑ በኋላ መልመጃዎቹን ወደ መስራትና የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት ወደ መለማመድና ተግባራዊ ወደ ማድረግ ሂደት ይሸጋገራሉ ማለት ነው። ለዚህም አስረጅ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን ከመማሪያ መጽሐፉ የተወሰደ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ገለጻ እንመልከት።

1. ዓረፍተ ነገር

ዓረፍተ ነገር- የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፉ ቃላት ወይም ሐረጋት ቀንጅነት ነው፡፡

ዓ.ነገር በመደብ፣በጾታና በቁጥር የሚስማማ ቢያንስ ቢያንስ እንደ የስያሜ ጠባይ ያለው /ባለቤት/እና አንድ የድርጊት አመልካች ቃልን/ግስ/ የሚይዝ ነው፡፡ ሁለት መደበኛ ክፍሎች አሉት፡፡

ምሳሌ፡- አየለ መጣ፡፡ በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ ‹‹አየለ›› - ድርጊት ፈጻሚ /ባለቤት/ ሲሆን

‹‹መጣ›› - ድርጊት አመልካች/ግስ/ነው፡፡

ከላይ የቀረበውን ዓ.ነገር በስያሜ ቃሉና በድርጊት አመልካቹ ቃል ላይ ገላጮችን በመጨመር ማሳደግ ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ወፍራሙ አየለ ዛሬ መጣ፡፡

ለ. አጭር ወፍራሙ አየለ ዛሬ ጧት መጣ፡፡

ሐ. የጠፋው አጭር ወፍራሙ አየለ ዛሬ ጧት ብቻውን መጣ፡፡

1.1 ከላይ የቀረበውን ምሳሌ ተመልክታችሁ በስያሜ ቃላቱና በድርጊት አመልካች ቃላት ላይ ልዩ ልዩ ገላጮችን በመጨመር የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች አስረዝሙ፡፡

ሀ. ጃኬት ገዛች፡፡

ለ. መጽሐፍ አነበበ፡፡

. . . /7ኛ ክፍል፤ገጽ፣27/

ከቀረበው አስረጅ መገንዘብ እንደሚቻለው አስቀድሞ ስለ አረፍተ ነገር ምንነትና ክፍሎች፤ እንዲሁም አንድን አረፍተ ነገር አስፋፍቶ መጻፍ ስለሚቻልበት ዘዴ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻ አቅርቧል፡፡ ከዚያም ከገለጻውና ምሳሌዎቹ ጋር ተዛማጅነት ያለው መልመጃ/ጥያቄ ለተማሪዎች ሰንዝሯል፡፡ይህም አቀራረብ ተማሪዎች አስቀድመው ሰዋስዋዊ ገለጻውንና ምሳሌዎቹን እንዲገነዘቡ፤ ቀጥለው ደግሞ ግንዛቤያቸውን በመመርኮዝ ተዛማጅነት ያላቸውን መልመጃዎች ወደ መስራት እንዲሸጋገሩ የሚያደርጋቸው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት ተደራጅተው መቅረብ መቻላቸውን ያመላክታል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣*‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አስቀድመው ስለ ቋንቋው ስርአት ገለጻና ምሳሌዎችን በመስጠት የቋንቋውን ስርአት ወደመለማመድ የሚያሸጋግሩኝ ሆነው አግኝቻቸ ዋለሁ፡፡››* (ሰንጠረዥ ሰምንት፣መጠይቅ ቁጥር አስራ አንድ) በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ የ40% ተማሪዎች አዎንታዊ፣ የ10%

ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛልና የ50% ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ነው፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በበቂ ሁኔታ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት ተደራጅተው አለመቅረባቸውን ያሳያል፡፡ ምልከታውም የሚያስገነዝበው በዚህ ስልት ተደራጅተው የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ጥቂት(አራት ብቻ) መሆናቸውን ነው፡፡

መ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ

ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች እንዳየናቸው የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ሁሉ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እናገኛለን፡፡ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አስራ ሁለት የተለያዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልት ቀርበው ይገኙበታል፡፡ እነሱም ስለ ምዕላድና ቃላት (ገጽ፣1-2)፣ ስለ ቅጥያዎች (ገጽ፣4)፣ስለተፈጥሯዊና ሰዋስዋዊ ጾታ (ገጽ፣5)፣ስለ ቃል ክፍሎች (ገጽ፣11)፣ስለሐረግ (ገጽ፣17)፣ ስለ አረፍተ ነገር አይነቶች (ገጽ፣22)፣ ስለ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ (ገጽ፣36)፣ ስለ የስምና የግስ ገላጮች (ገጽ፣47)፣ ስለ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች (ገጽ፣49)፣ ስለ ጥብቀት(ገጽ፣53) ስለ አያያዦችና መስተዋድዶች (ገጽ፣144) እና ስለ ሰዋስዋዊ ስህተት (ገጽ፣230) የቀረቡት ይገኙበታል፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎች እንደየተስተምህሮ ባህሪያቸው በተለያዩ የአደረጃጀት ስልቶች የቀረቡ ይዘቶችን ለመማር የሚያስችላቸውን እድል ከፍቶላቸዋል ማለት ነው፡፡ በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንድ አይነት የአደረጃጀት ስልት ብቻ መከተል ትምህርቱን አሰልቺና የሚጠላ ሊያደርገው ይችላልና የተለያዩ የአቀራረብና የአደረጃጀት ስልቶችን እንደየሁኔታውና አስፈላጊነቱ አመጣጥኖ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ የሚከተለውን ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በአስረጅነት የተወሰደ አንድ ሰዋስዋዊ ገለጻ እንመልከት፡፡

<u>ማስታወሻ</u>

አረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ከሚኖራቸው የግስ ብዛት አኳያ ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

<u>ነጠላ ዐ.ነገር</u> የሚባለው በውስጡ አንድ ግስ ብቻ የያዘ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ዳፉርሳ በጠዋት ወደ ት/ቤት ሄደ፡፡

<u>ውስብስብ ዐ.ነገር</u> የሚባለው ከአንድ ግስ በላይ የያዘ ዐ.ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ኦርካይዶ በጠዋት ተነስቶ ወደ ት/ቤት ሄደ፡፡

3. ቀጥለው ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት እስተካክላችሁ ጻፉና
ነጠላና ውስብስብ ዐረፍተ ነገር በማለት መልሱ።
ምሳሌ፦1. ወደ ወጡ ላይ እነሱ (ያልተስተካከለ)
እነሱ ወደ ላይ ወጡ። (ነጠላ ዐ.ነገር)
2. ወደ ልመለስ አልቻልኩም፤ ስለዚህ ለመማር ግብርናዬ (ያልተስተካከለ)
ለመማር አልቻልኩም፤ ስለዚህ ወደ ግብርናዬ ልመለስ። (ውስብስብ)
3.1 የገዛውን ትናንት ነው ከበደ እያነበበ መጽሐፍ
3.2 ትምህርት እየሮጠ ወደ አየለ ቤት ሄደ
. . . /8ኛ ክፍል፤ገጽ22)

ከዚህ በላይ ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተወስዶ በአስረጅነት የቀረበውን ሰዋስዋዊ ይዘት ስንመለከት ይዞት ስለተነሳው ርዕሰ ጉዳይ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ ይሰጣል። በማስከተልም ለተማሪዎች ገለጻውንና ምሳሌዎቹን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸው ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ተዘጋጅተውላቸዋል ወይም ቀርበውላቸዋል። ይህም የሚያመለክተው ከመነሻው እንደተገለጸው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት ተደራጅተው የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች እንዳሉ ነው። ሰንጠረዥ ሰባት፣ መጠይቅ ቁጥር አስራ ሦስት ላይ እንደሚታየው ይህን አስመልክቶ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ ‹‹*በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎችንና ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርአት ለመለማመድ በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው ቀርበዋል።*›› በሚል ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ፣ የአንድ መምህር/ት አዎንታዊ ሲሆን፤ የአንድ መምህር/ት ደግሞ ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ነው። ይህም የሚያስገነዝበው ምንም እንኳ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በዚህ የአደረጃጀት ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቢኖሩም በቂ ወይም አጥጋቢ ናቸው ለማለት እንደማይቻል ነው። ሆኖም ይህ መጽሀፍ ከሌሎቹ ተተኳሪ መጻህፍት አኳያ ሲታይ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የተደራጁ በርከት ያሉ(አስራ ሁለት) ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ይዞ እንደሚገኝ ከተደረገው ፍተሻ ለመገንዘብ ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ለመገምገም ያለመ ነው፡፡ ጥናቱ አላማውን ከግብ ማድረስ ይችል ዘንድ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹን አቀራረብና አደረጃጀት በክለሳ ድርሳን ውስጥ ካቀረባቸው ንድፈ ሀሳቦች አንጻር ለመተንተንና ከመምህራንና ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ፣ ከመጻህፍቱ አዘጋጆች በቃል መጠይቅ ከተገኙ ምላሾች፤እንዲሁም በየደረጃው ከተዘጋጁ መርሐ ትምህርቶች ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማገናኘት ትንታኔውን ለማጠናከር ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት በግምገማው ሂደት የሚከተሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለማስተዋል ተችሏል፡፡

- ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁ አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ግልጽነት የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ተማሪዎችን ሊያደናግሩ የሚችሉ ገለጻዎች፣ ምሳሌዎች፣ትዕዛዞችና ጥያቄዎች በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ታይተዋል፡፡
- በአራቱም አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ትክክለኛነታቸውን ጠብቀው የቀረቡ ናቸው፡፡ ሆኖም በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ አልፎ አልፎ ስህተት የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መታየታቸው አልቀረም፡፡
- በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች (ከስነ-ድምጽ፣ከስነ-ምዕላድ፣ከስነ-አገባብና ከስነ-ፍች) የተውጣጡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ አቀራረባቸው ተመጣጣኝነት ወይም ሚዛናዊነት የጎደለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በተለይም ደግሞ ስነ-ድምጽ በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ዝቅተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ታይቷል፡፡
- በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኛዎቹ ውስብስብና ከተማሪዎች የመገንዘብ ወይም የመስራት አቅም በላይ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ የማይመጥኑና የየደረጃዎቹን መርሃ

ትምህርቶች መሰረት ያላደረጉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በመቅረባቸው ምክንያት የተገቢነት ችግር ተስተውሎባቸዋል፡፡

- በአራቱም አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኛዎቹ ተከታታይነታቸውን ጠብቀው በመማሪያ መጻህፍቱ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተከታታይነታቸው ወይም ድግግሞሻቸው ሲታይ ሚዛናዊነት የጎደለውና ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የመሄድ ሁኔታቸውም ድክመት የሚታይበት ሆኖ ተግኝቷል፡፡ እንዲሁም በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ አንዴ ብቻ ቀርበው ሳይደጋገሙ የቀሩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም መጻህፍቱ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት አንጻር ድክመት የሚታይባቸው መሆኑን ይጠቁማል፡፡
- አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ቀጣይነታቸው ወይም ተለጣጣቂነታቸው ሳይቋረጥ በአራቱም የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ሆኖም ከደረጃ ደረጃ ወይም ከክፍል ክፍል ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ክብደት እየጨመሩ የመሄድ ሁኔታቸው ሲፈተሽ ከፍተኛ ድክመት የሚታይባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም ቀጣይነታቸውን ያልጠበቁ ወይም የመቆራረጥ ችግር የሚታይባቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች መኖራቸውንም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልት ቀርበው ወይም ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በአራቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኛዎቹ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአደረጃጀት ስልት ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ሁለቱን የአደረጃጀት ስልቶች አመጣጥኖ በመጠቀም ረገድ ድክመት ታይቶባቸዋል፡፡

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳብ

በዚህ ጥናት ተተኳሪ አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የታዩ ጠንካራ ጎኖች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የዚህ ጥናት አቅራቢ አስተያየት ነው፡፡ የመማሪያ መጻህፍቱ እንደገና ሲዘጋጁ ወይም ሲሻሻሉ በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የታዩት ድክመቶች እርምት

ወይም ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይገባልና የሚከተሉትን የመፍትሔ ሀሳቦች ለመጠቆም ተሞክሯል።

- አልፎ አልፎ በሰዋስው ትምህርት ይዘት ገለጻዎች፣ ምሳሌዎች፣ የመልመጃ ትዕዛዞችና ጥያቄዎች ላይ የታዩ የግልጽነት ችግሮችን ማስተካከል፤
- በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች የተውጣጡ ወይም ተመጣጣኝነታቸውንና ሚዛናዊነታቸውን የጠበቁ ሆነው እዲቀርቡ ማድረግ፤
- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች በየደረጃው ሊማሯቸው የሚገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው መቅረባቸው ብቻ ፋይዳ አይኖረውም። በመሆኑም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከምዕራፍ ምዕራፍ ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ እንዲሄዱ ማድረግ ወይም ይህን ማረጋገጥ፤
- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሁሉም የእርከኑ መጻህፍት ውስጥ ቀጣይነትና ተለጣጣቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤እንዲሁም ከደረጃ ደረጃ ወይም ከክፍል ክፍል ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ እንዲሄዱ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤
- እንደ አስፈላጊነቱና የተማሪዎችን ዳራ መሰረት በማድረግ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት አደራጅቶ ማቅረብ፤ወደ አንዱ ስልት ላይ ብቻ አለማዘንበል፤
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው የትምህርት ባለሙያዎች፣መምህራንና ተማሪዎች በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት እንዲገመግሙ እድል መስጠት ወይም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ግብረመልሶችን ተግባር ላይ ማዋል፤
- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እንዲያዘጋጁ ቢደረግ፤ ወይም ደግሞ ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ወይም አካላት ግንዛቤያቸውን ሊያበለጽግ የሚችል ስልጠና፣ የልምድ ልውውጥ፣ የመሳሰሉትን እንዲያገኙ ማድረግ።

# ዋቢ ጽሁፎች


ሁሉባንተ አደመ (1994) ‹‹በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተዘጋጁ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አደረጃጀት ግምገማ›› የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ። አ.አ.ዩ።

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) ‹‹በአዲስ አበባ ከተማና አማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ። አ.አ.ዩ።

ባየ ይማም። (1987) ። <u>የአማርኛ ሰዋስው።</u> አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ።

—————————። (2000) ። <u>የአማርኛ ሰዋስው።</u> የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማህበር።

ተስፋዬ በቀለ (1993) ‹‹በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለስምንተኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ። አ.አ.ዩ።

ጌታሁን አማረ። (1990) ። <u>ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።</u> አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

—————————። (1993) ። ‹‹በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለአምስተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ።›› <u>የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ መጽሔት።</u> ቁጥር 11፣53-67።

Batston, R. (1994). <u>Language Teaching: Grammar</u>. Oxford: OUP.

Celce- Murcia, M. and Hills, S. (1988). <u>Techniques and Resources in Teaching Grammar</u>. Oxford: OUP.

Cross, D. (1991). <u>A practical Handbook of Language Teaching</u>. London: Cassel Villiers House.

Cunningsworth, A. (1995). <u>Choosing Your Course Book</u>. Oxford: Heineman.

Dawson, C. (1984). <u>Teaching English as a Foreign Language</u>. Edinburgh: Nelson Harp.

Edge, J. (1993). <u>Essentials of English Language Teaching</u>. London: Longman.

Good, C.V. (ed.) (1973). Dictionary of Education. New York: Mc Graw Hill Book Company.

Grant, N. (1987). Making the Most of Your Text Books. London: Longman.

Harmer, J. (1987). Teaching and Learning Grammar. London: Longman.

————. (1991). The Practice of English Language Teaching. London: Longman.

Krashen, S. (1987). Principles and Practice in Second Language Acquisition. London: Prentice Hall International.

Larsen- Freeman, D. (1986). Techniques and Principles in Language Teaching. Oxford: OUP.

————. (1991). "Teaching Grammar". In Celce- Murcia, M.(ed.), Teaching English as a Second or Foreign Language.(pp. 279-295). Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Leech,G. (1994). "Students' Grammar Teachers' Grammar- Learners' Grammar" in Bygate, M., Tonkyn, A. and Williams, E. (ed.). Grammar and the Language Teacher. New York: Prentice Hall.

Mitchell, R. (1994)." Grammar, Syllabuses and Teachers." In Bygate, M. 'etal.' (eds.), Grammar and the Language Teacher. (pp.90-104). New York: Prentice Hall.

Nunan, D. (1988). Syllabus Design. Oxford: OUP.

Richards, J.C. and Rodgers, T. (1986). Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: CUP.

Robinson, P.C. (1991). ESP Today: A practitioner's Guide. New York: Prentice Hall.

Rowntree, D. (1981). A Dictionary of Education. London: Harper and Row Publishers.

Sheldon, L.E. (1988)." Evaluating ELT Text Book and Materials." ELT Journal. Vol.42, No.4,237-246.

Stern, H.H. (1983). Fundamental Concepts of Language Teaching. Oxford: OUP.

Stevick, E.W. (1986). Images and Options in the Language Classroom. Cambridge: CUP.

Swan, M. (1994). "Design Criteria for Pedagogical Language Rules." In Bygate, M. 'etal.' (eds.), Grammar and the Language Teacher. (pp.45-55). New York: Prentice Hall.

Taba, H. (1962). Curriculum Development: Theory and Practice. New York: Harcourt Brace Jovanovich.

Tonkyn, A. (1994). " Introduction: Grammar and the Language Teacher." In Bygate, M.'etal.' (eds.), Grammar and the Language Teacher. (pp.1-14). New York: Prentice Hall.

Tyler, R.W. (1949). Basic Principles of Curriculum and Instruction. Chicago: The University of Chicago Press.

Ubanya, P. (1955). Teaching Methods Across Curriculum. Collini International Textbooks: London.

Ur, P. (1988). Grammar Practice Activities. Cambridge: CUP.

——————. (1996). A course in Language Teaching. Cambridge: CUP.

Vassilakis, G. (1997). " Materials and Methods: Need They be in Conflict?" Paper presented at TESOL Greece Saturday Seminar on Material Choice and Development in the EFL Classroom.

## አባሪ አንድ

### የመማሪያ መጻህፍቱ አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ ምላሽ

**ሀ. የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ**

ቀን፡- 03/05/2004 ዓ/ም

ቦታ፡- ሐዋሳ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ (በቃለ መጠይቅ ተደራጊው ቢሮ ውስጥ)

ሰዓት፡- 9፡20 - 10፡05

I. የአዘጋጁ/የአሻሻዩ ዳራ

ሀ. መጽሐፉን ባዘጋጁበት ጊዜ የነበረዎ የትምህርት ደረጃ፡- 12+4

ለ. መጽሐፉን ባዘጋጁበት ጊዜ የነበረዎ ሀላፊነት፡- መምህር (ይርጋለም አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)

ሐ. ሙያዎ፡- መምህርነት

መ. የትምህርት መስክ፡- አማርኛ/የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ

II. ጥያቄዎች

1. በ1997 እና በ1998 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ከዋሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች/አሻሻዮች ውስጥ አንዱ እርስዎ ነዎት፤እርስዎ የተሳተፉባቸው መጻህፍት የትኞቹ ናቸው?

   ምላሽ፡- *‹‹የተሳተፍኩት በስድስተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍና በመምህሩ መምሪያ ላይ ሲሆን ይኸውም በአሻሻይነት ሳይሆን በአዘጋጅነት ነው፡፡››*

2. ወደ መማሪያ መጽሐፉና የመምህሩ መምሪያ ዝግጅነት ከመግባታችሁ በፊት ምን ምን ቅድመ ዝግጅቶች አደረጋችሁ? ለምሳሌ ስልጠና፣ ወርክሾፕ፣ የልምድ ልውውጥ፣ የመሳሰሉት?

   ምላሽ፡- *‹‹ምንም አይነት ቅድመ ዝግጅት አልነበረም፡፡ ስልጠና፣የልምድ ልውውጥ፣ወዘተ ያልካቸውን ነገሮች ሁሉ አላደረግንም፡፡ ከየምናስተምርበት ትምህርት ቤት የክልሉ ትምህርት ቢሮ በደብዳቤ ጠራን፡፡ ከዚያም መርሃ ትምህርቱንና የጽህፈት መሳሪያዎችን አድሎን ባጀቱ ሊቃጠል ስለሆነ በሚል ምክንያት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመማሪያ መጽሐፉን እንድናዘጋጅ ትዕዛዝና መመሪያ ተሰጠን፡፡ይኸው ነው፤በጥድፊያ ነበር የምንሰራው፡፡ እናዘጋጅ የነበረውም ሐዋሳ ታቦር ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት*

ቤት ውስጥ እየዋልንና እያደርን ነበር። የክልሉ ትምህርት ቢሮ ፍራሽ አስገብቶልን እዛው ነበር የምናድረው ቁርስ፣ምሳና እራት፣ሻይ ቡና እዚያው ነበር የሚመጣልን። ትምህርት ቢሮው ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ያደርግብን ነበር።››

3. ሥራውን በግል ወይስ በቡድን የሰራችሁት?

**ምላሽ፡-** ‹‹ለሁለት ለሁለት (ጥንድ ጥንድ) ሆነን ነው ያዘጋጀነው። እኔና አብሮኝ የነበረው በመጀመሪያ ምዕራፎችን ተከፋፈልን። በየግላችን ልዩ ልዩ ምንባቦችንና መልመጃዎችን ካዘጋጀን በኋላ የሰራነውን ተቀያይረን ተራረምን። እርስ በርስ ሀሳብ እየተለዋወጥን እርምት አደረግን። በዚህ ሁኔታ ነው ያዘጋጀነው።››

4. ያቀረባችኋቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከየት መረጣችሁ? ለምሳሌ ከመርሃ ትምህርት? ከፍሰት ሰንጠረዥ?››

**ምላሽ፡-** ‹‹መነሻ ያደረግነው መርሃ ትምህርቱን ነው። ነገር ግን የግላችን የሆኑ የተለያዩ ማቴሪያሎችንም በአጋዥነት ተጠቅመናል፤ ስለዚህም መርሃ ትምህርቱን ብቻ ተመርኩዘን ሳይሆን እኛም ለደረጃው ይመጥናሉ ብለን ያመንባቸውን ሰዋስዋዊ ይዘቶች አካተናል ማለት ነው።››

5. ከመርሃ ትምህርቱ ወጣ ለማለት ወይም መርሃ ትምህርቱ ውስጥ ካሉት ውስጥ ላለማካተት አስገዳጅ ሁኔታዎች ገጥመዋችሁ ነበር?

**ምላሽ፡-** ‹‹የገጠመን ችግር የለም። መርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች በሙሉ በመጽሐፉ ውስጥ አካተናል። እንዲያውም ቀደም ሲል ከነበሩት የመማሪያ መጻህፍት ጠቃሚ ናቸው ያልናቸውንም ይዘቶች ጨምረንበታል።››

6. በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው?ለምሳሌ፡-

**ከግልጽነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** ‹‹መጽሐፉን ለማዘጋጀት የተሰጠን ጊዜ በጣም አጭር ከመሆኑ የተነሳ የሩጫና የይድረስ ይድረስ ስራ ነው የሰራነው። በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የግልጽነት ችግርም ሆነ ሌሎች ስህተቶች አይኖሩም ብዬ አላምንም።››

**ከትክክለኛነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** ‹‹ከዚህም አኳያ የመረጥናቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሙሉ ትክክል ናቸው የሚል እምነት የለኝም። ምክንያቱም መርሃ ትምህርቱ ራሱ ችግር አለበት።

*የክልሉን ተማሪዎች በደንብ ግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም አዘገጃጀቱ።›› *

**ከተገቢነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ይህም ቀደም ሲል እንዳልኩህ መርሃ ትምህርቱ ላይ ችግር የሚታይ ከሆነ እኛ የመረጥናቸው ይዘቶችም ላይ ችግር መኖሩ አይቀርም። ሁሉም ይዘቶች ተገቢ ናቸው ለማለት የሚቻል አይመስለኝም። አልፎ አልፎ ችግሮ ሊኖሩባቸው ይችላል።››*

**ከሚዛናዊነት/ተመጣጣኝነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ ያቀረብናቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አንተ ቅድም እንዳልከኝ ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች ተመጣጥነው ቀርበዋል ብዬ አላምንም። ስናዘጋጅ ይህን ታሳቢ አላደረግንም።አስቀድሞ ምንም የማሰቢያ፣የማሰላሰያ ጊዜ አልነበረንም።ተጠራን፣መጣን ፣ወዲያው ወደ ዝግጅት ገባን።››*

7. በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው?

ለምሳሌ፡-

**ከተከታይይነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ተከታታይነት ጠብቀናል ብዬ ልልህ አልችልም። ደረጃ በደረጃም እያሳደግናቸው የሄድን አይመስለኝም። ይህንን ሁኔታ ከኔ ጋር አብሮ ያዘጋጀውን ሰው ካገኘኸው ሊያረጋግጥልህ ይችላል። በአጠቃላይ ተከታታይነትን በተመለከተ ሀሳቡም አልነበረም።››*

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትን በተመለከተ?

ምላሽ፡- *‹‹አንተ የአደረጃጀት ስልቶች ወይም መርሆዎች የምትላቸውን ሁሉ አልተከተልንም። እውነቱን ለመናገር ግንዛቤውም አልነበረንም፤ ልምዱም የለንም። እኛ ያዘጋጀነው ቀደም ሲል የነበሩትን የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት በሞዴልነት በመውሰድ ነው።››*

**ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልትን በተመለከተ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ይህን በተመለከተ ምንም ጊዜውም ግንዛቤውም አልነበረንም አልኩህ እኮ!››*

8. ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ተናጠላዊ ወይስ አገባባዊ በሆነ መንገድ ነው ያቀረባችኋቸው?

**ምላሽ፡-** *‹‹የመመጣጠናቸው ሁኔታ ሲታይ ችግር ሊኖርበት ይችል ይሆናል እንጂ ተናጠላዊም አገባባዊም አቀራረብ የተጠቀምን ይመስለኛል።››*

9. የአርትኦት ስራውንና የማጣሪያ ንባቡን እንዴት አከናወናችሁት?

ምላሽ፡- ‹‹ሁለት ሆነን አዘጋጀን፤ኤዲት የሚያደርገው ሌላ ሰው ነበር። እኛና ኤዲተሩ የተስማማንበት ስራ ለጸሐፊዋ ይሰጣል። ከዚህ በኋላ ነው ለህትመት የተላከው››

10. መማሪያ መጽሐፉ ታትሞ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የተመለከቱት ወይም ከሌላ ሰው/አካል ያገኙት ምጋቤ ምላሽ አለ?

ምላሽ፡- ‹‹ከሌላ ሰው ወይም አካል ምንም የደረሰኝ አስተያየት የለም። ወደ ፊት ከአንተ እጠብቃለሁ (ሳቅ ብለው)። ከታተመ በኋላ መጽሐፉን በግሌ አይቼዋለሁ። እሱን ብቻም ሳይሆን አሁን ያው እንደምታየኝ እዚህ ኮሌጅ ውስጥ እያስተማርኩ ስለ ሆነ በእርከኑ ያሉትን ሁሉንም የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች ሰብስቤ በደንብ እያየኋቸው ነው። በመሆኑም አንተ በምትለው በሰዋስው ይዘት ላይ ብቻም ሳይሆን በሌሎቹም ይዘቶች ላይ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ። መጻህፍቱ በሙሉ እንደገና መዘጋጀት ያለባቸው ናቸው።››

11. በአጠቃላይ ስለ መጽሐፉ ዝግጅት ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን የሚሉት ካለ?

ምላሽ፡- ‹‹አንድ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ቅድመ ዝግጅት መኖር አለበት። አንተ ቅድም ያልካቸው ስልጠና፣ወርክሾፕ፣የልምድ ልውውጥ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ጠቃሚ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በተጨማሪም በቂ ጊዜ ሊሰጥ ይገባል። ገና ለገና ባጀት ይቃጠላል በማለት የክልሉ ትምህርት ቢሮ እኛን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጁ ማለቱ አንድ ሃላፊነት ከተጣለበት ተቋም የሚጠበቅና ተገቢም አይመስለኝም። እኛ እንድናዘጋጅ የጠሩን ወይም የጋበዙን አካላት ምን ቅድመ ሁኔታ እንደሚያስፈልገንና ምን ያህል ጊዜ እንደሚበቃን በደንብ የተረዱ አይመስለኝም። ይህ ለወደፊቱ ሊታረም ይገባል። በአጠቃላይ ዝግጅቱ የተዋጣለት ነው የሚል እምነት የለኝም። መርሃ ትምህርቱ ራሱ ይህንን ቋንቋ ማነው የሚማረው? የሚለውን ጥያቄ በደንብ የሚመልስ አይመስለኝም። በመሆኑም መርሃ ትምህርቱም ሆነ የመማሪያ መጻህፍቱ እንደገና በደንብ ታስቦባቸው ሊዘጋጁ ይገባል እልሃለሁ።››

ጠያቂ፡- የስራ ጊዜዎን በመስዋትና በቀናንት ስለተባበሩኝ ከልብ አመስግንዎታለሁ!

ተጠያቂ፡- ምንም አይደለም፤ ከዚህ የበለጠም ነገር ተባብረረን መስራት ይገባናል።

ለ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ

ቀን፡- 06/05/2004ዓ.ም

ቦታ፡- በመምህርቷ መኖሪያ ቤት (ይርጋለም ከተማ)

ሰዓት፡- 2፡45 - 4፡10

I. የአዘጋጇ/የአሻሻዩዋ ዳራ

ሀ. መጽሐፉን ባዘጋጁበት ጊዜ የነበረዎ የትምህርት ደረጃ፡- 12+4

ለ. መጽሐፉን ባዘጋጁበት ጊዜ የነበረዎ ሃላፊነት፡- መምህር (ይርጋለም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት)

ሐ. ሙያዎ፡- መምህርነት

መ. የትምህርት መስክ፡- አማርኛ (የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ)

II. ጥያቄዎች

1. በ 1997 እና በ1998 ዓ.ም ታትመው ስራ ላይ ከዋሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች/አሻሻዮች ውስጥ አንዷ እርስዎ ነዎት፤ የተሳተፉባቸው መጻህፍት የትኞቹ ናቸው?

   ምላሽ፡- *‹‹እንዳዘጋጅ የተሳተፍኩባቸው መጻህፍት የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ ናቸው፡፡ በወቅቱ ስራው ማሻሻል ሳይሆን ዝግጅት ነው፡፡››*

   ለአዘጋጅነት እንዴት ሊመረጡ ቻሉ? ልምድ ነበረዎት?

   ምላሽ፡- *‹‹ከዛ በፊት ምንም አይነት ልምድ አልነበረኝም፡፡ በአዘጋጅነት ልመረጥ የቻልኩበት ዋናው ምክንያት በማስተምርበት ትምህርት ቤት በወቅቱ ከፍተኛ የሆነ የስራ አፈጻጸም ውጤት ስለነበረኝ ነው፡፡ በዚህ መስፈርት ነው የክልሉ ትምህርት ቢሮ በአዘጋጅነት እንድሳተፍ የመረጠኝ፡፡ ከዛ በፊት ምንም አይነት መጽሐፍ ላይ ተሳትፌ አላውቅም፡፡ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በደብዳቤ ጠራኝ፤ አዋሳ ሄጄ በዝግጅቱ ሂደት ተሳተፍኩ፡፡››*

2. ወደ መማሪያ መጽሐፉና የመምህሩ መምሪያ ዝግጅት ከመግባታችሁ በፊት ምን ምን ቅድመ ዝግጅት አደረጋችሁ? ለምሳሌ ስልጠና፣ ወርክሾፕ፣ የልምድ ልውውጥ፣ የመ ሳሰሉት?

   ምላሽ፡- *‹‹በክልሉ ትምህርት ቢሮ አማካይነት ተጠርተን አዋሳ ሄድን፤ሃላፊነቱን*

*እንደምንወስድ ተነገረን፤ ከዛም ሁለት ሁለት እያደረጉ አጣመሩን። ከኔ ጋር የነበረው ቀደም ሲል የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅቷል፤ ልምድ ነበረው ፤ እንግዲህ የልምድ ልውውጡ በእኔና በሱ መካከል እንጂ በክልሉ ትምህርት ቢሮ በኩል የተደረገልን ምንም ቅድመ ዝግጅት የለም። ለዝግጅቱ የሚያስፈልጉንን ግብአቶች አድለውናል። ለምሳሌ የጽህፈት መሳሪያዎች፤መርሃ ትምህርቱን፤ የመሳሰሉትን ከሰጡን በኋላ ወዲያውኑ ነው መጽሐፉን ወደ ማዘጋጀት የገባነው። ሃያ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው መጽሐፍ እንድናዘጋጅ የተደረገው።››*

3. ስራውን በግል ወይስ በቡድን የሰራችሁት?

   ምላሽ፦ *‹‹ቅድም እንደነገርኩህ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሁለት ሁለት አድርጎ ነው የመደበን። እያንዳንዱን ስራ በጋራ (ለሁለት) ነው የሰራነው። አዋሳ ታቦር ትምህርት ቤት ነበር እየተገናኘን የምናዘጋጀው። ባዘጋጀነው ስራ ላይ እንወያያለን፤ እንከራከራለን። እያንዳንዱ ዝግጅት ውስጥ የሁለታችንም አስተዋጽኦ ወይም እጅ አለበት።››*

4. ያቀረባችኋቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከየት መረጣችሁ? ለምሳሌ ከመርሃ ትምህርት ከፍሰት ሰንጠረዥ?

   ምላሽ፦ *‹‹በዋነኝነት መሰረት ያደረግነው መርሃ ትምህርቱን ነው። ሌሎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከባየና ከጌታሁን መጻህፍት መርጠንና ለደረጃው እንዲመጥን አድርገን አካተናል። በመሆኑም ከመርሃ ትምህርቱ ውጪ የራሳችንን ልዩ ልዩ መርጃ መሳሪያዎች በመጠቀም ሰዋስወዊ ይዘቶችን ጨምረንበታል።››*

5. ከመርሃ ትምህርቱ ወጣ ለማለት ወይም መርሃ ትምህርቱ ውስጥ ካሉት ውስጥ ላለማካተት አስገዳጅ ሁኔታዎች ገጥመዋችሁ ነበር?

   ምላሽ፦ *‹‹በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች በሙሉ ያካተትን ይመስለኛል። የሚደጋገሙ የመሰሉንን እየተውንም የራሳችንን ጨምረንበታል። በአጠቃላይ መጽሐፉ ክልላዊ ይዘት እንዲኖረው የቻልነውን ያህል ጥረናል።››*

6. በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው? ለምሳሌ፦

   ከግልጽነት አኳያ?

   ምላሽ፦ *‹‹የግልጽነት ችግር አለበት ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ምንም ልምድና ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ የተዘጋጀ እንደመሆኑ የተለያዩ የግልጽነት ችግሮች ተፈጥረዋል።*

*ይህንን ራሴም መጽሐፉ ከታተመ በኋላ አይቼው አረጋግጫለሁ።››*

**ከትክክለኛነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ያቀረብናቸውን ይዘቶች ከትክክለኛነታቸው አኳያ ሳያቸው ያደረግነው ጥረት ከሞላ ጎደልም ቢሆን የተሳካ ይመስለኛል።ያን ያህል የጎላ ችግር ያለባቸው አይመስለኝም።››*

**ከተገቢነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ይዘቶቹ የተገቢነት ችግር አለባቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ትምህርቱን የሚጀምሩት ከ3ኛ ክፍል ነው፤ ሁለተኛ ቋንቋቸው ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያቀረብናቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለተማሪዎቹ የሚመጥኑ አይመስለኝም። የመጽሐፉን አዘገጃጀት አሁን ላይ ሆኜ ሳየው ከአፍ መፍቻ ቋንቋ መጽሐፍ አዘገጃጀት ብዙም የተለየ ሁኔታ ያለው አይደለም።››*

**ከሚዛናዊነት/ተመጣጣኝነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹እኛ ስናዘጋጅ ለሁሉም የሰዋስው ክፍሎች ትኩረት የሰጠን ይመስለኛል። ምክንያቱም መርሃ ትምህርቱ ውስጥ በመኖራቸው ነው። ሁሉም አይነት የሰዋስው ክፍሎች ይኑሩበት እንጂ ሚዛናዊነታቸው ላይ እርግጠኛ አይደለሁም።››*

7. ከመርሃ ትምህርቱ የተጠቀሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው?ለምሳሌ፡-

**ከተከታታይነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹አንድ ይዘት ተከታታይነት ከሌለው በተማሪዎች ዘንድ በቀላሉ ሊረሳ ስለሚችል በመጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ እንዲደጋገም ለማድረግ ሞክረናል። ነገር ግን ለሁሉም ይዘቶች ድግግሞሽ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥተናል ብዬ አላምንም። የስፋትና የጥልቀት ወይም የክብደት ደረጃ እየጨመረ የመሄድ ሁኔታን አላገናዘብንም ወይም ግምት ውስጥ አላስገባንም። ያው እንደነገርኩህ ይሄ ከዝግጅት ጊዜው እጥረት አኳያ የተፈጠረ ችግር ነው። አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው ያዘጋጀነው።››*

**ከቀጣይነት/ከተለጣጣቂነት አኳያ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ተለጣጣቂነትን ጠብቋል ማለት አይቻልም። በተለይ ከአምስተኛ እስከ ሰባተኛ ያሉትን መጻህፍት አላየንም፤ ከነዚህ መጻህፍት አዘጋጆች ጋርም ተወያይተን አልሰራንም። እኛ ያዘጋጀነው የስምንተኛ ክፍሉን መርሃ ትምህርት ብቻ በማየት ነው።*

*ከታች ካሉት ይልቅ እኛ ያየነው የዘጠነኛ ክፍሉን አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች ወደ ፊት እንዳይቸገሩ በማለት ነው እንደዚህ ያደረግ ነው።››*

**ከዝርዝር ወደ አጠቃለይ የአደረጃጀት ስልትን በተመለከተ?**

**ምላሽ፡-** *‹‹ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስለሚሉት የአደረጃጀት ዘዴዎች እኔም ሆንኩ አብሮኝ የነበረው ባልደረባዬ ምንም የምናውቀው ጉዳይ አልነበረም። አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ሁለቱንም ስልቶች የተጠቀምን ይመስለኛል። ይህን ያደረግነው ግን እውቀቱ ወይም ግንዛቤው ኖሮን ሳይሆን ቀደም ሲል የነበረውን የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በዝግጅታችን ወቅት በሞዴልነት እንጠቀምበት ስለነበር ነው።››*

8. ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ተናጠላቂ ወይስ አገባባዊ በሆነ መንገድ ነው ያቀርባችኋቸው?

   **ምላሽ፡-** *‹‹ተናጠላዊም አገባባዊም አቀራረብ ተጠቅመናል። ጥቅምና ጉዳቱን አመዛዝነን ሳይሆን ዝም ብለን ነው ሁለቱንም አቀራረቦች የተጠቀምነው።››*

9. የአርትኦት ስራውንና የማጣሪያ ንባቡን እንዴት አከናወናችሁት?

   **ምላሽ፡-** *‹‹አርታኢ ነበረን። እኔና ባልደረባዬ ያዘጋጀነውን አርታኢው ያየው ነበር። አርታኢው ያየው ስራ ወደ ህትመት ገብቷል። ከታተመ በኋላ ግን ብዙ ችግሮች ተፈጥረውበት አይቻለሁ። በዚህም በጣም ነው ያዘንኩት።››*

10. የመማሪያ መጽሐፉ ታትሞ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የተመለከቱት ወይም ከሌላ ሰው/አካል ያገኙት ምጋቤ ምላሽ አለ?

    **ምላሽ፡-** *‹‹ከታተመ በኋላ ራሴ አይቼው በጣም ደንግጫለሁ። ምክንያቱም በርካታ ችግሮች እንዳሉበት አስተውያለሁ። በደረጃው የሚያስተምሩበት አንዳንድ መምህራንም ችግር እንዳለበት ነግረውኛል፤ አስተያየትም ሰጥተውኛል። መጽሐፉ ለከተማ ተማሪዎች ምንም አይልም፤ ለገጠር ተማሪዎች ግን ከባድ ነው ይሉኛል። እኔም ይህንን ሁኔታ በደንብ ተረድቻለሁ። በጣም የሚያሳዝነው ግን ይህንኑ መጽሐፍ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ምንም ማሻሻያ ሳያደርግበት ወይም እኛን አስተያየት ሳይጠይቅ በ 2003ዓ.ም እንደገና ለህትመት ማብቃቱ ነው።››*

11. በአጠቃላይ ስለ መጽሐፉ ዝግጅት ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን የሚሉት ካለ?

    **ምላሽ፡-** *‹‹ጠንካራ ጎኖች የምላቸው፡- መርሃ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ መሰረት ማድረጋችን፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ (አንድ ወር ባልሞላ) መጽሐፉን ማዘጋጀታችን፤*

*የተለያዩ መጻህፍትን በማጣቀሻነት ለማየት መሞከራችንና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ዕለት በዕለት የእኛን ዝግጅት እየተከታተለ ማበረታታቱ እንደ ጠንካራ ጎን የማያቸው ሲሆኑ፤ እንደ ድክመት የማያቸው ደግሞ፡- ይህንን ሃላፊነት እኛ መቀበል ሳይገባን መቀበላችን፤ ቀደም ሲል የነበሩትን መማሪያ መጻህፍት አለመገምገማችን፤ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ያለምንም ቅድመ ዝግጅት፤ ስልጠና፣ የልምድ ልውውጥ፣ የመሳሰሉትን ሳያደርግ እኛ በቀጥታ ለዚያውም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንድናዘጋጅ ማድረጉ እንደ ትልቅ ድክመት ነው የማያቸው፡፡ ወደፊት እነዚህ ነገሮች ሊታረሙ ይገባል፡፡ ለተማሪዎች ከታሰበ ዝግጅቱ በቂ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ነው የምለው፡፡››*

ጠያቂ፡- የሥራ ጊዜዎን በመሰዋትና በቀናነት ስለተባበሩኝ ከልብ አመሰግንዎታለሁ!

ተጠያቂ፡- ምንም አይደለም፤ አንተ እንኳ ከሩቅ መጥተህ የለም ወይ፡፡

# አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ውድ መምህር/ት

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጁ አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት አስመልክቶ መምህራን ያላቸውን አስተያየት መሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ እርስዎም በመጠይቁ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብና አስተያየትዎን በመሙላት ይተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ውድ ጊዜዎን በመሰዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበሩኝ በቅድሚያ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

I. አጠቃላይ መረጃ

1. ዕድሜ -----------------------
2. ጾታ ------------------------
3. የትምህርት ደረጃ ---------------------
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ፡- አብይ ------------ ንዑስ -------------
5. የአገልግሎት ዘመን ------------------
6. የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ -------------------
7. የትምህርት ቤቱ ስም ------------------------

II. የመማሪያ መጻህፍቱን አስመልክቶ የቀረቡ ጥያቄዎች አመላለስ መመሪያ

ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አምስት አምስት ምርጫዎች ቀርበዋል፡፡እነሱም፡- 5-በጣም እስማማለሁ፣4-እስማማለሁ፣ 3-መወሰን ያስቸግረኛል፣2-አልስማማም እና 1-በጣም አልስማማም የሚሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም እርስዎ ተገቢ ነው ብለው ባሰቡት መልስ ቁጥር ትይዩ ይህን ምልክት (x) በማድረግ ያመልክቱ፡፡

አመሰግናለሁ!

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች/ማስታወሻዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 2 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትእዛዞች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 3 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ምሳሌዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 4 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃ ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 5 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ስህተት የሆኑ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ | | | | | |
| 6 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰወስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ስለ አማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ማወቅ የሚገባቸውን የሚያሳውቁ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች የመስራት አቅም ወይም የክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ የተውጣጡ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ | | | | | |
| 10 | በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ጨምረዋል፡፡ | | | | | |
| 11 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ካሉበት የክፍል ደረጃ በፊት የተዋወቋቸው ናቸው፡፡ | | | | | |
| 12 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርአት ራሳቸው በሂደት እንዲያውቁት በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 13 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሰዋስው ትምህርት ገለፃዎችንና ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርአት ለመለማመድ በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ | | | | | |

14. ስለ መማሪያ መጽሐፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ያለዎትን ተጨማሪ አስተያየት ይግለጹ፡- --------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

**የተከበራችሁ ተማሪዎች**

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጁ አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት አስመልክቶ ተማሪዎች ያላቸውን አስተያየት መሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ በመጠይቁ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ አስተያየታችሁን በመሙላት ትተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ውድ ጊዜያችሁን በመሰዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበራችሁኝ በቅድሚያ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

**I. አጠቃላይ መረጃ**

1. ዕድሜ ----------------
2. ጾታ ------------------
3. የክፍል ደረጃ ------------------------------
4. የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------

**II. የመማሪያ መጻህፍቱን አስመልክቶ የቀረቡ ጥያቄዎች አመላለስ መመሪያ**

ቀጥሎ በቀረበላችሁ ሰንጠረዥ ውስጥ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አምስት አምስት ምርጫዎች ቀርበዋል፡፡ እነሱም፡- 5-በጣም እስማማለሁ፣ 4-እስማማለሁ፣ 3-መወሰን ያስቸግረኛል፣ 2-አልስማማም እና 1-በጣም አልስማማም የሚሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም እናንተ ተገቢ ነው ብላችሁ ባመናችሁበት መልስ ቁጥር ትይዩ ይህን ምልክት (x) በማድረግ አመልክቱ፡፡

አመሰግናለሁ!

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች/ማስታወሻዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ትእዛዞች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ምሳሌዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 5 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስለ አማርኛ ቋንቋ ስርአት ማወቅ የሚገባኝን ነገር ያሳውቁኛል፡፡ | | | | | |
| 6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመገንዘብ ወይም ከመስራት ችሎታዬ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ቀርበውልኛል፡፡ | | | | | |
| 8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አሁን ካለሁበት የክፍል ደረጃ በፊት ተዋውቂያቸው ነበር፡፡ | | | | | |
| 9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ካለፈው አመት የጠነከሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 10 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቋንቋውን ስርአት ራሴ በሂደት እንዳውቅ ወይም እንድደርስበት ለመለማመድ የሚያስችሉኝ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 11 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አስቀድመው ስለቋንቋው ስርአት ገለፃና ምሳሌዎችን በመስጠት የቋንቋውን ስርአት ወደ መለማመድ የሚያሸጋግሩኝ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ | | | | | |

12. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አስመልክቶ ያለህን/ሽን ተጨማሪ አስተያየት ግለፅ/ጭ፡-

______________________________________________

______________________________________________

# አባሪ አራት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍትን ላዘጋጁ/ላሻሻሉ ባለሙያዎች የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ፡፡**

**I. የአዘጋጁ/የአሻሻዩ ዳራ**

**ሀ. መጽሐፉን ባዘጋጁበት ጊዜ የነበረዎ የትምህርት ደረጃ ፡- ------------------------**

**ለ. መጽሐፉን ባዘጋጁበት ጊዜ የነበረዎ ሃላፊነት ፡- ----------------------------**

**ሐ. ሙያዎ ፡- ----------------------------------**

**መ. የትምህርት መስክ ፡- --------------------------**

**II. ጥያቄዎች**

1. በ 1997 እና በ 1998 ዓ.ም ታትመው ስራ ላይ ከዋሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች/አሻሻዮች ውስጥ አንዱ እርስዎ ነዎት፤ እርስዎ የተሳተፉባቸው መጻህፍት የትኞቹ ናቸው?
2. ወደ አማርኛ መማሪያ መጻህፍቱ ዝግጅት ከመግባታችሁ በፊት ምን ምን ቅድመ ዝግጅቶችን አደረጋችሁ? (ስልጠና፣ ወርክሾፕ፣ የልምድ ልውውጥ፣...)
3. ስራውን በግል ወይስ በቡድን የሰራችሁት?
4. ያቀረባችኋቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከየት መረጣችሁ? (ከመርሃ ትምህርት፣ ከፍሰት ሰንጠረዥ፣...)
5. ከመርሃ ትምህርቱ ወጣ ለማለት ወይም መርሃ ትምህርቱ ውስጥ ካሉት ውስጥ ላለማካተት አስገዳጅ ሁኔታዎች ገጥመዋችሁ ነበር?
6. በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አቀረባችኋቸው? (ከግልጽነት፣ ከትክክለኛነት፣ ከተገቢነት፣ ከሚዛናዊት/ተመጣጣኝነት፣... አኳያ)
7. በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዴት አደራጃችኋቸው? (ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት፣... አኳያ)
8. ሰዋስዋዊ ቅርጽን፣ ፍችንና አገባብን በተመጣጠነ መልክ ለማቅረብ አልማችሁ ሰርታችኋል? (ተናጠላዊ ወይስ አገባባዊ አቀራረብ ነው የተጠቀማችሁት?)
9. የአርትኦት ስራውንና የማጣሪያ ንባቡን እንዴት አከናወናችሁት?
10. መማሪያ መጻህፍቱ ታትመው ስራ ላይ ከዋሉ በኋላ የተመለከቷቸው ወይም ከሌላ ሰው/አካል ያገኙት ምጋቤ ምላሽ አለ?
11. በአጠቃላይ ስለመፃህፍቱ ዝግጅት ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን የሚሉት ካለ፡፡

**ከልብ አመሰግናሁ!**

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸውና የፈረምኩት ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም፡-** **ባዩ ተሾመ** **ፊርማ፡-** [signature]

**አድራሻ፡-**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፡፡

**ቀን፡-** 28/10/2004

**አማካሪ፡-** **ጌታሁን አማረ (ዶ/ር)** **ፊርማ፡-** ____________________

**ቀን፡-** ____________________